አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
የጆርናሊዝም እና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍ
እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ከተራ መውሰድ አንጻር፤ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና

በ

አስቴር ገመዳ

ግንቦት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ከተራ መውሰድ አንጻር፤ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አስቴር ገመዳ

ግንቦት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ከተራ መውሰድ አንጻር፣ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና

በ

አስቴር ገመዳ

ግንቦት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ጥ. ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

የፈተና ቦርድ አባላት ፊርማ

አማካሪ 1. ጌታቸው አንዳሉማሬ _____

ፈታኞች 1. ጌታሁን አመጋሪ (ዶ/ር) _____

2. አንዳጋው አንተነህ (ዶ/ር) _____

ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከ ተጠነቃቀበት ጊዜ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጽሁፌን በተደጋጋሚ በማንበብ፣ ተገቢው ማስተካከያ ይደረግ ዘንድ፣ ገንቢ አስተያየታቸውንና ያላሰለሰ ምክራቸው ላልተለየኝ መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ጌታቸው እንዳላማው ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በተጨማሪም የጥናቱ ዓላማ ይሳካ ዘንድ መረጃውን በመስጠት ለተባበሩኝ ለአግዓዚያን ቁጥር ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርት ለወ/ት ጽጌ እሸቱ እና ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸው። እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ነጻ የትምህርት እድል የሰጠኝን የስዊድን መንግስት እና በጀት በመፍቀድ ጥናቱን እንዳከናውን የተባበረኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ክልብ አመሰግናለሁ።

ከዚህም ባሻገር ሃዘኔን በማስረሳት ጥናቱን እንድሰራ ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉልኝን የትምህርት ክፍሉ መምህራን አቶ ደረጀ ገብሬ፣ ዶ/ር ጌታሁን አማረ፣ አቶ ጌታቸው እንዳላማው እና ለክፍል ጓደኞቼ በሙሉ በተለይም ተማሪ ብርሃኔ አድማሱ ቀረጻውን ወደ ጽሁፍ በመቀየር የረዳችኝ እና ከጎኔ በመሆን የጓደኝነት ምክሯን እየለገሰች ያጠነከረችኝን ክልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

በመጨረሻም በሞራልም ሆነ በገንዘብ ድጋፍዋ ላልተለየችኝ እናቴ ለወ/ሮ ቅመም አበበ፣ እንደ እናት አባት ሆና አሳድጋ ለዚህ ያበቃችኝ እና መጨረሻዬን ለማየት ስትጓጓ ያልተሳካላት፤ የልፋቴን ፍሬ ለማየት ወራት ሲቀራት ለተለየችኝ አያቴ እማሆይ አበበች ጎንፋ እና ለጥናቱ የሚሆነውን መረጃ በመተርጎም ለረዳኝ ለጥላዬ ፍቃዱ ምስጋናዬ ክልብ የመነጨ ነው።

ማስታወሻነቱ

እድሜዋን በሙሉ ከእኔ ጋር
ተንገላታ ለእዚህ ያደረሰችኝና
የልፋቷን ውጤት ሳትመለከት
ለቀረችው ለእናቴ ለእማሆይ
አበበች ጎንፋ ይሁንልኝ!!!

ማውጫ

ገጽ

አርዕስት

ምስጋና i

የሰንጠረዥ ማውጫ vi

አጎጽሮተ ጥናት vii

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 4

1.5 የጥናቱ ወሰን 4

1.6 ምህጻረ ቃላትና ምልክቶች 5

1.6.1 ምልክቶች 5

1.6.2 ምህጻረ ቃላት 7

ምዕራፍ ሁለት ፡- ክለሳ ድርሳናት

2.1 የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ምንነት 8

2.2 የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትንተና 10

2.3 የተራ መውሰድ 11

2.4 የተራ መውሰድ ውቅሮች 11

2.5 የተራ መውሰድ አካላት 14

2.5.1 የተራ መገንቢያ አሃድ (turn constructional unit) 15

2.5.2 የተራ አሰጣጥ አካል (turn allocation component) 16

2.5.3 የአርምሞ ጊዜ (silence time) 16
2.5.4 የተራ መቋረጥ እና ድርርቦሽ (interruptions and overlaps) 17
2.5.5 ማስተካከያ (repair) 18
2.6 የተራ መውሰድ መርሆች (principles of turn taking) 20
2.7 አለማቀፋዊ የተራ መውሰድ ህጎች 20
2.8 የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህጎች 22
2.9 ተራ መውሰድ በንግግር ልውውጥ ውስጥ 24
2.10 የንግግር ልውውጥ ባህሪያት 26

ምዕራፍ ሶስት፡-የጥናቱ ዘዴ

3.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች 28

3.2 መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ 29

3.3 በቀረጻ የተገኙ መረጃዎችን መተንተኛ ሞዴል 29

3.4 የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን 29

ምእራፍ አራት፡- የመረጃ ውጤት ትንተና እና ትርጉማ

4.1 የተራዊ ንግግር ድግግሞሽ.....31

4.2 የተራ መውሰድ አካላት 32

4.2.1 ተራን መገንቢያ አሃዶች 32

4.2.2 ባለተራን መምረጫ ስልቶች 38

4.2.3 ማስተካከያን መሻት 39

4.2.4 ድርርቦሽ 43

4.3 በተራ መውሰድ ወቅት ተደጋግመው የተከሰቱ ውቅሮች 47

4.3.1. ማነሳሳት- ምላሽ- ግምገማ 47

4.3.2. ማነሳሳት- ምለሽ- ምጋቤ ምላሽ 50

4.3.3 ጥያቄ-ምላሽ.....51

4.4 በተራ መውሰድ ወቅት የተራ አሰጣጥ ሂደት 53

4.5 የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህጎች 55

4.6 በራስ ተነሳሽነት ተራ መውሰድ 57

ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ እና ጠቋሚ አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ 60

5.2 ጠቋሚ አስተያየት.....63

ዋቢ ጽሁፎች 65

አባሪዎች

ቀረጻ አንድ 70

ቀረጻ ሁለት 83

ቀረጻ ሶስት 99

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ ገጽ

1. የተራ አወሳሰድ መጠናዊ ንጽጽር በመምህራ እና በተማሪዎች መካከል.....31
2. የተራ መገንቢያ አሃዶች ስርጭት.....36
3. የተራዊ ንግግር ርዝመት.....37

አጎጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማዓዚያን ቁጥር ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የመምህር እና ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ዲስኩርን ከተራ መውሰድ አካያ መተንተን ነው። ይህንን ዓላማውን ከግብ ለማድረስም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ አድርጓል። እንዲሁም መቅረጸ ድምጽ ወምስል ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ በጥቅም ላይ ውሏል። በዚህም የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ሂደቱ ቀረጻ ተካሂዶ ተተንትኗል። በትንተናው መሰረትም አንደኛው በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በተራ መውሰድ ወቅት ተደጋግሞ የተከሰተው የተራ መውሰድ ውቅር ጥያቄ-መልስ ወይም ማነሳሳት-ምላሽ ነው። ሁለተኛው የተራ መውሰድ አካላት የሚባሉት ተራን መገንቢያ አሃድ፣ ተራን መምረጫ ስልት፣ መቋረጥ ወይም ድርርቦሽ፣ አርምሞ እና ማስተካከያ ናቸው። እያንዳንዳቸውን ከጥናቱ ግኝት አንጻርም ስንፈትሽ፡- ተራን መገንቢያ አሃዶች ናቸው ብለው ምሁራን የጠቀሷቸው ቃላዊ፣ ድምጻዊ፣ ሀረጋዊ እና ዓረፍተ ነገራዊ የተራ መገንቢያ አሃዶች በጥናቱ የተከሰቱ ሲሆኑ በዚህ ጥናት ግን ከነዚህም በተጨማሪ አዲስ ተራ መገንቢያ አሃድ ግጥም ተከስቷል። ማስተካከያን መሻት ተሳታፊዎች በመናገር፣ በማዳመጥ እና በመረዳት ረገድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች፣ መፍትሄ የሚሰጡበት ነው። በክፍል ውስጥ ተራዊ ንግግርም ይህ ስልት ለዚሁ ተግባር ሲከናወን ተስተውሏል። በዚህ ጥናት የተገኘው ግኝት እንደሚጠቁመው በተራ መውሰድ ወቅት ከሚደረጉ አራት ማስተካከያዎች ውስጥ ሶስቱ ብቻ ተግባራዊ መሆናቸውን ነው። ከተራ አሰጣጥ ረገድ ስንመለከት በዚህ ጥናት አብዛኛውን ጊዜ ተራ የሚሰጡት መምህርቷ ሲሆኑ ተራውን የሚቀበሉት ደግሞ ተማሪዎች ናቸው። ሂደቱ ተመሳሳይ ሆኖ እያለ አንዳንድ ጊዜ ተራ ሳይሰጣቸው ለራሳቸው ተራ በመስጠት ንግግር የሚያደርጉ ተማሪዎች ግን ተራውን ከተማሪዎች የሚቀበሉበት ሁኔታም አለ። ሶስተኛው ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ የሚወስዱት የጥያቄዎች መቅለል፣ መምህርቷ ምላሽ በመስጠት ላይ እያሉ ሳይጨርሱ ለተማሪዎቹ ልቅ ወይም ክፍት አድርገው ሲተው፣ የተረኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ምላሽ ስህተት መሆን እና የሌሎች ተማሪዎች ምላሹ ስህተት መሆኑን ማወቅ ወዘተ በራስ ተነሳሽነት ለሚወሰድ ተራ መውሰድ አበይት ምክንያቶች ናቸው። በተራ አወሳሰድ ረገድ ደግሞ ተማሪዎች ከመምህርቷ በበለጠ ብዙ ተራዎችን እንደወሰዱ ጥናቱ አሳይቷል። የተራዊ ንግግር ቃላት ብዛትን በተመለከተም የመምህርቷ አንጻራዊ ርዝመት ታይቶባቸዋል። ከዚህ ግኝት በመነሳትም የትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች የንግግርን ክሂል በመምህራን ስልጠና ውስጥ ቢያካትት፣ መምህራን የክፍል ውስጥ ዲስኩርን በመተንተን የክፍል ውስጥ መስተጋብራቸውን ቢያሻሽሉ፣ በዚህ ጥናት የተገኙ አዲስ ግኝቶች የሆኑት የተራ መውሰድ ውቅሮች እና የተራ መገንቢያ አሃዶች አዲስ ጥናት ቢካሄድባቸው...ይበልጥ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናን በማሳየት የመማር ማስተማር መስተጋብሩን ሊያሻሽሉ ይችላሉ የሚሉት ጠቋሚ አስተያየቶች ናቸው።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ጀምሮ የብዙ ጥናታዊ ምርምሮች ዋነኛ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ከነዚህም ተጠቃሾቹ ስነልሳን፣ ተግባራዊ ስነልሳን እና ስነ ትምህርታዊ ምርምሮች ናቸው (ክርስቲ፣2002)። ስንክሌየር እና ኮልተርድ (1975፣15) እንደሚጠቁሙት የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ጥናት ቋንቋን መሰረት በማድረግ የተጀመረው በ1940 አካባቢ ነው። በ1960 እና በ1970 መጀመሪያ አካባቢ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሀገራት በዲስኩር ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ብዙ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናዎች ተከሂደዋል። ይህም ብዙ ምሁራን በስነልሳን እና በተግባራዊ ስነልሳን ዙሪያ ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምር አድርጓል።

እንዲሁም የመቅረጸ ድምጾች በኋላም በመቅረጸ ምስል ወድምጽ በመታገዝ የዲስኩር ትንተና ስራ ተደራሽ እንዲሆን አድርጎታል። ከዚሁም ጋር ተያይዘው ብቅ ያሉ እጅግ በጣም ብዙ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ሞዴሎች አሉ። የተወሰኑት በብዙ የስነልሳን ልማዶች (Lingustic traditions) ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በዘርዓሰብ አቀራረብ (Ethnographic approach) በስነልቦናዊ አቀራረብ ዙሪያ የተመሰረቱ ናቸው። ሌሎች የትምህርት መስኮች እሳካሁንም ማንኛውንም ተገቢ የመሰላቸውን በትምህርታዊ ወይም በስነ ትምህርታዊ ምርምሮች (educational or pedagogical research) የሚታዩ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ (ስንክሌየር እና ኮልተርድ፣1975)።

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና የተራን ጠብቆ መናገር ውቅሮች እና በመማር ማስተማር ላይ ያላቸውን ውጤት ለመመርመር መሳሪያ ነው (ራይምስ፣2008)። ይህም ማለት የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በመምህር ተኮርም ሆነ በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሒደት ተራ መውሰድ በተግባር ላይ መዋሉን ሲሆን፤ በተወሰነ መልኩ ልዩነት የሚፈጠረው የተራ መውሰዱ እና መቀበሉ መጠን እና በሚፈጠረው የተራ መውሰድ አይነት ላይ ነው።

እንደ ክራምስች (1987፣22) አባባል ከሆነ በመምህር ተኮር መስተጋብር ሒደት ወቅት መምህሩ ቀጣይ ተናጋሪ ይመርጣል። እንዲሁም ተማሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ

ያደርጋል። ተማሪዎች በመነቃቃት እርስ በርስ እንዲደማመጡ የማድረግ መጠኑ ዝቅተኛ ነው። ከዚህ በመነሳት ተራ ምንጊዜም የሚሰራጨው ከመምህሩ ወደ ተማሪዎች እንደገና ተመልሶ ወደ መምህሩ ነው ማለት እንችላለን። ይሁን እንጂ በተማሪ ተኮር ክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ከተማሪ ወደ ተማሪ የሚሆንበትም መንገድ አለ።

ቫንላየር (1988፣94) እንደሚጠቁሙት የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በተለይ ትኩረት የሚያደርገው በክፍል ውስጥ ማን እንደሚናገር እና ተናጋሪዎቹ መቼ ለህግ እንደሚገዙ ማጥናት ላይ ነው። በተጨማሪም ቫንላየር እንደሚሉት ከላይ የተጠቀሱት የክፍል ውስጥ መስተጋብሮች ትኩረት (የተናጋሪዎች ማንነት እና ለህግ የሚገዙበት ጊዜ) በየትኛውም ቦታ የሁሉም ዲስኩር ትንተና ባህሪያት ናቸው። ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ለህግ የሚገዙበት ጊዜ ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ እንደ ግዴታ እና ገደብ ሊሆን ይችላል።

ይህ ማለት መስተጋብሩ የሚካሔድበት መንገድ የተማሪዎቹ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል። ምሁራን እንደገለጹት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ተማሪዎች ቋንቋን ተጠቅመው እንዲናገሩ እና ተማሪዎች እርስ በእርስ ንግግር እንዲያደርጉ እድሉን በማመቻቸት ይደግፋል ወይም ያበረታታል (ኦልራይት፣ 1984፤ ኤሊስ፣ 1988፤ ቫንላየር፣1988) ።

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር ከማድረግ በላይም ያሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን በመጠቆም ለተማሪዎች አመቺ የሆኑ የመማሪያ መጻህፍትን እና መልመጃዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል (ብራውን እና ዩል፣1983) ።

ስለዚህ በክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ውቅሮች ላይ ጥልቅ ምልከታ ማካሄድ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለመመርመር በጣም ጠቃሚ ነው።

ይሁን እንጂ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ውቅሮች ዙሪያ የተካሄደ ጥናታዊ ምርምር የለም። በተወሰነ መልኩ ከዚህ ርእስ ጋር ባይገናኝም በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ ንግግር ልውውጥ የተካሄደ ጥናት ሲኖር ጥናቱንም ያካሄዱት ከበደ ይመር (2000) ሲሆኑ ርዕሳቸውም "የንግግር ልውውጥ ትንተና" የሚል ነው። ጥናታቸውም በንግግር ዲስኩር ስር ይመደባል። ይሁን እንጂ የከበደ ይመር ጥናት የንግግር ልውውጥ ውቅሮችን አጠቃላይ የሚመለከት በመሆኑ አጥኚዋ ከንግግር ልውውጥ መካከል አንዱ የሆነውን ተራ መውሰድን ከክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና አንጻር እንድትመለከት መንገድ አመልክቷታል።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር

የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማሻሻል እና ተጨማሪ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማድረግ የተራን ጠብቆ መናገር ውቅሮችን ማጥናት ቀላል ባይሆንም አስፈላጊ ነው። ክራምሽች (1987፣22) እንደሚገልጹት ተማሪዎች እንዴት ተራን ጠብቀው መናገር እንዳለባቸው ማስተማር ቀላል አይደለም። ስለዚህ ይህ መጠናት የሚያስፈልገው ችግሮች በስፋት የሚታዩበት አካባቢ ነው ይላሉ።

ከችግሮቹም መካከል አንዱ መምህርቷ በስራ ላይ በነበረችበት ወቅት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ህጎችን ተግባራዊ ሲያደርጉ አለማስተዋሏ አጥኚዋን ጥናቱን እንድታካሄድ መነሻ ሆኗታል። ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት ጥናት ያልተካሄደበት በመሆኑ አጥኚዋ ጥናቱን እንድታካሄድ ፍላጎት አድሮባታል።

ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

1. በተራ መውሰድ ሂደት ተደጋግመው የሚከሰቱት ውቅሮች ምን ምን ናቸው?
2. ተማሪዎች እና መምህራን የትኛውን የተራ መውሰድ ህግ ተግባራዊ ያደርጋሉ?
3. በተራ መውሰድ ሂደት ውስጥ ማን ለማን ተራ ይሰጣል ወይም ማን ከማን ተራን ይቀበላል?
4. ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነትስ ተራ ይወስዳሉ ወይስ አይወስዱም? የሚወስዱ ከሆነ ምን ክስተት ሲፈጠር ነው?

1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተራ መውሰድ አደረጃጀት እና የተራ መውሰድ ህጎች አተገባበር ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንጻር መመራመር ላይ ነው። ጥናቱም በዝርዝር የሚመለከተው የተማሪዎችን እና የመምህራንን የተራ አወሳሰድ ሂደትን ዓላማ በማድረግ ነው። ስለዚህ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. በተራ መውሰድ ሂደት ተደጋግመው የሚከሰቱ ውቅሮችን መለየት፤
2. ተማሪዎች እና መምህራን ተግባራዊ የሚያደርጉትን የተራ መውሰድ ህግ መመርመር፤
3. በክፍል ውስጥ ማን ለማን ተራ እንደሚሰጥ እና ማን ከማን ተራ እንደሚቀበል መፈተሽ፤

4. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ተራን የሚወስዱ መሆን አለመሆናቸዉን መለየት እና የሚወስዱ ከሆነ የሚወስዱበትን ጊዜ ማጥናት፤

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት አሁን ተጠናቆ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይኖረዋል፡፡

1. የክፍል ውስጥ ዲስኩርን በመተንተን መምህራን በክፍል ውስጥ በሚደረጉ ንግግሮች አካባቢያዊ ልዩነቶችን (የተማሪዎችን ዳራ እና የባህል ልዩነትን) እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡
2. መምህራን የክፍል ውስጥ ዲስኩርን ሲተነትኑ ስነትምህርታዊ ውጤታማነት ይሻሻላል፡ ይህም ሲባል የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር፣ በመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ይዘቶችን ለማካተት እና መልመጃዎችን ለማዘጋጀት ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ለመማሪያ መጻህፍትና ለመርህ ትምህርት አዘጋጆች የትኩረት አቅጣጫን ይጠቁማል፡፡
3. ለንግግራዊ ዲስኩር በተለይም ለንግግር ክሂል ትምህርት መጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለንግግር ትምህርት ይዘት መረጣና ትኩረት እገዛ ያደርጋል፡፡
4. ከዚህ በኋላ ለሚያጠኑ አጥኚዎች መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.5. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ዓላማ በተማሪዎች እና መምህራን ተራ አወሳሰድ ሂደት ተግባራዊ የሚሆኑ የተራ መውሰድ አደረጃጀቶች እና ተግባራዊ የሚሆኑ ህጎችን መመርመር እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የሚያተኩረው፡-

- በንግግር ዲስኩር ወይም በቃላዊ ገለጻ ላይ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃውን ለመሰብሰብ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር እና የቋንቋ መምህራንን መልካም ፍቃድ የሚጠይቅ በመሆኑ እና በተጨማሪም ጥናቱን ለማካሄድ የተፈቀደው ጊዜ እና ገንዘብ በቂ ባለመሆኑ ጊዜን እና ገንዘብን ለመቆጠብ እንዲሁም የጥናቱን ውስብስብነት ለማስወገድ ሲባል ነው

- ከይዘት አንጻርም ሲታይ ትኩረቱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመምህር ተማሪ ንግግር ልውውጥ ላይ የተማሪዎች እና መምህራን ተራ አወሳሰድ ላይ ነው።
- ስለሆነም ይህ ጥናት ተደጋግመው በሚከሰቱት የተራ መውሰድ ውቅሮች ፣ በአደረጃጀት ስርዓቶቹ፣ ተራ መውሰድ ህጎች፣ ማስተካከያን በመሻት እና በመስጠት ስልቶቹ ተራን በመለዋወጫ ዘዴዎቹ ና በንግግር ድርርቦሾቹ ላይ ብቻ ይመሰረታል፤ ያተኩራል።

1.6. ምልክቶች እና ምህጻረ ቃላት

1.6.1. ምልክቶች

በጽሁፋዊ መረጃ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ ምልክቶች

@አሃድ@	በሳቅ መካከል የሚደረግ ንግግር
@@@	ሳቅ
..,...	መቋረጥ (እስከ 2 ሰኮንድ)
º º	ከንግግር ልውውጡ ውጭ ዝቅ ባለ ድምጽ የሚደረግ ንግግር (የማይሰማ ድምጽ)
[ ]	ድርርቦሽ
-	አስፈላጊ የሆነ የንግግር መቋረጥ
( )	ግልጽ ያልሆኑ ጽሁፋዊ መረጃዎችን ማመልከቻ
(( ))	የአጥኚው አስተያየት
(.)	ጊዜውን ያልጠበቀ አጭር መቋረጥ
//	ይህ የሚያሳየው የአሁኑ ተናጋሪ ንግግር በሌላ ሰው ንግግር የሚደረብበት ቦታ
[	የግራ ቅንፍ የሚያመለክተው ድርርቦሹ የሚጀምርበትን ቦታ ነው
]	የቀኝ ቅንፍ የሚያመለክተው የሁለቱ ተናጋሪዎች ድርርቦሽ የሚያልቅበትን ቦታ ነው

= የእኩል ይሆናል ምልክት ምንም እረፍት እና ክፍተት ያለመኖሩን ያመለክታል። ሁለት የእኩል ይሆናል ምልክት አንዱ በመጀመሪያው መስመር መጨረሻ ላይ እና ሌላኛው በሁለተኛው መስመር መጀመሪያ ላይ በማስገባት ምንም ክፍተት አንዳሌላ እንጠቀምበታለን።

—— ያለምንም ንግግር ያለፈ አጭር ጊዜን ያመለክታል።

↑ የሚያመለክተው ከፍ በማድረግ የሚካሄድን ንግግር (የድምጽ አነሳስን) ነው።

↓ ዝቅ በማድረግ የሚካሄድ ንግግርን ይመለከታል።

::: ረጅም ድምጽን ያመለክታል።

. የተሳሳተ ንግግር የቆመበት ቦታ

⊤ ⊥ የመጀመሪያው ተናጋሪ ተጨማሪ ሃሳብ በመስጠት ላይ እያለ ሁለተኛው ተናጋሪ ተደርቦ የሚናገርበትን ቦታ ያመለክታል።

›‹ በዚህ ምልክት ውስጥ ያስቀመጥነው ንግግር ወይም ድምጽ በአካባቢው ካሉ ንግግሮች ወይም ድምጾች ጎልቶ የሚወጣ ከሆነ ነው።

(∅) ምንም አይነት ንግግር የማይኖርበት ጊዜ ለማመልከት እንጠቀምበታለን። በዚህ ጊዜ ልንሰማ የምንችለው የተረጋጋ መንፈስ የተሞላበት የተናጋሪዎች የእርስ በርስ ውይይት ነው።

‹› በምልክት ውስጥ የተቀመጠ ንግግር በአካባቢው ካሉ ድምጾች ጎልቶ የማይሰማ ከሆነ ነው።

1.6.2. ምህጻረ ቃላት

መ/ት= መምህርት

ወተ = ወንድ ተማሪ

ሴተ = ሴት ተማሪ

ተህ = ተማሪ በህብረት

ቀ1 = ቀረጻ አንድ

ቀ2 = ቀረጻ ሁለት

ቀ3 = ቀረጻ ሶስት

ሴተ1 = የመጀመሪያዋ ሴት ተማሪ

ሴተ2 = ከመጀመሪያዋ ሴት ተማሪ በመቀጠል በክትትሎሽ የገባች ሌላ ተማሪ

ወተ1 = የመጀመሪያው ወንድ ተማሪ

ወተ2 = ከመጀመሪያው ወንድ ተማሪ በመቀጠል በክትትሎሽ የገባ ሌላ ወንድ ተማሪ

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1. የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ምንነት

ኦልራይት (1980) እና ቫንላየር (1988) እንደሚሉት ተፈጥሮኣዊ ትርጓሜ ያለው የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በብዛት በክፍል ውስጥ በሚገኙ አካላት ላይ ያተኩራል። ከነዚህም መካከል መምህራን፣ ተማሪዎች እና ምልከታ የሚያካሄደው ወይም ተመራማሪው ተጠቃሽ ናቸው። ኩማራቫዲቭሉ (1999) በጥናታቸው እንደገለጹት ባካሄዱት ጥናት ውስጥ ብዙ ሃሳቦችን ያካተተን የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ጥቅም አሳይተዋል። ማንኛውም የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በታሰበው እና በተደራሹ ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት መተንተን አለበት። በአንድ በኩል በመምህሩ ሃሳብ እና በተማሪው ትርጓሜ መካከል ባለው ልዩነት እና በሌላ መልኩ በመምህሩ እና በተማሪው ሃሳብ እና በተመልካቹ ትርጓሜ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ማተኮር አለበት ይላሉ።

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናን ምንነት በተመለከተ ብዙ ምሁራን የራሳቸውን ፍቺ ሰጥተዋል ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

ራይምስ (2008) የክፍል ውስጥ ዲስኩርን ፍቺ በአጭሩ ሲገልጹ ፦

> *የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ማለት አውድ እና ንግግር እንዴት አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርጉ ለመረዳት የሚደረግ ነው። በመማሪያ ክፍል አውድ (አውድም ከክፍል ውጭ እና በክፍል ውስጥ በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ተጽእኖ እንደሚደርስበት በመረዳት) በአገልግሎት ላይ የዋለን ቋንቋ መተንተን ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል።*

ቫንላየር (1988፣94) እንደሚጠቁሙት የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በተለይ ትኩረት የሚያደርገው በክፍል ውስጥ ማን እንደሚናገር እና ተናጋሪዎቹ መቼ ለህግ እንደሚገዙ በማጥናት ላይ ነው። በተጨማሪም ቫንላየር እንደሚሉት ከላይ የተጠቀሱት የክፍል ውስጥ መስተጋብሮች ትኩረት (የተናጋሪዎች ማንነት እና ለህግ የሚገዙበት ጊዜ) በየትኛውም ቦታ የሁሉም ዲስኩር ትንተና ባህሪያት ናቸው። ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ለህግ በሚገዙበት ጊዜ ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ እንደ ግዴታ እና ገደብ ሊሆኑ ይችላል።

በልማዳዊ ዘዴ መምህራን እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮች የክፍል ውስጥ ዲስኩርን ለመተንተን ተማሪዎች በተግባር በሚያሳዩአቸው እና በክፍል ውስጥ በሚፈጥሯቸው አዳዲስ ነገሮች ላይ ያተኩሩ ነበር። በተጨማሪም የተማሪዎችን እውቀት ወይም የትምህርት አቀባበላቸውን የሚመዝኑት ተማሪዎች በሚያስመዘግቡት ነጥብ (grade)፣ በፈተናዎች፣ በሚሰሯቸው የቤት ስራዎች እና ስለባህሪያቸው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ ተመስርተው ነው።

እንደ ማህበረሰባዊያን የትምህርት አመለካከት (Social constructivist perspectives) ከሆነ እውቀት የምናገኘው እና ለአንድ ነገር ትርጉም የምንሰጠው አእምሮአችን ለነገሮች ትርጉም ለመስጠት በሚያከናውነው ተግባር ላይ በመመስረት ብቻ ሳይሆን በዲስኩር እና በማህበራዊ መስተጋብር ላይም በመመስረት ነው። ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በክፍል ውስጥ መምህራን እና ተማሪዎች ለተግባቦታቸው የሚጠቀሙበትን ቋንቋ በክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ላይ በማተኮር የሚመረመርበትን መንገድ ጠቁሟል። የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና አላማ መምህራን በክፍል ውስጥ መስተጋብር ወቅት የሚፈጠሩ ውቅሮችን በማገናዘብ አግባብነት ያለውን የማስተማሪያ ዘዴ እንዲመርጡ መርዳት ነው። በተጨማሪም መምህራን በክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና የክፍል ውስጥ መስተጋብር ሂደት ተገቢውን የማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ የራሳቸውን የክፍል ውስጥ መስተጋብር እና የተማሪዎችን የመማር ሂደት ለመለወጥ የተሻለ እድል ይኖራቸዋል (ሩገን፣2010)።

ከማህበረሰባዊያን የትምህርት አመለካከት በተጨማሪም የቋንቋ መማር ማህበረሰባዊ ተፈጥሮ (The Social nature of learning) የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናን እና የቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ ኖርተን እና ቶህይ (2002) የሚከተለውን ሃሳብ አቅርበዋል። የቋንቋ መማር ማህበረሰባዊ ተፈጥሮ በክፍል ውስጥ የቋንቋ ተማሪዎች ማንነት እና ተሳትፎ ላይ ያተኩራል። ቋንቋን መማር ለጥንት ተማሪዎች (Traditional students) ትርጉም ሲሰጥ ይህንንም ይገልጹ የነበሩት በፍቃደኝነት በመሳተፍ እና ለቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ እውቀት በመጨበጥ ነው። በሌላ አባባል የቋንቋ መማር ማህበረሰባዊ ተፈጥሮ ተማሪዎች የተማሩት ትምህርት ከተማሩበት ዘዴ ጋር እንዴት ይዛመዳል የሚል ነው። ስለዚህ ትምህርታዊ ምርምር ማተኮር ያለበት አንድ ተማሪ መቀበል በሚችለው እውቀት እና ክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ባለ ማህበረሰባዊ መዋቅር እና በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ተማሪዎች ሊይዟቸው በሚችሏቸው ባህሪያት እና አመለካከቶች ላይም መሆን አለበት። በተመሳሳይ መልኩ

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናም እነዚህን የሚያደርግ ነው። በክፍል ውስጥ የሚከሰቱ የንግግር መዋቅሮችን በመመልከት እና ለተማሪዎች የተሰጣቸውን ትኩረት በመገንዘብ መፍትሄ ይፈልጋል (ሬክስ እና ስኪለር፣ 2009)።

2.2. የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትንተና

የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትንተና በክፍል ውስጥ መምህራን እና ተማሪዎች የሚያደርጉትን መስተጋብር ቃላዊ ባህርይ ለማጥናት ቀድመው የተመረጡ እና ቀድመው የተወሰኑ ምልከታዎችን ይጠቀማል። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ባይጠቀስም የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትንተና ትውረታዊ መሰረቱ የሚታዩ ባህሪዎችን ባልተዛባ ትንተና ላይ የሚያተኩረው ባህሪያዊ ስነልቦና ነው። በዚህም መሰረት ለክፍል ውስጥ መስተጋብር ትንተና ምልከታ ያስፈልጋሉ ተብለው የሚታሰቡት መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት ባህሪያት እና የመምህራን ማህደር (portfolio) ናቸው። እነዚህ ነገሮችም በአጠቃላይ የትምህርት መስክ ጥንታዊ እና ታዋቂ በሆነው በ1970 በእነፍላንደርስ በተዘጋጀው "The Flanders interaction analysis categories" በተሰኘው እቅድ ውስጥ በደንብ ተንጸባርቀዋል። የፍላንደር ሞዴል በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተከታታይ የሆኑ ዘዴዎችንም አብራርቷል (ኩማራቫዲቬሉ፣ 1999፡455)።

የመስተጋብር ዘዴ (Interaction scheme) መጠቀም የክፍል ውስጥ አላማን እና ሂደትን በተለይም የመምህርና የተማሪ ንግግርን ለመገንዘብ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን ሁሉም የመስተጋብር ዘዴ የሚከተሉት ድክመቶች አሉባቸው (ኩማራቫዲቬሉ፣ 1999፡455-456)።

1. በተማሪዎች እና በመምህራን ቃላዊ ባህሪይ ውጤት ላይ ብቻ በማተኮር ለክፍል ውስጥ ሂደት እና ለትምህርቱ ውጤት ዝቅተኛ ወይም ምንም ግምት አይሰጥም።
2. በቁጥራዊ መለኪያ ላይ ብቻ በማተኮር ወደ ቁጥር መለወጥ ለማይችሉት የተግባቦት ሃሳቦች ትኩረት አይሰጥም።
3. የመስተጋብር ዘዴዎች በአንድ አቅጣጫ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ማለትም የመረጃ ፍሰቱ ከተመልካቹ ወደ መምህሩ ሲሆን፤ ተመልካቹም እንደ ተቆጣጣሪ ወይም እንደ ሱፐርቫይዘር ሊወሰድ ይችላል።
4. በአንድ አቅጣጫ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ናቸው። ምክንያቱም የምልከታቸው መሰረት በአብዛኛው በአንድ አንጻር ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፤ ይህም በተመልካቹ ላይ ብቻ ነው።

ስለሆነም የመስተጋብር ዘይቤው በሚታዩ የመምህሩ ባህሪይ ላይ ተመልካቹ ባለው ግንዛቤ ላይ ያተኩራል።

2.3. ተራ መውሰድ

የንግግር ልውውጥ ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚሳተፉበት የንግግር መስተጋብር ነው። ስለሆነም የመናገር እድሉ ለተሳታፊዎቹ የሚዳረሰው በዘፈቀደ ሳይሆን ማን፣ መቼና ለምን ያህል ጊዜ ይናገር በሚለው ተራን ጠብቆ በመናገር ስምምነት ነው (ሪቻርድስ፣1980፣424)። "ተራ አንድን ነገር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በአግባቡ ለማከናወን ያግዛል" (ሳክስ እና ሌሎች፣1974)። ከበደ ይመር (2000) ሆፐር እና ሌሎች (1986፣170)ን ዋቢ በማድረግ እንደገለጹት "እያንዳንዱ ተሳታፊ ንግግሩን መቼ ይጨርስ? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄም በንግግር ልውውጥ ጊዜ ያጋጥማል። የዚህ ችግር መሰረታዊ መፍትሄ ደግሞ ‹በአንድ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ ይናገር› የሚለው ህግ ነው" ይላሉ።

በምሁራኑ ገለጻ መሰረት የንግግር ልውውጥ አድራጊዎች ሀሳባቸውን ተራ በተራ ያለ ችግር መግለጽ ይችሉ ዘንድ፣ በመናገር ላይ ያለው ሰው ንግግሩን ሲጨርስ፣ ቀጣዩ ተናጋሪ ተራውን ጠብቆ መናገር ይጠበቅበታል።

2.4. የተራ መውሰድ ውቅሮች

ተራ መውሰድ፣ ጥያቄን መጠየቅ እና መመለስ፣ ምጋቤ ምላሽ መስጠት እና ተማሪዎች ብዙ እንዲያስቡ ማድረግ አስፈላጊ የክፍል ውስጥ ዲስኩር አላባውያን ናቸው። በልማዳዊ ክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ውቅሮች ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ እና ማነሳሳት-ምላሽ-ምጋቤ ምላሽ ናቸው። እነዚህም የተራ መውሰድ ውቅሮች በክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ እና ተግባቦታዊ አውድ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ (ራይምስ፣2008፣155)። እንዲሁም ኒኮልስ (1993) እንደገለጹት በክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ባህላዊ የተራ መውሰድ ውቅሮች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም፦

1ኛ. ጥያቄ-ምላሽ-አስተያየት ሲሆን ይህም ከራይምስ ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ጋር ተመሳሳይ ነው።

2ኛ. ጥያቄ-አጸፋ ጥያቄ-ምላሽ-አስተያየት (Question-Counter question-answer-comment) ናቸው።

ኒኮልስ (1993) እንደሚጠቁሙት በክፍል ውስጥ ውይይት ተማሪዎች ርእሰ ጉዳይ ይመርጣሉ ወይም ይቆጣጠራሉ፤ ሆኖም ግን የባህላዊ ተራ መውሰድ ውቅሮች መለወጥ የክፍል ውስጥ ዲስኩርን አይለውጠውም። ራይምስ (2008፣156) እንደሚስማሙት ባህላዊ የተራ መውሰድ ውቅሮች በትምህርት ወቅት ለተወሰኑ ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዳይገልጹ ገደብ ሲሆንባቸው ለሌሎች ደግሞ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ (እንዲሳተፉ) ማበረታቻ ሲሆን ይስተዋላል። የባህላዊ ተራ መውሰድ ውቅሮች በቋንቋ ክፍል ውስጥ አድሎኣዊ የሆነ መምህር ተኮር ዲስኩርን ያስገኛሉ።

በክፍል ውስጥ የሚካሄድ መስተጋብር በዋናነት የሚመሰረተው በማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ላይ ነው። ራይምስ (2008፣158) ሁጅ መሃን (1985)ን በመጥቀስ እንደሚገልጹት ይህ አይነቱ የተራ መውሰድ ውቅር በመጀመሪያ የተጀመረው በሁጅ መሃን ነው። በዚህም መሰረት የሚከተለውን ቅደም ተከተል ይከተላል።

ማነሳሳት፡- መምህር፡ አሁን ስንት ሰኣት ነው

ምላሽ፡- ጃክሰን፡ 1፡30

ግምገማ፡- መምህር፡ በጣም ጥሩ ጃክሰን! (ራይምስ፣2008፣158)

ራይምስ (2008) እንደሚገልጹት ምንም እንኳን የንግግር መለዋወጥ በልማዳዊ ክፍል ውስጥ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ቢኖረውም ከላይ የተጠቀሰው አይነት ግምገማ ግን ከጓደኛ ጋር በሚደረግ ንግግር ውስጥ አይስተዋልም ይላሉ።

የማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ቅደም ተከተል ከክፍል ውጭ ከሚደረጉ የጥያቄ እና መልስ ቅደም ተከተሎች በግልጽ ይለያል። ምክንያቱም ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ጥያቄ እና መልስ ብቻ ሳይሆን ሶስተኛውን ቅጥያ ግምገማን ይጨምራል። በአብዛኛው ከክፍል ውጭ በሚደረጉ ንግግሮች ውስጥ ያለውን አረፍተ ንግግር በግልጽ አንገመግምም፤ በምትኩ ግን ምላሽ እንሰጣለን።

ለምሳሌ፡-

መረጃ መጠየቅ: መምህር 1: አሁን ስንት ሰኣት ነው

መረጃ መስጠት፡ መምህር 2: 1፡30

ቅድመ ንግግር መዝጊያ (Pre-closing): መምህር 1: ኦ! መሄድ አለብኝ

ንግግር መዝጊያ (Closing): መምህር 2: እሺ ነገ እንገናኛለን! (ራይምስ፤2008፣159)

በእርግጥ መምህር 2 ሰአቱን የመናገር ችሎታ አላቸው። ዋናው ጠቃሚ ነገር መምህር 1 የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘታቸው ነው። ነገር ግን የምላሽ ሰጪው ሰአት የሚያሳየው 1:32 ቢሆን ይህ ትንሽ ጉድለት በዚህ አውድ ቦታ አይሰጠውም። ስለዚህም የተሰጠን ምላሽ ትክክል ይሁን ስህተት መገምገም አንችልም (ራይምስ፤2008፣159)።

በመጠኑም ቢሆን ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ተማሪዎች ስለ አንድ ርእስ ያላቸውን እውቀት የመለኪያ ዘዴ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ይህ ቅደም ተከተል መሰረታዊ ክህሎትን እና መረጃዎችን ለማጠናከር ይረዳል። ነገር ግን ይህ ቅደም ተከተል ክፍሉን በበላይነት ሲገዛ መምህሩ መልእክቱን በቴሌቭዥን ወይም በሬድዮ ከሚያስተላልፍ ሰው በምንም አይለይም።

የክፍል ውስጥ ንግግርም ሆነ የማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ቅደም ተከተል ከግምገማም በላይ ብዙ ስራዎችን ለመስራት ያገለግላሉ።

እነሱም፡-

- ✓ ተራ በመውሰድ ምላሽ ለመስጠት ያነሳሳል።
- ✓ አዲስ ተማሪዎችን ለውይይት ይጋብዛል።
- ✓ ርእስን እንዲቀይሩ ይረዳቸዋል።
- ✓ ተማሪዎች በሂደት ወደ ሰፊ ርእሰ ጉዳይ እንዲያመሩ ይረዳቸዋል።
- ✓ የማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ቅደም ተከተል ተማሪዎች በአንድ ጉዳይ ላይ በጥልቀት እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል።
- ✓ በማነሳሳት ወቅት የሚነሱ ጥያቄዎች ተማሪዎችን ወደ ችግር ፈቺነት ሊወስዳቸው ይችላል።
- ✓ እንዲሁም ተማሪዎች ስለ አዲስ ርእሰ ጉዳይ ምን ያህል እንደሚያውቁ ለመለካትም ይረዳል።

በማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ የሚነሱ የጥያቄ አይነቶች በሁለት ይመደባሉ። እነሱም የታወቀ ምላሽ ያላቸው ጥያቄዎች (Known-answer questions) እና ልቅ ጥያቄዎች (open-ended questions) ናቸው። የታወቀ ምላሽ ያላቸው ጥያቄዎች የማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ቅደም ተከተል አነሳሾች ናቸው። አገልግሎታቸውም ጠያቂው የሚያውቀውን መረጃ ተማሪዎች እንዲያንጸባርቁ ማድረግ ነው። የታወቀ ምላሽ ያላቸው ጥያቄዎች መምህሩ በአእምሮው

የሚያውቀው አንድ እና አንድ ምላሽ ያላቸው ናቸው። በዚህም የተነሳ ራይምስ (2008፣161) ቀጥተኛ በሆነ ትችት "እኔ የማስበውን ገምት ወይም ተናገር እንደማለት ነው" ይሉታል።

ልቅ ጥያቄዎች እውነተኛ፣ ቀና፣ መረጃ ፈላጊ፣ የልዩነት ጥያቄ ወዘተ በመባል ይታወቃል። እነዚህ ጥያቄዎች አንድ ትክክለኛ ምላሽ ብቻ የማይሹ እና ጠያቂው በአእምሮው ምንም አይነት ቀድሞ ያሰበው ምላሽ ላይኖረው ይችላል። ስለሆነም ልቅ ጥያቄዎች መምህር መር ከሆነው የማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ ውቅር ይልቅ በተማሪ እና በመምህር መካከል ወደ ሚደረግ ውይይት የሚያመሩ ናቸው (ራይምስ፤2008፣162)።

2.5. የተራ መውሰድ አካላት

ሳክስ እና ሌሎች (1974፣696) "በንግግር ልውውጥ ወቅት ቀላል የተራ መውሰድ አደረጃጀት ዘዴ" በሚለው ጽሁፋቸው ተናጋሪዎች በንግግር ልውውጥ ዉስጥ የተራ አወሳሰድን የሚቆጣጠሩበትን ዘዴ ይገልጻሉ። ምንም እንኳን ተናጋሪዎች ቢቀያየሩም፣ የተራው ስፋት እና ቅደም ተከተል ቢለያይም፤ ምልክቶቹ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ጊዜ አንድ አካል እንዲናገር፣ ሽግግሩ በጥሩ ሁኔታ እንዲዋቀር እና ተራ ለመስጠትም (turn allocation) እንዲመች ያገለግላሉ።

እንዲሁም ደግሞ ሳክስ እና ሌሎች (1974፣697) እንደሚገልጹት የተራ መውሰድ ህግን ፣የንግግር ልውውጥን በሚያስተካክሉ፣ ተራን በሚያስጠብቁ፣ ክፍተትን (gap) እና መደራረብን (overlap) ለመቀነስ የሚያገለግሉትን በሁለት አካል ና በተለያዩ ህጎች ይገልጹዋቸዋል። የመጀመሪያው አካል የተራ መገንቢያ አካል (turn constructional unit) ሲሆን ይህም ለተራ መውሰድ ሂደት የሚያገለግሉ የአሃድ አይነቶችን (unit types) የሚቆጣጠር ነው።

ሁለተኛው የተራ አሰጣጥ አካል (turn allocation component) በተናጋሪዎች መካከል ያሉ የተራ ለውጦችን የሚቆጣጠር የንግግር ልውውጥ የሚጠበቅበትን መንገድ የሚያሳይ ነው (ሳክስ እና ሌሎች፣1974፣697)።

2.5.1. የተራ መገንቢያ አሃድ (turn constructional unit)

ተራዎች በርዝመት እና በስነልሳን ድር (linguistic texture) ሊለያዩ ከሚችሉ ተራ መገንቢያ አሃዶች የሚመሰረቱ ናቸው (ሽርማን፣1998)። በተጨማሪም ሳክስ እና ሌሎች (1974፣698) እንደሚሉት የተራ መገንቢያ አሃድ አረፍተነገራዊ፣ ሀረጋዊ እና ቃላዊ መገንቢያዎችን ሊወክሉ ይችላሉ። ይህም ማለት የተራ መገንቢያ አሃዶች አገባባዊ መዋቅር ውስጥ እንደ ሙሉ ሰዋስዋዊ አረፍተ ነገር ወይም እንደ ነጠላ ቃል ሊያገለግሉ ይችላሉ።

በተራ አሰጣጥ ሂደቱም በመጀመሪያ ተናጋሪው ለአንድ ጊዜ ተራ እንዲኖረው ስልጣን አለው። የዚህ ተራ ፍጻሜ ደግሞ ከተናጋሪነት ወደ አድማጭነት የሚተላለፍበት የመጀመሪያ የመሸገገሪያ ቦታ (initial transition relevance place) ወይም የተራ መገንቢያ ቦታ አለው (ሳክስ እና ሌሎች፣1974)። ሽርማን (1998) እንደሚገልጹት አብዛኛውን ጊዜ የንግግር ልውውጥ ሚዛናዊ አይደለም። ይህም ሚዛናዊ አለመሆን የሚያሳየው አንዱ ከሌላው በላይ እንደሚናገር ነው። አንዱ ለንግግሩ ረጅም ተራን ሲወስድ ሌላኛው በመድረኩ የሚናገርበትን እድል ይከለክላል። እሳቸው እንደሚሉት የንግግር ልውውጥ በበላይነት ተጽእኖ ማሳደርን ለመተግበር መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል። ሰልቲንግ (2000) የሳክስ (1974)ን ስራ በመመርመር የተራ መገንቢያ አሃድ ሙሉ ተራ ማለትም እንደ ብያኔው በስነልሳን አሃድ (linguistic unit) ሳይሆን በተራ መሸጋገሪያ ጠቃሚ ቦታ የሚያልቅበት ጠቃሚ በሆነ ተጽእኖ መለኪያ፣ በአገባብ እና እቅድ ላይ የተመሰረተ ነው። ማንኛውም ሙሉ ተራ (complet turn) የተራ መገንቢያ አሃድ ነው። ነገር ግን ማንኛውም የተራ መገንቢያ አሃድም ተራ ሊሆን ይችላል። ሰልቲንግ (2000) እንደሚሉት ጠቃሚ የተራ መሸጋገሪያ ቦታ በመናገር ላይ ባለው ተናጋሪ ሊረዝም ይችላል። ይህም ማለት የንግግር ልውውጥ አደረጃጀት ፈጣን ተናጋሪነትን እና ፈጣን አድማጭነትን አጣምሮ መያዝን ያካትታል። ምክንያቱም ድርርቦሽን ለማስወገድ እያንዳንዱ አድማጭ ጠቃሚ የሽግግር ቦታን መጠበቅ አለበት።

2.5.2. የተራ አሰጣጥ አካል (turn allocation component)

የተራ አሰጣጥ አካላት በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም ተረኛው ተናጋሪ የሚቀጥለውን የሚመርጥበት እና የሚቀጥለው ተናጋሪ ራሱን በመምረጥ ተራ የሚሰጥበት ነው። ለተራ መስጠት የተጻፈው ህግ የሚከተለውን ይመስላል (ሳክስ እና ሌሎች፣1974፣700)፡-

1ኛ. ተረኛው ተናጋሪ የሚቀጥለውን መምረጥ ይችላል።

2ኛ. ተረኛው ተናጋሪ የሚቀጥለውን ካልመረጠ ምናልባት ራሱን ሊመርጥ ይችላል። ነገር ግን ግዴታ መተግበር የለበትም።

3ኛ. ተረኛው ተናጋሪ የሚቀጥለውን ካልመረጠ ሌላውም ራሱን ካልመረጠ ተረኛው ተናጋሪ መቀጠል ይችላል፤ ነገር ግን ግዴታ አይደለም። የመጀመሪያውም ሆነ ሁለተኛው ህግ ሳይተገበር ቀርቶ ተረኛው ተናጋሪ ከቀጠለ የተጻፈው ህግ በሚቀጥለው የመሸጋገሪያ ቦታ ላይ በድጋሚ ይተገበር እና ሽግግር እስኪፈጸም ድረስ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል በተደጋጋሚ ይተገበራል (ሳክስ እና ሌሎች፣1974)።

እነዚህ ህጎች በአንድ ጊዜ አንድ ተናጋሪ መናገር እንዳለበት የሚያረጋግጡ ና መደራረቦች፣ መቆራረጦች እና ክፍተቶችን የሚያስወግዱ ናቸው። ነገር ግን ስቺፍሪን (1988) እንደሚሉት የተራ መቀያየር ህጎች ለአሁኑ እና ለሚቀጥለው ተረኛ መስተካከል አለባቸው። እሳቸው በጥናታቸው እንደዘገቡትም በቃላት እና በአረፍተ ነገሮች የመነሻ ቃላት ትርጉም ይዘት ላይ በመመስረት ተራዎች ቀደም ካሉ ተራዎች ተለይተው ይቀመጣሉ። ለምሳሌ፡- በ "ግን" የሚጀምሩ ተራዎች በ "ስለዚህ" እና በ "እና" ከሚጀምሩ ተራዎች በተሻለ መልኩ ትክክለኛ የመሸጋገሪያ ቦታ ላይ ሊከሰቱ አይችሉም።

2.5.3. የአርምሞ ጊዜ (silence time)

ሳክስ እና ሌሎች (1974፣) ሶስት የአርምሞ አይነቶችን ይለያሉ። እነሱም ዝንጋታ (Lapses)፣ ተግታ (Pauses)፣ እና ክፍተት (Gaps) ናቸው። እያንዳንዳቸውንም በማብራራት ሲገልጹ በተራ ውስጥ ዝምታ በሚከሰትበት ወቅት ምክንያቱ ጠቃሚ ቦታ ላይ አለመሆን ከሆነ እረፍት ይባላል። ክፍተት ደግሞ የሆነን ርዕሰ ጉዳይ ካጠናቀቁ በኋላ የሚፈጠር ዝምታ ነው። ዝንጋታ

ጠቃሚ የመሸጋገሪያ ቦታዎች ላይ የሚፈጠሩ ረጅም ዝምታዎች ናቸው ይላሉ። ተረኛው ተናጋሪ ራሱን በመምረጥ ክፍተቱን ወደ ተግታ በመለወጥ እና ጠቃሚ መሸጋገሪያ ቦታ ላይ የሚያልቅ ሌላ የተራ መገንቢያ አሃድ በመፍጠር ክፍተቶች ወደ ዝንጋታ እንዳይሸጋገሩ መከልከል ይቻላል። እነሱ እንደሚሉት አርምሞ እንደ ንግግር ሁሉ ጉልበት አለው። አጫጭር አርምሞዎች የማሰቢያ ጊዜ ተደርገው ሲወሰዱ ረጃጅም አርምሞዎች ደግሞ መልካም እና መጥፎ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበት ተደርገው ይወሰዳሉ።

2.5.4. የተራ መቋረጥ እና ድርርቦሽ (interruptions and overlaps)

የተራ መደራረብ ሲፈጠር አንዱ ተናጋሪ ያቋርጣል። ይህ ደግሞ የድርርቦሹን አካል ወይም ድርርቦሹን ያስወግዳል (ሳክስ እና ሌሎች፤1974፤706)። ስርዓትን ጠብቆ አንድ ለአንድ በሚደረግ ንግግር ላይ እንደ መቆራረጥ እና መደራረብ ያሉ ሁሉ እንዳላስፈላጊ እና እንደ ግጭት ምልክት ተደርገው ይታሰባሉ። ነገር ግን ኢድልስኪ (1981) እንደሚገልጹት በአንድ ላይ ንግግር ማድረግ ያለውን ባህርይ ሲገልጹ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በየራሳቸው ንግግር ሁሉም ተሳታፊዎች በነጻነት ሃሳባቸውን የሚያንጸባርቁበት ወይም በአንድ ላይ በመሆን አንድ ሃሳብ የሚገነቡበት ሊሆን ይችላል።

ተራን ጠብቆ የንግግር ልውውጥ በማድረግ ሂደት፣ ባለተራው ተናጋሪ ንግግሩን ገና ሳይጨርስ፣ በመናገር ላይ እያለ፣ ቀጣዩ ተሳታፊ ቸኩሎ ንግግር በመጀመሩ የተነሳ የንግግር ድርርቦሽ ይከሰታል። በሌላ በኩልም በተራ መውሰድ ወቅት ንግግሩ ሲጀምር እና ሲያልቅ ሁለት ተናጋሪዎች በአንድ ላይ መናገር የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ከሆኑ ድርርቦሹ ሊከሰት ይችላል (ሳክስ እና ሌሎች፤1974)።

በንግግር ወቅት ድርርቦሽ በብዙ መልኩ ሊከሰት እንደሚችል ከበደ ይመር (2000፤21) ኮሆነን (2004፤20-21)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው በዝርዝር ይገልጻሉ።

1. ተደርቦ በመጨረስ፣ ንግግሩን በመጨረስ ላይ ካለው ተናጋሪ ጋር ቀጣዩ ተናጋሪ በመጠኑ ደርቦ በመናገር ተራውን በሚጀምርበት መሸጋገሪያ ላይ ይከሰታል።
2. በዲስኩር ማጠናከሪያዎች አማካኝነት ይፈጠራል፤ የንግግሩን መቀጠል ለማመልከት ሲባል ተግባራዊ በሚሆኑ የኋልዮሽ ትውስታ አማካኝነት ድርርቦሽ ይኖራል።
3. በተሳታፊዎች መካከል ግንኙነት ለመመስረት እና ለማጠናከር ሲባል በሚከናወኑ አጫጭር ተመሳሳይ ቃላት(አዎን፣ትክክል) ድግግሞሾች የተነሳ ሊከሰት ይችላል።

4. ተደርቦ በመጀመር ወይም ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተናጋሪዎች ንግግሩን ለመጀመር አንድ ላይ በአንድ ጊዜ በሚናገሩበት ጊዜ ይፈጠራል፤ ነገር ግን ንግግሩን የሚቀጥለው ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ሰው ብቻ ነው።
5. በሳቅ፣ ግንኙነትን ለማጠናከር በሚደረግ ሳቅ ወይም ሳቅን በመጋራት ጊዜ ድርርቦሹ ይፈጠራል።
6. ክፍተትን በመሙላት፣ ተናጋሪው በመናገር ላይ እያለ በሚዘገይበት ጊዜ ክፍተቱን ለመሙላት በሚደረግ ንግግር ሳቢያ ይፈጠራል።
7. በመናገር ላይ ያለውን ተሳታፊ ድንገት በማቋረጥ ጣልቃ በሚገባ ተናጋሪ አማካኝነት ይፈጠራል።
8. በሽምገላ ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ሳቢያ ይፈጠራል፤ በሁለት ተሳታፊዎች መካከል በሚደረግ ክርክር ጣልቃ በመግባት ክርክሩን ለማስቆምና ርእሰ ጉዳዩን ለማስቀየር በሚያደርገው ጥረት ድርርቦሽ ይከሰታል።

ከዚህም የምንረዳው ድርርቦሹ የሚከሰትበት ስርጭት ሲታይም ከአንዱ ተራዊ ንግግር ወደ ሌላው ተራዊ ንግግር ከሚደረገው የመሸጋገሪያ ቦታ ከጊዜ አንጻር ቀርቦ ወይም ርቆ ሊሆን ይችላል። ይህም ሲባል ከአንዱ ተራዊ ንግግር ሽግግር ከሚደረግበት ቦታ አኳያ የመከሰቻ ቦታው ሲታይ፣ መሸጋገሪያውን ቀድሞ ወይም ተከትሎ፣ በቅርበት ወይም በርቀት የሚፈጠር መሆኑን ያሳያል።

2.5.5. ማስተካከያ (repair)

ከበደ ይመር (2000፣18) ዎንግ (2000:247)ን በመጥቀስ እንደሚገልጹት ማስተካከያ "በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ጊዜ በስህተት እርማት እና በስነልሳናዊ ስህተቶች ሳቢያ ለሚያጋጥሙ የተግባቦት ችግሮች በሚሰጥ ማብራሪያ ላይ የተወሰነ ነው" ። በንግግር ልውውጥ ሂደት የሚደረገው ግን ስህተትን በቀጥታ ለማረም አይደለም። በመናገር ወይም በማዳመጥ ወይም በመረዳት ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣ ተሳታፊዎች መፍትሄ የሚሰጡበት ነው ይላሉ።

ይህም ሲባል በሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ ሳያተኩር በንግግር ጊዜ ቃላት ቶሎ አለማግኘት ለምሳሌ ስም መርሳት፣ በሰሙት ወይም በተረዱት ነገር ላይ እርግጠኛ አለመሆንን፣

የይብራራልኝ እና የማረጋገጫ ጥያቄዎችን፣ወዘተ...ሁሉ የሚያካትት ነው። ተዋቃሪዎቹም የሚስተካከለው ነገር (የስህተቱ ምንጭ የሆነው አረፍተ ንግግር)፣ ለማስተካከያ ተነሳሶትና መፍትሄ/ማስተካከያ ናቸው (ከበደ ይመር፣2000፣18)።

ነገር ግን በአብዛኛው ልቆ የሚታየው ገጽታው የማስተካከያ ተነሳሶት አደረጃጀቱ ነው (ሼግሎፍ፣2007፣207)። በተጨማሪም ሼግሎፍ (2007፣207) እንደጠቀሱት የአደረጃጀት ስርዓቱን በተመለከተ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ።

1) ማስተካከያውን ያነሳው ማነው? (ተናጋሪው ራሱ ወይስ ሌሎች ተሳታፊዎች)

2) ማስተካከያው የተነሳው የት ላይ ነው? (ችግሩ ከተከሰተበት በምን ያህል ርቀት ወይም በየትኛው ተራዊ ንግግር) የሚሉት ናቸው ።

ማስተካከያን የመሻት ተነሳሶት የሚከሰተው በዚያው ችግሩ በተነሳበት፣ቀጥሎ በሚመጣው እና በሶስተኛው ተራዊ ንግግር ላይ ነው። ከነዚህ ከሶስቱ በተጨማሪም ሌላ በአራተኛው ተራዊ ንግግር ላይ አዲስ የመከሰቻ ቦታም አለ። ይህም "አራተኛው የማስተካከያ ተነሳሶት" ተብሎ የሚጠራ እንደሆነ ሼግሎፍ (2007) ይገልጻሉ።

ከበደ ይመር (2000፣19) ስኬግሎፍ እና ሌሎች (1977)ን እና ኦልራይት (1991)ን በመጥቀስ ማስተካከያ እንዲሰጥ ማን አነሳሳ? ማስተካከያውንስ ማን ሰጠ? የሚሉትን በተመለከተ ደግሞ የመስኩ ምሁራን የሚከተሉትን አራት የአደረጃጀት ስርዓቶችን እንደሚጠቁሙ ያስረዳሉ።

1. በራስ አነሳሽነት ማስተካከል (self initiated repair)፡- ተናጋሪው የራሱን ችግር በመገንዘብ፣ ራሱ ለችግሩ ማስተካከያ ይሰጣል።
2. በራስ አነሳሽነት በሌላ ሰው ሲስተካከል (self initiated other repair)፡- ተናጋሪው በንግግሩ ሂደት ችግር የገጠመው መሆኑን በመጠቆም የሌሎችን ማስተካከያ ይሻል። (ለምሳሌ፡-ስያሜ ቃላትን ብንረሳ)
3. በሌሎች አነሳሽነት የራስን ችግር ማስተካከል (other initiated self repair)፡- ተሳታፊዎች ችግር መከሰቱን ሲያመለክቱ በስህተቱ ላይ አስተያየት ሲሰጡ፣ ተናጋሪው ራሱ ማስተካከያ ያቀርባል።

4. ሌሎች አነሳስተው ሌሎች ያስተካክላሉ። (other initiated other repair)፡- ከተናጋሪው ውጭ ያሉ (ነገር ግን ንግግሩን የሚከታተሉ) ሰዎች ችግሩን በመረዳት ማስተካከያ ይሰጣሉ።

2.6. የተራ መውሰድ መርሆች (principles of turn taking)

የንግግር ልውውጥ ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች መግባባት በመፍጠር ተሳታፊዎቹ ቢያንስ ስለአንድ ርእሰ ጉዳይ የሚነጋገሩበት ነው። የንግግር ልውውጥ ከአንድ ቋንቋ ጽሁፍ የሚለየው (monologic texts) የሚለየው በተናጋሪው ፍጥነት (speakers-swift) ነው (ኮክትሩክ፣2012)። ሳክስ እና ሌሎች (1974) እንደሚገልጹት የሰዎች የንግግር ልውውጥ ወይም መስተጋብር ሲደመጥ ስርዓቱን የጠበቀ ተራ መውሰድ ማደራጀት መቻል አለመቻላቸውን ማወቅ ይቻላል። በዚህ መልኩ የተወሰኑ የንግግር ስርአቶችን መፍጠር እና መጠበቅ ይችላሉ። ስለ ስርአት ሲናገሩ ተናጋሪዎች ተራ መውሰድን የሚያደራጁበትን መንገድ ይገልጻሉ። በንግግር ልውውጥ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ በአንድ ጊዜ የንግግር መድረኩን ይቆጣጠራል፤ ንግግሩን የሚከታተሉትም የንግግር መድረኩን በየተራ ይቆጣጠሩታል። በክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ወቅት ትኩረት የሚሰጠው የንግግር ልውውጥ ስርአት ለመፍጠር ተናጋሪዎች የሚተገብሯቸው ደንቦች መመርመር እና ማግኘት ላይ ነው። ይህንን በተመለከተ ሳክስ እና ሌሎች በጽሁፋቸው ውስጥ ገልጸውታል። በንግግር ውስጥ የተራ መውሰድ ሞዴልም የተገኘው በዚህ ምርምር ሲሆን ይህም በዲስኩር ትንተና ውስጥ እስከዛሬ ደረጃውን የጠበቀ ሞዴል ተደርጎ ይወሰዳል (ኮክትሩክ፣2012)።

2.7. አለማቀፋዊ የተራ መውሰድ ህጎች

አለማቀፋዊ የተራ መውሰድ ህጎችን በተመለከተ ሳክስ እና ሌሎች እና ማኮል በስራቸው ውስጥ ህጎቹን በሁለት በመከፋፈል ተመልክተዋቸዋል። የሁለቱም ምሁራን ጽሁፍ እንደሚያመለክተው በህጎቹ መካከል ልዩነት አይታይበትም። ለምሳሌነትም የሁለቱም ምሁራን ህጎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. የሳክስ እና ሌሎች (1974) በጽሁፋቸው ህጎቹን በሁለት ከፍለው ተመልክተዋቸዋል። እነሱም፡-

አንደኛው እና ልንመለከተው የሚገባው እንዲህ የሚል ነው፤ ያለምንም ክፍተት ወይም መደራረብ ከአንዱ ወደ ሚቀጥለው የሚደረግ የተራ ሽግግር የተለመደ ነው። በተራ መውሰድ ወቅት ጥቂት ክፍተት እና ጥቂት መደራረብ አንድ ላይ በመሆን አብዛኛውን የሽግግር ድርሻ ይይዛሉ። ምሁራኑ ይህንኑ ህግ በማክበር የአሁን ተረኛ ተናጋሪ የሚቀጥለውን ተረኛ ተናጋሪ ወደ ጠቃሚ መሸጋገሪያ ቦታ ያቀርባል በማለት ተስፋ ያደርጋሉ። በዚህ መንገድ የአሁኑን ተናጋሪ የመጨረስ መብት ጥሰት ማስወገድ ይቻላል።

ሁለተኛው የዚህ ሞዴል ህግ በንግግር ወቅት የሚፈጠሩ ተራ መውሰዶችን ያደራጃል። ተናጋሪዎች ተራ የሚወስዱበትም ሶስት አማራጭ መንገዶች አሉ። እነሱም፦

ህግ1. ተረኛው/ዋ ተናጋሪ የመናገር መብቱን ከተሳታፊዎች ለአንዱ ይሰጣል። ለምሳሌ፦ ተናጋሪው/ዋ በቀላሉ እንዲናገር ሌሎቹ ተሳታፊዎች በመጠየቅ ወይም ጥያቄ በማንሳት

ህግ2. ተረኛ ተናጋሪው/ዋ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ከደረሰ በኋላ ተናጋሪው ለራሱ የመናገር መብት ይሰጣል።

ህግ3. ተረኛ ተናጋሪው/ዋ የሚቀጥለውን ተናጋሪ ካልመረጠ፤ ተናጋሪው ሌላ የተራ መገንቢያ አሃድ ሊፈጥር ይችላል ወይም ሳይናገር ሊቀር ይችላል። ተረኛው ተናጋሪ ተራውን የበለጠ ማስፋት ከፈለገ ሁለተኛው ህግ በስራ ላይ ይውላል። ማለትም ከ1-3 የተዘረዘሩት ህጎች በሚቀጥለው ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ የተናጋሪ መተካት እስኪፈጠር ድረስ በድጋሚ ይተገበራሉ (ሳክስ እና ሌሎች፤1974)።

2. ማኩል (ዓ.ም ያልተጠቀሰ) እንደሚገልጹት ተራ መውሰድ በተፈጥሮአዊ ንግግር ውስጥ በሚከተሉት ሁለት ህጎች ይመራል።

ለማንኛውም ተራ የመጀመሪያው ተራ መገንቢያ አሃድ በመጀመሪያ ጠቃሚ የመሸጋገሪያ ቦታ፦

- ሀ. ቀድሞ ሲተገበር የነበረው ተራ የአሁኑ ተረኛ የሚቀጥለውን ተረኛ በመምረጥ ሲፈጸም ከነበረ፤ የተመረጠው አካል የሚቀጥለውን የመናገር ተራ የመውሰድ መብት እና ግዴታ አለበት፤ ሌላ ማንም ሰው ይህንን መብት እና ግዴታ አይኖረውም፤ ሽግግር የሚፈጠረውም እዚህ ቦታ ላይ ነው።
- ለ. በመተግበር ላይ የነበረው ተራ የአሁኑ ተረኛ የሚቀጥለውን ተረኛ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ ለቀጣይ ተናጋሪነት ራሱን መምረጥ ይችላል። ነገር ግን

ግዴታ አይደለም፤ ቀድሞ የጀመረው የተራ መብት ስለሚያገኝ ሽግግር እዚህ ቦታ ላይ ይፈጠራል።

- ሐ. ሲተገበር የነበረው አካሄድ የአሁኑ ተረኛ የሚቀጥለውን ተረኛ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ ሌላ ተናጋሪም ራሱን ካልመረጠ፤ የአሁኑ ተናጋሪ የመቀጠል መብት አለው፤ ነገር ግን ግዴታ አይደለም።

በመጀመሪያው የተራ መገንቢያ አሃድ መሸጋገሪያ ቦታ ላይ 1ሀ እና 1ለ ካልተተገበረ እና የ1ሐ ህግ ከቀጠለ ከሀ-ሐ ያለው ህግ በሚቀጥለው የመሸጋገሪያ ቦታ ላይ ይተገበራል። እያንዳንዱ ህግም በሚቀጥለው የመሸጋገሪያ ቦታ ላይ ሽግግሩ ውጤታማ እስኪሆን ድረስ በተደጋጋሚ ይተገበራል።

እነዚህ የማኮል (ዓ.ም ያልተጠቀሰ) እና የሳክስ እና ሌሎች (1974) ስራዎች የዘረዘሯቸው ህጎች ክፍተት እና መደራረብን ለመቀነስ ይረዳሉ። እነዚህ ህጎች እንደ ንግግር ልውውጥ ሃብቶች በማገልገል የተናጋሪ ሽግግር በስኬት እንዲከናወን፣ በተናጋሪዎች መካከል መናበብ ኖሮ ሽግግር እንዲካሄድ እና በአንዱ ተናጋሪ ዝምታ ጊዜ ብቻ እንዲሆን ያደርጋል። የመጀመሪያው ተናጋሪ ተራውን ከመጨረሱ በፊት ሌላ ተናጋሪ አይናገርም። ስለዚህ ሽግግር ከአንዱ ተናጋሪ በኋላ ስለሚተገበር ህጎቹ ክፍተት እንዳይፈጠር እገዛ ያደርጋሉ።

2.8. የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህጎች

እንደ ሞርቴንሰን (2008፣19) አገላለጽ የሚከተሉት ህጎች በጥልቀት ከተገለበጡ እና በተደጋጋሚ ከተደመጡ ከመቅረጸ ድምጽ ወምስል የተገኙ ናቸው። እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚካሄዱ የተራ ንግግርን በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ናቸው።

1. ለማንኛውም የመምህር ተራ ፤የመጀመሪያ ተራ መገንቢያ አሃድ በመጀመሪያ የሽግግር ቦታ :-

ሀ. የመምህሩ ተራ የአሁኑ ተረኛ የሚቀጥለውን የመምረጥ ቴክኒክ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤ የመናገር መብት እና ግዴታ የሚሰጠው ለአንድ ተማሪ ነው። ማንም ሌላ ሰው የመናገር መብት እና ግዴታ የለውም፤ ስለዚህ ሽግግር የሚፈጠረውም በጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ ነው።

ለ. እስካሁን የነበረው የመምህሩ ተራ የአሁኑ ተናጋሪ የሚቀጥለውን በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ ተረኛው ተናጋሪ ወይም መምህሩ መቀጠል አለበት።

2. ከላይ የተጠቀሰው 1ሀ ከተተገበረ ወይም ስራ ላይ ከዋለ ፤ ለማንኛውም በዚህ መልኩ በተራ ለተመረጠ ተማሪ የመጀመሪያ ተራ መገንቢያ አሃድ በመጀመሪያ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ፡-

ሀ. እስካሁን የተመረጡት ተማሪዎች ተራ የወቅቱ ተረኛ የሚቀጥለውን በመምረጥ ሂደት ላይ የተመሰረተ ከሆነ፣ የመናገር መብት እና ግዴታ ለመምህሩ ይሰጣል፤ ከሱ ውጭ ማንም ይህን መብት እና ግዴታ አይኖረውም እናም ሽግግሩ በዚህ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ይከሰታል።

ለ. እስካሁን የተመረጡት ተራዎች የወቅቱ ተረኛ የሚቀጥለውን ተናጋሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ ራስን መምረጥ ሊተገበር ይችላል። ነገር ግን ግዴታ ስላልሆነ መምህሩ የንግግሩ ጀማሪ በመሆን ሽግግሩ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ እንዲከሰት ያደርጋል።

ሐ. እስካሁን የተመረጡት ተማሪዎች ተራ የሚቀጥለውን ተናጋሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ መምህሩ ራሱን ካልመረጠ ተረኛ ተነጋሪው ሊቀጥል ይችላል ነገር ግን ግዴታ አይደለም።

3. ለማንኛውም የመምህሩ ተራ የመጀመሪያ ተራ መገንቢያ አሃድ በመጀመሪያ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ 1ሀ ከተተገበረ ወይም 1ለ ከተተገበረ እና መምህሩ ከቀጠለ ከ1ሀ-1ለ የተዘረዘሩት ህጎች በሚቀጥለው ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ በድጋሚ ይተገበራሉ የሚቀጥለው ወደ ተማሪው ሽግግር እስኪደረግ ድረስ በእያንዳንዷ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ ይተገበራል::

4. ለማንኛውም የተማሪዎች ተራ የመጀመሪያ ተራ መገንቢያ አሃድ በመጀመሪያ ጠቃሚ የመሸጋገሪያ ቦታ 2ሀ እና 2ለ ካልተተገበሩ እና 2ሐ ከቀጠለ፤ የአሁኑ ተናጋሪ ከቀጠለ ከዚያ ከ2ሀ-2ሐ የተጻፉ ህጎች በሚቀጥለው ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ በድጋሚ ይተገበራሉ። እናም ወደ መምህሩ ሽግግር እስኪደረግ ድረስ በተደጋጋሚ በእያንዳንዱ ጠቃሚ የሽግግር ቦታ ላይ ይተገበራል (ሞርቴንሰን፤ 2008፣19)።

እዚህ ጋር መገንዘብ ያለብን እነዚህ ህጎች በክፍል ውስጥ የተማሪ እና መምህር መስተጋብር ውስጥ በግብዓትነት የሚኖሩ ከሆነ፣ ለዚህ መስተጋብር አንዱን አካል መምህሩን እንደ ሃላፊ

ለማስቀመጥ መሰረት ይኖረናል። ከ1-4 የተዘረዘሩት ህጎች ቢጣሱ ማለትም በአጠቃላይ ህግ ውስጥ ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ተናጋሪነትን መምራት የሚችሉት መምህራን ብቻ ናቸው።

ተማሪዎች ተናጋሪዎችን መምረጥ ይችላሉ ማለትም ንግግራቸውን ለመቀጠል ወይም መምህራናቸውን በመምረጥ ተራቸውን መስጠት ይችላሉ። የተማሪዎች ተራ መለዋወጥ ግን ላይከሰት ይችላል። መለዋወጥን ለሰዎች ክፍት በማድረግ እንደ ፈጠራዊ ስሜት አድርጎ መመልከት ይቻላል (ሞርቴንሰን፣ 2008)።

በአጭሩ ሞርቴንሰን (2008) እንደሚገልጹት ከላይ በተዘረዘሩት ህጎች መሰረት "የተለያዩ ተሳታፊዎች መብት በክፍል ውስጥ የሚሰራጨው የተሳታፊዎች ልዩነት፣ የጋራ መረዳት እና የመምህሩን ሙያዊ እውቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።"

2.9. ተራ መውሰድ በንግግር ልውውጥ ውስጥ

በተራ መውሰድ ላይ የተካሄደው የመጀመሪያ ጥናት እና ለሌሎች ተመራማሪዎች እንደ መሰረት ሆኖ ያገለገለው የሳክስ እና ሌሎች (1974) ስራ ነው። እነሱም በጥናታቸው ተናጋሪዎች የተራ መውሰድን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ አሳይተዋል። በተጨማሪም ስለ ተራ መውሰድ ሶስት መሰረታዊ እውነታዎችን ይጠቅሳሉ።

1. ተራ መውሰድ ይከሰታል።
2. በአንድ ጊዜ አንድ ተናጋሪ ብቻ ይናገራል እና
3. ተራዎች የሚወሰዱት በተቻለ መጠን በመሃከላቸው ባለ ትንሽ ክፍተት ወይም ድርርቦሽ ሊሆን ይችላል።

በእርግጥ በአንድ ጊዜ የሚናገሩ ከአንድ በላይ ተናጋሪዎች ሊኖሩ እና ብዙ ድርርቦሽ በንግግር ልውውጥ ጊዜ ሊኖር ይችላል (ሳክስ እና ሌሎች፣ 1974)።

እንደ ቫንላየር (1988) አገላለጽ ከሆነ በአጠቃላይ ተራ መውሰድ በውድድር እና በተነሳሽነት የሚመራ ነው። ምንም እንኳን በተራ መውሰድ ወቅት መምህሩ መድረኩን መቆጣጠር የሚሻ ቢሆንም በተቃራኒው ተማሪዎቹም መድረኩን ለመቆጣጠር እድል ሲሹ ይንጸባረቃል። በዚህም የተነሳ የአሁኑ ተናጋሪ መድረኩን ተቆጣጥሮ እድሉን ላለመልቀቅ የሚያደርገው ጥረት

የአድማጮችን ተራ ይቀንሰዋል። ምንም እንኳን ተረኛ ተናጋሪው ረጅም ጊዜ እንደሚፈጅ ቢያውቁም አድማጮች ተራ ለማግኘት የመጨረሻውን ሰአት በጉጉት ይጠባበቃሉ።

ሃችባይ እና ዎፊት (2002) እንደሚሉት "በንግግር ልውውጥ እያንዳንዱ ተናጋሪ በንግግሩ ፍትሃዊ የሆነ ወይም እኩል ድርሻ ሊሰጠው ይገባል"። በዚህ መሰረት የንግግር ልውውጥ ተሳታፊዎች ስርዓቱን የጠበቀ የተራ ልውውጥ ለመፍጠር ተባብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

እንደ ሳክስ እና ሌሎች (1974፣700-701) አገላለጽ ከሆነ በማንኛውም የንግግር ልውውጥ ውስጥ የሚከተሉትን እውነታዎች እንመለከታለን። እነሱም፡-

1. ተናጋሪ ይደጋገማል ወይም ይከሰታል።
2. በአብዛኛው በአንድ ጊዜ አንድ አካል ይናገራል።
3. በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ተናጋሪ ይናገራል ነገር ግን ለአጭር ጊዜ ነው።
4. ያለምንም ክፍተት ወይም ድርርቦሽ ከአንዱ ተራ ወደሚቀጥለው መሸጋገር ይኖራል።
5. የተራ ስርአት ወይም ቅደም ተከተል ቋሚ ስላልሆነ ይለዋወጣል።
6. የተራ መጠን ቋሚ አይደለም።
7. የንግግር ልውውጥ ርዝማኔ ቀድሞ አይገለጽም።
8. ተናጋሪዎች የሚሉት ቀድሞ አይገለጽም።
9. አንጻራዊ የተራ ስርጭት ቀድሞ አይወሰንም።
10. የተናጋሪዎች ብዛት ይለዋወጣል።
11. ንግግር ተከታታይ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል።
12. ተራ የመስጠት ዘዴ ይተገብራሉ። ተረኛ ተናጋሪ የሚከተለውን ሊመርጥ ይችላል (ለቀጣዩ ተናጋሪ ጥያቄ በማቅረብ)። ወይም ተናጋሪዎች ራሳቸውን ሊመርጡ ይችላሉ።
13. በርካታ የተራ መገንቢያ መለኪያዎች ይተገበራሉ።
14. የተራ መውሰድ ስህተት እና ጥሰት ሲኖር ጥገና ወይም እድሳት ይኖራል። ለምሳሌ ሁለት ተናጋሪዎች በአንድ ጊዜ እየተናገሩ ከሆነ አንዱ ንግግሩ ሳይበሰል ካቆመ የተፈጠረው ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ ያደርጋል።

2.10. የንግግር ልውውጥ ባህሪያት

ሳክስ እና ሌሎች (1974፣700) በንግግር ልውውጥ ሂደት የሚከተሉት ባህሪያት እንደሚከሰቱ በዝርዝር ያስረዳሉ።

1. ተራን ጠብቆ መናገር ቢያንስ አንድ ጊዜ ይቀየራል።
2. በአንድ ጊዜ ቢያንስ አንድ ሰው ብቻ ይናገራል።
3. ከአንድ በላይ ተናጋሪዎች በአንድ ጊዜ የሚናገሩበት አጋጣሚ ቢኖርም ጊዜው በጣም አጭር ነው።
4. ከ"ተራ" ወደ "ተራ" በሚደረግ ሽግግር (transition)፣ መጠነኛ የሆነ ድርርቦሽ(overlap)ና ክፍተት(gap) መከሰታቸው የተለመደ ባህሪ ቢሆንም ፣ያለነዚህ ተግባራትም ሽግግሩ ይተገበራል።
5. የ"ተራ"ው መጠኑም ሆነ ክትትሎሹ የተወሰነ አይደለም ።
6. "ተራ"ን አመልካች ስልቶች (ተረኛው ራሱን ሲመርጥ ወይም በተናጋሪው ሲመረጥ) በግልጽ ይተገበራሉ።
7. የተለያዩ "ተራ" ን መገንቢያ አሃዶች (ቃል፣ሀረግ፣አረፍተ ነገር) ይከሰታሉ።
8. "ተራ" ጠብቆ በመናገር ሂደት ማስተካከያ (ሁለቱም በአንድ ጊዜ አንድ ላይ መናገር በሚጀምሩበት አጋጣሚ)ይኖራል።

በተጨማሪም ሄሪቴጅ (1998፣5) "በተቋማዊ ንግግር ልውውጥ የሚደረጉት የተራ በተራ ንግግሮች፣ ምንም እንኳን ከመደበኛው የንግግር ልውውጥ ጋር በአብዛኛው ቢመሳሰሉም፣ የራሳቸው የሆነ የአደረጃጀት ስርአትም አላቸው" ይላሉ። ይህም ተሳታፊዎቹ ስለሚበዙና በስራ ድርሻቸው ስለሚለያዩ፣ የንግግር ልውውጡ አድማጮች ባሉበትና በመደበኛ ሁኔታ ስለሚደረግ እንደሆነ አክለው ያስረዳሉ።

ስለሆነም ተሳታፊዎቹ ሀሳባቸውን መግለጽ ይችሉ ዘንድ፣ በመናገር ላይ ያለው ተሳታፊ ተናግሮ ሲጨርስ፣ ቀጣዩ ተናጋሪ ንግግሩን የሚጀምርበትን ተራን በመውሰድ የመናገር መስተጋብራዊ የአደረጃጀት ስርአትን ይከተላል (ኩክ፣1989፤ሪቻርድስ፣1980)። ይህ የአደረጃጀት ስርአትም ተናጋሪ የነበረው አድማጭ፣ አድማጭ የነበረው ተናጋሪ በመሆን ተራ በተራ የንግግር መስተጋብሩን የሚያከናውኑ መሆናቸውን ያሳያል።

የንግግር ልውውጥ ትንተና ከዲስኩር ትንተና ጋር ያለውን ዝምድና ከበደ ይመር (2000) ታኔን (1982)ን በመጥቀስ ሲያስረዱ፤ የዲስኩር ትንተና የተጻፈንም ሆነ የተነገረ ቋንቋን ይይዛል። የተጻፈው በጽሁፋዊ ዲስኩር እንደ እሳቸው አገላለጽ በውህድ አሃድ ስር ሲካተት ፤ የተነገረው ደግሞ በንግግር ውስጥ ይጠቃለላል። የንግግር ልውውጥ ትንተናም በንግግር ውስጥ የሚካተት በመሆኑ አንዱ የዲስኩር ትንተና ክፍል ነው ይላሉ።

የመምህር ተማሪ የክፍል ውስጥ ዲስኩር ላይ ትንተና ማድረግ ስለመማር ማስተማር ክንውኑ ግንዛቤን ያስጨብጣል። የንግግር ልውውጡን ውቅሮች፣ ያተገባበር ስርአቱን፣ ትርጉምን ለመረዳት፣ የሚደረገውን ጥረት ለይቶ ለማመልከት ተማሪዎች የንግግር ክህሎታቸውን ማዳበር ይችሉ ዘንድ ተፈጥሮኣዊውን የንግግር ልውውጥ በመጠቀም በመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ይዘቶችን ለማካተት፣ መልመጃዎችን እና ስልተ ትግበራዎችን ለማዘጋጀት ያግዛል (ካኒንግስዎርዝ፣ 1987፤ ብራውን እና ዩል፣ 1983)።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የሚያተኩረው የተማሪዎች እና የመምህራን ዲስኩርን ከተራ መውሰድ አኳያ መመርመር ላይ ነው። ተራ መውሰድ ወይም የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና በባህሪው መተንተን ያለበት በአይነታዊ የጥናት ዘዴ ነው። ይህም ጥናቱን ገላጭ ስለሚያደርገው ጥናቱ የሚካሔደው በገላጭ የምርምር ዘዴ ነው።

3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱ የሚካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ስር በሚገኘው በአግዓዚያን ቁጥር 3 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ትምህርት ቤቱም የተመረጠው በአላማ ተኮር ናሙና (purposive sampling) ነው። ያለው እንዳወቀ (1998) እንደሚሉት ፦

> *ይህ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ነው። እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖራቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳታፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን አላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎችን ነገሮችን ይመርጣል።*

ስለዚህም አጥኚዋ ይህንን የናሙና ዘዴ የመረጠችው የሚፈለገውን መረጃ ለመስጠት ወይም በክፍል ውስጥ ለመቀረጽ ፍቃደኛ የሆኑ መምህራን በዚህ ትምህርት ቤት የሚገኙ በመሆናቸው ነው። ይህንንም ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት የኒውኤራ እና የቤተልሔም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን ባነጋገረችበት ወቅት የጽሁፍ መጠይቅ ለመሙላት እንጂ ለመቀረጽ ፍቃደኛ አይደለንም ባሏት መሰረት የአግዓዚያን ቁጥር 3 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መርጣለች። አጥኚዋ በስራ ላይ በነበረችበት ወቅት በዚሁ ትምህርት ቤት ታስተምር ስለነበር መምህራንም ጥናቱ እንዲካሄድባቸው በቀላሉ ፍቃደኛ ሆነው ተገኝተዋል።

በአግዓዚያን ቁ.3 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ። ነገር ግን የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአጠቃላይ ብሄራዊ ፈተና የሚዘጋጁበት ወቅት ስለሆነ ለጥናቱ አልተመረጡም። በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። በትምህርት ቤቱ 10 የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ይገኛሉ። የቅጅው ትርጓሜ እና ትንተና ጊዜ ስለሚፈጅ እና ለመቆጣጠርም አዳጋች ስለሚሆን ከአስሩ ምድቦች አንዱን ክፍል "9C"ን በእጣ

ለይታለች። በእጣ በተለየው ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በጥናቱ ተካተዋል። እንዲሁም በክፍሉ የሚያስተምሩት መምህርትም በአላማ ተኮር ናሙና በጥናቱ ተሳታፊነት ተካተዋል።

3.2. መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የንግግር ልውውጥ ትንተና የሚጠቀምበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መቅረጸ ምስል ወድምጽ ሲሆን፣ የሚመሰረተውም በተፈጥሮ በተከሰተው ንግግር ላይ ነው። መረጃውን ለመሰብሰብ በሁለት ባለሙያ እና በሁለት መቅረጸ ድምጽ ወምስል ለመቅረጽ ታስቦ የነበረ ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያ ብልሽት የተነሳ በአንድ ባለሙያ እና በአንድ መቅረጸ ድምጽ ወምስል ቀረጻው ተካሂዷል። ቀረጻውም ሲካሄድ የቀረጻ ባለሙያው ሙሉውን ክፍል ለማካተት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ቀረጻው የተካሄደው ለሶስት ቀናት ሲሆን፤ በአጠቃላይ ቀረጻው የፈጀው ጊዜም 90 ደቂቃ ነው። እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜም በአማካይ ለ30 ደቂቃ ቀረጻ ተካሂዶበታል።

3.3 በቀረጻ የተገኙ መረጃዎችን መተንተኛ ሞዴል

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመቅረጸ ድምጽ ወምስል የተገኙ መረጃዎች ተራ መውሰድን መሰረት በማድረግ ወደ ጽሁፍ በመቀየር ተተንትነዋል። ትንተናውንም ለማድረግ አጥኚዋ ሁለት ሞዴሎችን ተጠቅማለች። አንደኛው የተራ መውሰድ ህጎችን ለመተንተን የሳክስ እና ሌሎች (1974) ሞዴልን ተጠቅማለች። እነዚህም ምሁራን ተራ መውሰድ በንግግር ልውውጥ ውስጥ የሚል የመጀመሪያውን ሞዴል የፈጠሩ ሲሆኑ፣ ይህ ሞዴል የሚያተኩረውም በተፈጥሮ በተከሰተው ንግግር ላይ ነው። ስለዚህም ጥናቱ የሚያተኩረው በተፈጥሮ በተከሰተው ንግግር ላይ በመሆኑ አጥኚዋ ለጥናቱ ተስማሚ ሆኖ በማግኘቷ ይህንን ሞዴል ለጥናቱ ትንተና ተጠቅማለች። ሁለተኛው የተራ መውሰድ ውቅሮችን ለመተንተን የራይምስ (2008)ን ሞዴል በመጠቀም ተንትናለች። ይህም የተራ መውሰድ ውቅሮች በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከጥናቱ ጋር ስለሚስማማ ተመርጧል።

3.4. የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን

እንደ ከበደ ይመር (2000) አገላለጽ ንግግራዊ ዲስኩር ወዲያው ተሰምቶ ወዲያው የሚጠፋ መረጃ በመሆኑ ፣መረጃውን ደጋግሞ ለመስማትና ለማየት ያመች ዘንድ በመቅረጸ ድምጽ እና

በመቅረጸ ምስል አማካኝነት ቀርጾ ማቆየት ያስፈልጋል ። የሚቀረጸው መረጃም ተፈጥሮአዊ ይሆን ዘንድ የተሳታፊዎቹን ንግግር እንዳለ ቀርጻለች።

በቀጣዩ ሂደትም ቀረጻውን ወደ ጽሁፋዊ መረጃነት ቀይራለች። የንግግር ልውውጥን ወደ ጽሁፋዊ መረጃ መቀየር ሲባልም በድምጽ መልክ የተሰበሰበውን መረጃ ጽሁፋዊ ቅርጽ የማስያዝ ተግባርን ይመለከታል። በርግጥ ትክክለኛ መረጃው ወደ ጽሁፍ ቅርጽ ተቀይሮ የቀረበው ሳይሆን በድምጽ እና በምስል መልክ የተሰበሰበው ነው። ነገር ግን ወደ ጽሁፍ ቅርጽ የሚቀየረው፣ መረጃውን ለትንተና ለማመቻቸት ሲባል (የንግግር ልውውጡን ውቅሮች፣ አደረጃጀት፣ ተራን ጠብቆ መናገር፣ ወዘተ... በቀላሉ ለማየት ስለሚያስችል) ነው።

የመረጃ አተናተን ዘዴው አይነታዊ የትንተና ዘዴ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች የንግግር ልውውጡን እንዴት እንዳከናወኑት በተጠየቅ ለመግለጽ በጥሞና ማዳመጥን ስለሚጠይቅ የተራ አወሳሰዳቸውን መላልሳ በማዳመጥ፣ ወደ ጽሁፍ የተቀየረውን መረጃ መርምራለች። ወደ ጽሁፍ የተቀየረውንም መረጃ በመመርመር ተንትናለች።

ምእራፍ አራት

የመረጃ ውጤት ትንተና እና ትርጉማ

4.1. የተራዊ ንግግር ድግግሞሽ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የምንመለከተው በመምህርቷ እና በተማሪዎቹ መካከል ምን ያህል ተራዊ ንግግሮች እንደተካሄዱ ነው። ይህም የተራ አወሳሰድ መጠናቸውን እንድናነጻጽር ይረዳናል።

ሰንጠረዥ አንድ፡- የተራ አወሳሰድ መጠናዊ ንጽጽር በመምህርቷ እና በተማሪዎቿ መካከል

የጽሁፋዊ መረጃ መለያ ቁጥር	የተራዊ ንግግር ድግግሞሽ					
	መምህርት		ተማሪዎች		ድምር	
	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ
ቀ1	133	48.19	143	51.81	276	100
ቀ2	87	48.33	93	51.67	180	100
ቀ3	73	50.69	71	49.31	144	100
ድምር	293	48.8	307	51.25	600	100

ከሰንጠረዥ አንድ መገንዘብ እንደሚቻለው የተራ አወሳሰድ መጠን በተማሪዎች እና በመምህርቷ መካከል ልዩነት ይታይበታል። ይህም ከአጠቃላዩ 600 ተራዊ ንግግሮች ተማሪዎች 307(51.25%) ተራ ሲወስዱ መምህርቷ ደግሞ 293(48.8%) ጊዜ የመናገር ተራውን ወስደዋል። በመሆኑም በመምህርቷ እና በተማሪዎቹ መካካል ያለው የተራ አወሳሰድ ልዩነት ታይቶበታል። ከዚህም የምንረዳው ከመምህርቷ ይልቅ ተማሪዎች ብዙ የመናገር ተራ መውሰዳቸውን ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በመምህርቷ እና

በተማሪዎች መካከል ያለው የተራ አወሳሰድ ወጥነት አይታይበትም። ለምሳሌ የመምህርቷን ተራዊ ንግግር ብንመለከት ከመጀመሪያው ቀን እስከ ሶስተኛው ቀን ቀረጻ 133፣ 87፣73 በማለት ይሄዳል። ወደ ተማሪዎቹም ስንመጣ 143፣ 93፣71 በማለት ይለዋወጣል። ከዚህም በተጨማሪ በተከታታይ በተደረጉት ቀረጻዎች የተማሪዎቹም ሆነ የመምህርቷ ተራ መውሰድ መጠን 276፣ 180፣ 144 በመሆን እየቀነሰ መሄዱን እንረዳለን።

4.2. የተራ መውሰድ አካላት

በምዕራፍ ሁለት 2.6 እንደተገለጸው የተራ መውሰድ አካላት የሚባሉት ተራን መገንቢያ አሃድ፣ ተራን መምረጫ ስልት፣ መቋረጥ ወይም ድርርቦሽ፣ አርምሞ እና ማስተካከያ ናቸው። እያንዳንዳቸውም በመቀጠል እየተተነተኑ ይቀርባሉ።

4.2.1. ተራን መገንቢያ አሃዶች

የመናገር ተራ የደረሰው ተሳታፊ ንግግሩን ለማፍለቅ የተለያዩ የተራ መገንቢያ አሃዶችን ሊጠቀም ይችላል። እነዚህም የተራ መገንቢያ አሃዶች ከመዋቅር አንጻር ሲታዩ ዓረፍተ ነገራዊ፣ ቃላዊ እና ድምጻዊ ሊሆኑ ይችላሉ (ሳክስ እና ሌሎች 1974)። ከንግግር ልውውጡ የሚከተሉትን የመገንቢያ አሃዶች በመውሰድ እንፈትሻለን።

ሀ.ዓረፍተ ነገራዊ:- አረፍተ ነጋራዊ የተራ መገንቢያ አሃድ በየተራዊ ንግግሮቹ ወቅት ከአንዱ ተራ ወደ ሌላ ተራ በምንሸጋገርበት ወቅት የምንጠቀመው አረፍተ ነገርን ሲሆን ነው። ለዚህም ማስረጃ የሚከተሉትን ምሳሌዎች መመልከት እንችላለን።

ምሳሌ1 /ቀ1/.

256.መ/ት:- ሌላ ደግሞ ባርኔጣዎች

257.ሴተ:- ባርኔጣ ነዳ ጥገኛ ደግሞ -ዎች

258.መ/ት:- በጣም ጥሩ ጎበዞች አገሯ እስቲ ያልሞከረ ሰው ካስ

259.ሴተ:- አገር ነዳ ምእላድ ሲሆን---

260.መ/ት:- እ-

261.ሴተ:- ዋ ደግሞ ጥገኛ ምእላድ

262.መ/ት:- አገር ነዳ ምእላድ ዋ ድግሞ ጥገኛ ምእላድ

ከምሳሌ አንድ መመልከት እንደሚቻለው 258ኛው ተራዊ ንግግር ከአረፍተ ነገራዊ አሃድ የተገነባ ነው።

ምሳሌ 2/ቀ1/፡-

9. ተህ፡-_____
10. መ/ት፡- እሺ ተውኔት በየት ቦታ[ይታያል አልን]?
11. ተህ፡- [ቲያትር ቤት]
12. መ/ት፡- ተውኔት የራሱ የሆነ ቲያትር ቤት አለው። ድራማ እና ፊልም ብንመለከት በሬድዮ ወይም በቴሌቭዥን ይቀርባል። ተውኔት ግን የራሱ የሆነ ቦታ አለው ይህም ቲያትር ቤት ነው። እስቲ ከአዲስ አበባ ትያትር ቤቶች የሚነግረኝ
13. መ/ት ፡- እሺ እዚያጋ

ከምሳሌ ሁለት የምንረዳው ተራ ቁጥር 10 እና ተራ ቁጥር 12 ላይ የተጠቀሱት ተራዊ ንግግሮች የተገነቡት በዓረፍተ ነገራዊ መገንቢያ አሃድ መሆኑን ነው።

ለ.ቃላዊ፡- ከቃል የተገነባ ተራዊ ንግግር ለንግግር ልውውጡ መሸጋገሪያነት መዋሉን ያሳየናል።

ምሳሌ 3 /ቀ1/፡-

21. ወተ፡- መቼት
22. መ/ት፡-መቼት
23. ወተ፡- ታሪክ
24. መ/ት፡- ታሪክ
25. ሴተ፡- ትልም
26. መ/ት፡- ትልም
27. ወተ፡- ግጭት
28. መ/ት፡- ግጭት፣ተዋንያን ወይም ገጸባህሪያት የምንሳቸው ናቸው። እንግዲህ የዛሬው ትምህርታችን ደግሞ ሰዋስው ነው። ሰዋስው... ክዚያ ውስጥም ቅጥያዎች ናቸው። ገጽ109 አውጡ(2)

ከምሳሌው እንደምንረዳው ከተራ ቁጥር 21 እስከ 27 የሚገኙት ተራዊ ንግግሮች የተገነቡት ከቃላት መሆኑን ነው።

ምሳሌ 4 /ቀ1/፡-

165.ተህ፡- ባስቤት =ተሳቢ...
166.መ/ት፡- ቆይ እሺ እድል ሰጥቻሀ

167.ሴተ፡- ተሳቢ
168.መ/ት፡- ስምን ተሳቢ ላልሽ ወጣቱ ትውልድ ሀገር...
169.ሴተ፡- ወጣቱ ባስቤት ነው ትውልድ ደግሞ ተሳቢ ነው
170.መ/ት፡- እህ እሺ ሴላ የሚያስተካክል

በተጨማሪም ምሳሌ አራት ተራ ቁጥር 167 የተራ መገንቢያ አሃዱ ቃል መሆኑን ያመለክተናል።

ሐ. ድምጻዊ፡- ከቃል መሰል ድምጽ የተገነባ ተራዊ ንግግርን ይመለከታል።

ምሳሌ 5 /ቀ2/፡-

408.ተህ፡- ይህው ቲቸር
409.መ/ት፡-እ
410.ሴተ፡- ና
411.መ/ት፡- ና ነች ትቆምና የመጨረሻዋ ፊደል ና ነች ቀጥሎስ ደግሞ እሺ
412.ተህ፡- ቅ
413.መ/ት፡- ሳቅ ይሳል ቃሉ ቅ ን እንወስዳለን። ቀጥሎ የመጣውን ቅ አንወስድም ምክንያቱም በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርስ ቤት ነው እንጂ ቤት መምቻ ስለማይሆን ነው። ከዚያ ቀጥሎ

ከምሳሌ 5 የምንረዳው ተራ ቁጥር 409፣ 410 እና 412 የተገነቡት ከድምጻዊ መገንቢያ አሃድ መሆኑን ነው።

ምሳሌ 6 /ቀ3/፡-

574.መ/ት፡- እሺ ሴላ
575.ሴተ፡- ሰውኛ
576.መ/ት፡- እ
577.ወተ፡- ሰውኛ አለበት አሁን እዚጋ

ከቮፐን ትካዜ ከያሬድ ልቦና

መዓዛ የሞላብሽ የብስጭት ቃና

ብሎ

ንጹህ እንደ ጸሃይ ውብ እንደ ጨረቃ

ምስያ ይመስላል።

እንደዚሁም ምሳሌ 6 ተራ ቁጥር 576 የተገነባው ከድምጻዊ መገንቢያ አሃድ መሆኑን እንረዳለን።

ስለዚህ እነዚህ ምሳሌዎች "አንድ ተራዊ ንግግር ሲያንስ ከቃል መሰል ድምጽ ፣ ሲበዛ ደግሞ ከበርካታ አረፍተ ነገራዊ አሃዶች ሊገነባ ይችላል" የሚለውን የለርነር (1996)ን ግኝት የሚያረጋግጡ ናቸው።

ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት በቀረጻ ሁለት እና ሶስት ውስጥ ግን ከአረፍተ ነገር ውጭ ግጥሞችም የተራ መገንቢያ አሃድ በመሆን አገልግለዋል። ስለዚህ ይህ ጥናት እንደግኝት ያካተተው ግጥምን ነው። ለዚህ ግኝትም የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡-

ምሳሌ 7 /ቀ2/፡-

370.መ/ት፡- በጣም ጥሩ ሴሳ የሚያነብልን እሺ

371.ሴተ፡- ልጅቷ የዘመነችቷ

መስታዋቷን ---

372.መ/ት፡- መስተወቷን

373.ሴተ፡- ትልቋ መስታወቷ ፊት ትቆምና

ፊት ቆምና ሳቅ ግጥግ ሳቅ ግጥግ ሳብ

ደርሶ ፍልቅ ፍልቅልቅልቅ ከንፈር ግጥም

ደሞ ክፍት ደሞ ክፍት ደሞ ግጥምጥም

ወደ ኋላ ሂድት ሂድት ደሞም ምልስ ምልስልስ

ሽንጧን ሽንጧ ሰበር ቅልስ ቅልስልስ

ዳሌዋን ወዝ--ወዝ--@@@

374.ተህ፡- @@@-

375.መ/ት፡- @ቀጥይ ቀጥይ--@ ቂብቂብ ቁንቁን

በምሳሌ ሰባት ላይ እንደምንመለከተው 371ኛው እና 373ኛው ተራ የተገነባው ከግጥሞች፤ 372ኛው ከሀረግ ሲሆን 370ኛው እና 375ኛው ከአነሳሽ አረፍተ ነገር ነው። ከዚህም የምንረዳው ሰርነር (1996) ተራ መገንቢያ አሃዶች ናቸው ብለው ከዘረዘሯቸው ድምጻዊ፣ ቃላዊ እና ዓረፍተ ነገራዊ አሃዶች በተጨማሪም በዚህ ጥናት የተረጋገጠው ግጥም የተራ መገንቢያ አሃድ መሆኑን ነው።

በሚከተለው ሰንጠረዥ ደግሞ የተራ መገንቢያ አሃዶቹ በእያንዳንዱ መረጃ ውስጥ ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን እንመልከት፤

ሰንጠረዥ ሁለት፡- የተራ መገንቢያ አሃዶች ስርጭት

ተራን መገንቢያ አሃዶች	በእያንዳንዱ መረጃ ያላቸው የድግግሞሽ መጠን				
	ቀ1	ቀ2	ቀ3	ድምር	
				ቁጥር	መቶኛ
ቃል መሰል ድምጽ	9	13	2	24	4.32
ቃላዊ	69	41	32	142	25.54
ሀረጋዊ	55	46	21	122	21.94
አረፍተ ነገራዊ	98	63	73	234	42.09
ግጥማዊ	---	16	18	34	6.11
ድምር	231	179	146	556[1]	100

ከሰንጠረዥ ሁለት መመልከት እንደሚቻለው፤ የተራ መገንቢያ አሃዶች በእያንዳንዱ መረጃ ያላቸው ስርጭት የተለያየ ነው። ከጠቅላላው 556 ተራዊ ንግግሮች ውስጥ 234 (42.09) ያህሉ የተገነቡት ከአረፍተ ነገራዊ አሃድ ሲሆኑ 24 (4.32) ያህሉ ደግሞ ከቃል መሰል ድምጽ ነው።

[1] ይህ አጠቃላይ ተራዊ ንግግር በሰንጠረዥ አንድ ከተጠቀሰው ተራዊ ንግግር በመጠን ያነሰበት ምክንያት ተራውን የሚወስደው አካል ድምጽ የማይሰማ እና ምንም ምላሽ ሳይሰጥ በዝምታ የታለፈበት ከሆነ በተራ መገንቢያ አሃድ ውስጥ ልንመድበው ስለማንችል አይቆጠርም፤ ነገር ግን በመምህርቷ እና በተማሪዎች የተራዊ ንግግሮሽ ወቅት ተራውን የወሰደው ማን እንደሆነ ከታወቀ ስለሚቆጠር ነው።

ይህ ንጽጽራዊ ስሌት እንደሚጠቁመው አረፍተ ነገራዊ ተራን መገንቢያ አሃድ በሶስቱም መረጃዎች ያለው ስርጭት ሰፊ መሆኑን እና የቃል መሰል ድምጽ ተራን መገንቢያ አሃድ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ስለሆነም በመምህር ተማሪ የክፍል ውስጥ የንግግር መስተጋብር ተደጋግሞ የተከሰተው ተራን መገንቢያ አሃድ አረፍተ ነገራዊ ውቅር ሲሆን የድግግሞሽ መጠኑ አናሳ የነበረው ደግሞ የቃል መሰል ድምጽ ተራን መገንቢያ አሃድ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ይጠቁማል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም፣ በእያንዳንዱ ቀረጻ መረጃ ውስጥ ተራዊ ንግግሮቹ የተገነቡባቸውን ቃላት ብዛት በመቁጠር በመምህራን እና በተማሪዎች ተራዊ ንግግር መካካል ያለው የርዝመት መጠን እንደሚከተለው ተሰልቶ ለንጽጽር ቀርቧል።

ሰንጠረዥ ሶስት፡- የተራዊ ንግግር ርዝመት

የጽሁፋዊ መረጃ መለያ ቁጥር	የቃላት ብዛት በተራዊ ንግግር ውስጥ		
	መምህርት	ተማሪዎች	ድምር
ቀ1	1397	689	2086
ቀ2	1583	568	2151
ቀ3	1674	687	2361
ድምር	4654	1944	6598
መቶኛ	70.54	29.46	100

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በሶስቱም መረጃዎች መምህርቷ 4654 (70.54%) እና ተማሪዎች ደግሞ 1944 (29.46%) ቃላትን የያዙና በአረፍተ ነገራዊ አሃዶች የተገነቡ ተራዊ ንግግሮችን መጠቀማቸውን ነው። መጠናዊ ስሌቱ እንደሚያሳየውም መምህርቷ ከተማሪዎቹ ተራዊ ንግግሮች የረዛዘሙ ተራዎችን ተጠቅመዋል። ከዚህም በመነሳት መምህራን በተራ አወሳሰድ ረገድ ረጅም ጊዜን ይጠቀማሉ ማለት ይቻላል።

4.2.2 ባለተራን መምረጫ ስልቶች

የንግግር ልውውጥ ተሳታፊዎች ቀጣዩን ተናጋሪ በሁለት መንገዶች ሊመረጡ ይችላሉ። በምዕራፍ ሁለት 2.6.2 እንደተገለጸው አንድም እየተናገረ ያለው ተሳታፊ ቀጣዩን ተናጋሪ ሊመርጥ ይችላል፤ አለበለዚያም ቀጣዩ ተሳታፊ ራሱን በተናጋሪነት በመምረጥ ንግግሩን ይጀምራል። እነዚህን ስልቶች በሚከተለው ምሳሌ እንመልከት፡-

ምሳሌ 8 /ቀ1/፡-

2. መ/ት፡- እሺ... እሺ ተማሪዎች የ...ባለፈው ትምህርታችን ስለምን ነበር?
3. ወ፡- ስለ ተውኔት
4. መ/ት፡- እጅ በማውጣት! እሺ እህቴ
5. ሴ፡- ስለ ተውኔት
6. መ/ት፡- ተውኔት፣ተውኔት ምንድነው አልን?
7. ወ፡- የስነጽሁፍ ዘርፍ
8. መ/ት፡- እሺ ሴላ ተጨማሪ
9. ተ፡-_____
10. መ/ት፡- እሺ ተውኔት በየት ቦታ[ይታያል አልን]?
11. ተ፡- [ቲያትር ቤት]

ከላይ የተጠቀሱትን ተራዊ ንግግሮች ስንመለከት እየተናገረ ያለው ተሳታፊ ቀጣዩን ተናጋሪ ሊመርጥ ይችላል፤ የሚለውን የተራ መምረጫ ስልት የሚያሟላ ነው። ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው መምህርቷ ለተማሪዎች እንዲናገሩ እድል በሚሰጡበት ጊዜ ተራ ይወስዳሉ እንጂ ራሳቸውን በተናጋሪነት በመምረጥ ተራ አይወስዱም። ይህ የተራ መምረጫ ስልትም በምሳሌ 8 ላይ እና በአብዛኛው መረጃ ውስጥ የተከሰተው መምህርቷ በሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ አማካኝነት ነው። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከላይ ከተጠቀሰው የመምረጫ ስልት በተጨማሪ ተሳታፊዎች ራሳቸውን በመምረጥ ንግግር የሚጀምሩበትም ሁኔታ ይስተዋላል። ለአብነት ያህልም የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡-

ምሳሌ 9 /ቀ1/፡-

241.መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ ስሙ የሚለው እሺ ሃቢብ=
242.ወ፡- ስሙ ነዳ ምእሳድ
243.መ፡- ስሙ...
244.ተ፡- አይደለም
245.ወ፡- [ስም እና -ሹ]
246.ተ፡- [ስም እና -ሹ]
247.መ/ት፡- ስም እና ሹ በጣም ጥሩ በእናትህ

ከምሳሌ ዘጠኝ መረዳት የሚቻለው ከተራ ቁጥር 244 እስከ ተራ ቁጥር 246 ድረስ ያሉት ተራዊ ንግግሮች ተማሪዎች ራሳቸውን በተናጋሪነት በመምረጥ ተራ የወሰዱበት ሂደት መኖሩን ነው። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የተረጋገጠው በማስተማር ሂደቱ የተካሄዱ ተራዊ ንግግሮች ሁለቱንም የባለ ተራ መምረጫ ስልቶች በተግባር ላይ ማዋላቸውን ነው።

4.2.3 ማስተካከያን መሻት

በምዕራፍ ሁለት 2.6.5 ምሁራንን ዋቢ በማድረግ ለመግለጽ እንደተሞከረው ማስተካከያን መሻት ተሳታፊዎች በመናገር፣ በማዳመጥ እና በመረዳት ረገድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች፣ መፍትሄ የሚሰጡበት ነው። በመማሪያ ክፍል ተራዊ ንግግርም ይህ ስልት ለዚሁ ተግባር ሲከናወን ተስተውሏል።

ምሳሌ 10 /ቀ1/፡-

30. መ/ት፡- ቅጥያዎች ማለት ምን ማለት ነው?
31. ሴ፡- በአረፍተ ነገር መጀመሪያ እና መጨረሻ የሚገባ
32. መ/ት፡- በአረፍተ ነገር?
33. ሴ፡- [በሀረግ]
34. ተ፡- [በሀረግ]
35. መ/ት፡- እሷን የሚያስተካክል

ከምሳሌ አስር መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዋ በ31ኛው ተራዊ ንግግሯ ለፈጠረችው ስህተት በመምህርቷ አነሳሽነት በ32ኛው ተራዊ ንግግር የማረጋገጫ ጥያቄ ተጠይቃለች። በዚህም ሰዓት ተማሪዋ መሳሳቷን በማወቅ ትክክለኛ ምላሽ የመስላትን መልሳለች። በምትመልስበትም ወቅት

የክፍሉ ተማሪዎች በ34ኛው ተራ ቁጥር ከሷ ጋራ በመደረብ ተመሳሳይ መልስ መልሰዋል። ይሁን እንጂ በድጋሚም የተሰጠው ምላሽ ትክክል ባለመሆኑ የተነሳ መምህርቷ ለሌላ ተማሪ በተራ ቁጥር 35 እንዲያስተካክሏት እድል ሰጥተዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማስተካከያው እንዲሰጥ ማን አነሳሳ ማስተካከያውንስ ማን ሰጠ የሚሉትን ጥያቄዎች በተመለከተም በጥናቱ ውስጥ የተገኙት ግኝቶች ትንተና ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል።

ሀ. በራስ አነሳሽነት የሚደረግ ማስተካከያ

በራስ አነሳሽነት የሚደረግ ማስተካከያ ማለት በተራዊ ንግግር ወቅት በመናገር ላይ ያለው ሰው በንግግሩ ላይ ችግር እንደተፈጠረ ሲረዳ ችግሩ ከተከሰተበት ተራዊ ንግግር ሳይርቅ ወዲያውኑ በራሱ ተነሳሽነት ማስተካከያ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው።

ምሳሌ 11 /ቀ1/፦

185.መ/ት፦ መጫወት ነው የሚሆነው። መንቀፍ በሚለው እስቲ ሞክሪ እሺ እ

186.ሴተ፦ አባትየው ጥሩ ስራ ስላልሰራ ስልጁ ነቀፈው ማለቴ ልጁን ነቀፈው።

187.መ/ት፦ ልጁን ነቀፈው። ስለዚህ ባለቤት ማነው አባትየው የተነቀፈው ልጅየው ነው። ማህበር በሚለው እሺ

ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው በተራ ቁጥር 186 ላይ በመናገር ላይ የነበረችው ተማሪ በንግግሯ ወቅት የተፈጠረ ችግር መኖሩን አውቃ በራሷ ተነሳሽነት ማስተካከያ መውሰዷን ነው።

ለ. በሌሎች አነሳሽነት በራስ የሚደረግ ማስተካከያ

በተራ መውሰድ ወቅት በመናገር ላይ ያለው ሰው በንግግሩ ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ችግር ያለበት መሆኑን ተገንዝቦው በሚያደርጉለት ማነሳሻ ሳቢያ በተፈጠረው ችግር ላይ ራሱ ማስተካከያ የሚሰጥበት ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፤

ምሳሌ 12 /ቀ1/፦

192.መ/ት፦ ባለቤቱ ማነው ኢትዮጵያ ነች እደደል- እሺ ልማቱ [ተሳቢ] ሆነ ማለት ነው። እሺ ስነምግባር በሚለው

193.ተህ፦ [ተሳቢ]

194.መ/ት፦ እሺ እንየው

195.ወተ፡- አንተነህ

196.መ/ት፡- እሺ አንተነህ ሶሪ

197.ወተ፡- በስነዜጋ ትምህርት ውስጥ ስነ ምግባር እንማራለን፡፡

198.መ/ት፡- በስነዜጋ አይደለም፡፡ ከምንማራቸው ትምህርቶች አንዱ ስነዜጋ እና ስነ ምግባር ነው፡፡

ከላይ በቀረበው ምሳሌ በተራዊ ንግግር ወቅት መምህርቷ በ194ኛው ተራ ቁጥር የተማሪውን ስም አሳስተው በመጥራታቸው ተማሪው በተራ ቁጥር 195 ስሙ አንተነህ መሆኑን በመንገር አስተካክሏቸዋል፡፡ እሳቸውም ማስተካከያውን በመቀበል ይቅርታን ጠይቀውታል፡፡ በመቀጠልም አንተነህ የሰጠው ምሳሌ ስህተት መሆኑን ነግረው ለችግሩም መፍትሄ የሚሆነውን ትክክለኛ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በሌሎች አነሳሽነት በራስ የሚደረግ ማስተካከያን ነው፡፡

ምሳሌ 13 /ቀ1/፡-

219.መ/ት አሁን ይህንን ክፍፍል ተመርኩዞ ምእላድ በስንት ይከፈላል

220.ተህ፡- በሁስት

221.ወተ፡- ምእላድ እና ነጻ ምእላድ

222.ተህ፡- አይደለም@@@

223.መ/ት፡- እንደገና

224.ወተ፡- ነጻ ምእላድ እና ጥገኛ ምእላድ

225.መ/ት፡- በጣም ጥሩ አክመል! እሺ እስቲ የቤቶችን ነጻ እና ጥገኛ ምእላድ ንገሩኝ

በምሳሌ 13 ላይ እንደምንመለከተው ተማሪው በ221ኛው ተራ ወቅት ስህተት ፈጽሟል መሳሳቱንም የክፍል ጓደኞቹ በህብረት በመሆን በሳቅ በታጀበ ንግግር ነግረውታል መምህርቷም እንደገና እንዲናገር እድል በመስጠታቸው የተነሳ በ224ኛው ተራ ቁጥር ላይ ስህተቱን በራሱ በማስተካከል ትክክለኛውን ምላሽ ተናግሯል፡፡ ስለዚህ ይህንን ምሳሌ በሌሎች አነሳሽነት በራስ የሚደረግ ማስተካከያ ስር ልንመድበው እንችላለን፡፡

ምሳሌ 14 /ቀ1/፡-

243.መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ ስሙ የሚስሙ እሺ ሃቢብ=

244.ወተ፡- ስሙ ነጻ ምእላድ

245.መ/ት፡- ስሙ...

246.ተህ፡- አይደለም

247.ወተ፡- [ስም እና -ሉ]

248.ተህ፡- [ስም እና -ሉ]

249.መ/ት፡- ስም እና ሉ በጣም ጥሩ በእናትህ

በተመሳሳይ መልኩ ምሳሌ 14 ላይ የሚገኘው ተራዊ ንግግር ከላይ ከተሰጡት ምሳሌዎች የሚለየው መሳሳቱን የሚነግሩት የክፍል ጓደኞቹ ሆነው እያለ መሳሳቱን ከነገሩት በኋላ በሚያስተካክልበት ወቅት የክፍል ጓደኞቹም በ248ኛው ተራ ላይ እንደሚታየው ከእሱ ጋር በመሆን በመመለሳቸው ነው። ይህም ከሁሉም ማስተካከያዎች ምድብ የማይካተት እና በዚህ ጥናት እንደግኝት የሚታይ ነው።

ሐ. በሌሎች አነሳሽነት በሌሎች የሚደረግ ማስተካከያ

ከተናጋሪው ውጭ ያሉት ተሳታፊዎች በተራ መውሰድ ወቅት የተከሰተውን ችግር በመረዳት ራሳቸው ለመፍትሄው አነሳስተው መልሰው ማስተካከያውን የሚሰጡበት ስልት ነው። ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት

ምሳሌ15 /ቀ1/፡-

134. መ/ት፡- ስለዚህ እየ- የምትሰሙ መነሻ ቅጥያ ነች ማለት ነው። በጣም ጥሩ በ- ነው የሚቀረን በበ- ደግሞ የሚሰራ

135.ወተ፡- በግ

136.ተህ፡- @@@

137.መ/ት፡- በግ ቃል ነው እሺ ሴላ

ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው መምህርቷ ተማሪዎችን በ- በምትባለው መነሻ ቅጥያ ቃል እንዲመሰርቱ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን በ135ኛው ተራ ቁጥር ላይ ተራ የተሰጠው ተማሪ የመለሰው ምላሽ ትክክል አለመሆኑን የክፍሉ ተማሪዎች በመሳቅ ገልጸውለታል። በመጨረሻም መምህርቷ በ137ኛው ተራ ላይ ማስተካከያ ሰጥተውታል። ከዚህም የምንረዳው ከተናጋሪው ውጭ ያሉ ተሳታፊዎች (መምህርቷ እና ተማሪዎች) ለመፍትሄ አነሳስተው ማስተካከያውን መስጠታቸውን ነው።

ምሳሌ 16 /ቀ1/፡-

149.መ/ት፡- አዎ በጣም ጥሩ ቃላቶች አሉበት ፤ሀረጎች አሉበት ተጨማሪ ደግሞ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ ተጨማሪ ሴሳ የምትሉት አለ ...,...አረፍተ ነገር በስንት ይመደባል አረፍተ ነገር ውስጥ ምን ዋና ነገሮችን እናገኛለን? እሺ

150.ሴተ፡- ባለቤት

151.መ/ት፡- እሺ ባለቤት እኔ

152.ሴተ፡- ሀረግ

153.መ/ት፡- ሀረግ አይደለም፡፡ ሴሳ ተጨማሪ ..,... ለምሳሌ በሀረግ ደረጃ አረፍተነገርን ስንመለከት ትክክል ናችሁ፡፡ መነሻ እና መድረሻ ሀረግ አለ፡፡ ይሄ ስምን እና ተሳቢን የሚይዘው ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ግስን የሚይዘው ነው፡፡ ነገር አረፍተ ነገር በመዋቅሩ ሶስት ነገር ይይዛል መጀመሪያ አሁን ትብለጽ ያለችው ባለቤት ሲደመር ተሳቢ መጨረሻ.... [ግስ]

ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው ተራው የተሰጣት ተማሪ በ152ኛው ተራ ቁጥር ላይ ምላሽ የሰጠች ሲሆን በ153ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷም ምላሽዋ የተሳሳተ መሆኑን ራሳቸው በመግለጽ ማስተካከያ መስጠታቸውን ነው፡፡

መ. በራስ አነሳሽነት በሌሎች የሚደረግ ማስተካከያ

ይህኛው የማስተካከያ አይነት ተናጋሪው በንግግሩ ሂደት ችግር የገጠመው መሆኑን በመጠቆም ሌሎች ተሳታፊዎች እንዲያስተካክሉት ያነሳሳል፡፡ተሳታፊዎችም ችግሩን ተረድተው ማስተካከያውን በመስጠት ትብብራቸውን ይገልጻሉ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን በተመለከተ በመረጃው ውስጥ የተገኘ አንድም ማስተካከያ የለም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት የተገኘው ግኝት የሚጠቁመው በተራ መውሰድ ወቅት ከሚደረጉ ማስተካከያዎች ውስጥ ሶስቱ ብቻ ተግባራዊ መሆናቸውን ነው፡፡

4.2.4 ድርርቦሽ

በንግግር ልውውጥ ወቅት ድርርቦሽ በብዙ መልኩ ሊከሰት እንደሚችል በምዕራፍ ሁለት 2.6.4 ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በጥናቱ ውስጥ የተከሰቱ መደራረቦችም በዚህ ክፍል ይተነተናሉ፡፡

ተራን ጠብቆ የንግግር ልውውጥ በማድረግ ሂደት፣ ባለተራው ተናጋሪ ንግግሩን ገና ሳይጨርስ፣ በመናገር ላይ እያለ፣ ቀጣዩ ተሳታፊ ወዲያውኑ ንግግር በመጀመሩ የተነሳ የንግግር ድርርቦሽ ይከሰታል። በሌላ በኩልም በተራ መውሰድ ወቅት ንግግሩ ሲጀምር እና ሲያልቅ ሁለት ተናጋሪዎች በአንድ ላይ መናገር የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ከሆኑ ድርርቦሹ ሊከሰት ይችላል (ሳክስ እና ሌሎች፣ 1974)።

ሀ. ተደርቦ በመጀመር

ተደርቦ በመጀመር የሚከሰት ድርርቦሽ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተናጋሪዎች ንግግሩን ለመጀመር አንድ ላይ በአንድ ጊዜ በሚናገሩበት ጊዜ ይፈጠራል፤ ነገር ግን ንግግሩን የሚቀጥለው ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ሰው ብቻ ነው።

ምሳሌ 17 /ቀ1/፦

87. መ/ት፦ /በሶስት አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ/ በጣም ጥሩ መደቦች ሶስት ናቸው። አንደኛ መደብ ስለ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ፤ አንደኛ መደብ እስቲ እነማናቸው?
88. ሴተ፦ [እኔ] እና እሱ
89. ወተ፦ [እኔ]
90. መ/ት፦ ነጠላ ቁጥር ሲሆን እኔ ብዙ ቁጥር ሲሆን

ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው መምህርቷ አንደኛ መደብ የሚባሉት እነማን እንደሆኑ እንድትናገር እድል የሰጧት ተማሪ በ88ኛው ተራ ቁጥር ንግግር በምትጀምርበት ወቅት በ89ኛው ተራ ቁጥር አንድ ወንድ ተማሪ ተደርቦ መልሷል። ይህም ተደርቦ በመጀመር ለሚከሰት ድርርቦሽ ማሳያ ነው።

ምሳሌ18 /ቀ2/፦

439. መ/ት፦ መነሳትሽ ነው
440. ተህ፦ ይሀው ቲቸር
441. ሴተ፦ [ማስት]
442. ተህ፦ [ማስት]
443. መ/ት፦ የሚያስተካክሳት እሺ እህቴ

ከዚህ ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው መምህርቷ ለ441ኛው ተራ ቁጥር ተናጋሪ እድል የሰጧት ሲሆን ተማሪዋ ንግግሯን ለመመለስ በምትጀምርበት ቅጽበት በ442ኛው ተራ ቁጥር ተማሪዎቹ በህብረት በመሆን በመደረብ መልሰዋል። በመቀጠልም መምህርቷ በ443ኛው ተራ ቁጥር እድል የሰጧት ተማሪ ብቻ መሳሳቷን በመውሰድ ሌላ የሚያስተካክላት ተማሪ በመፈለግ እድል ይሰጣሉ። ይህም የሚየሳየን የተሳሳተው ሙሉ ክፍሉ ቢሆንም እሳቸው ግን ምንጊዜም መቀጠል ያለበት አንድ ተማሪ መሆኑን በማመን እድሉን ለሌላ ሴት ተማሪ መስጠታቸውን ነው።

ለ. ተደርቦ በመጨረስ

ተደርቦ በመጨረስ የሚከሰት ድርርቦሽ ንግግሩን በመጨረስ ላይ ካለው ተናጋሪ ጋር ቀጣዩ ተናጋሪ ደርቦ በመናገር ተራውን የሚጀምርበት ነው።

ምሳሌ 19 /ቀ1/፦

64. መ/ት፦ ሰው ሰዎች ፤ነገሮችስ? ጠረጴዛ [ጠረጴዛዎች]፤ ወንበር [ወንበሮች]

65. ተህ፦ [ጠረጴዛዎች]፤ [ወንበሮች]

ከምሳሌው መገንዘብ የሚቻለው በ64ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷ ንግግራቸውን በመጨረስ ላይ እያሉ ተማሪዎቹ በህብረት በመሆን ተደርበው ንግግር መጀመራቸውን ነው። በተጨማሪም የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፦

ምሳሌ 20 /ቀ1/ ፦

178.መ/ት፦ እሺ ግንባታው ምንድነው የሚሆነው [ተሳቢ]

179.ተህ፦ [ተሳቢ]

180.መ/ት፦ እሺ የእጅ ካስ ባስቤት ወይም ተሳቢ በማድረግ ስሩ

በተራ ቁጥር 178 መምህርቷ ንግግራቸውን ሲጨርሱ በ179ኛው ተራ ቁጥር ተማሪዎቹ በሙሉ በመደረብ ንግግር ይጀምራሉ። ይህም የሚያሳን ተደርቦ በመጨረስ ወቅት የሚከሰት ድርርቦሽ መሆኑን ነው።

ሐ. የዲስኩር ማጠናከሪያ

በዲስኩር ማጠናከሪያዎች አማካኝነት የሚፈጠር ድርርቦሽ የንግግሩን መቀጠል ለማመልከት ሲባል ተግባራዊ በሚሆኑ የኋልዮሽ ትውስታ አማካኝነት የሚፈጠር ነው።

ምሳሌ 21 /ቀ1/፡-

108.መ/ት፡- በነጠላ ከሆነ እሱ እና እሷ በብዙ ከሆነ እ...

109.ተህ፡- [እነሱ]

110.መ/ት፡- [እነሱ] እንደገና ነጠላን ስንመለከት ጾታን ያመለክታል። እኔ የወል ነው፤እኛም የወል ነው አንተስ?

ከምሳሌ 21 መረዳት እንደምንችለው በ108ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷ ንግግራቸውን ለመቀጠል የራሳቸውን ምላሽ ለማስታወስ በሚሞክሩበት ወቅት ተማሪዎቹ በህብረት በ109ኛው ተራ ቁጥር ምላሽ ሰጥተዋቸዋል ወይም አስታውሰዋቸዋል። ይህ በሚሆንበት ጊዜም መምህርቷ በተማሪዎቹ ምላሽ ላይ በመደረብ ተራዊ ንግግር አድርገዋል። ከዚህም የምንረዳው በዲስኩር ማጠናከሪያ አማካኝነት የሚፈጠር ድርርቦሽ በኋልዮሽ ትውስታ አማካኝነት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት 2.6.4 እንደተገለጸው የተከሰተ መሆኑን ነው።

መ. ክፍተትን መሙላት

ተናጋሪው በመናገር ላይ እያለ በሚዘገይበት ጊዜ ክፍተቱን ለመሙላት በሚደረግ ንግግር ሳቢያ እና በመናገር ላይ ያለውን ተሳታፊ ድንገት በማቋረጥ ጣልቃ በሚገባ ተናጋሪ አማካኝነት ድርርቦሽ ይፈጠራል።

ምሳሌ 22 /ቀ1/፡-

108.መ/ት፡- እኛ እንደገና በሁለት ይከፈላሉ ነጠላ እና ብዙ ነው። የነጠላ ቁጥር አመልካች እናንተ እንዳሳችሁት እኔ ነው። ብዛትን አመልካች ደግሞ..,... [እኛ]

109. ተህ፡- [እነሱ]

ይህ ምሳሌ የሚያሳየን መምህርቷ በ108ኛው ተራ ቁጥር ላይ በመናገር ላይ እያሉ መዘግየታቸውን ነው። በዚህም ሰዓት ተማሪዎቹ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት የመሰላቸውን ምላሽ በ109ኛው ተራ ቁጥር ላይ በመናገር ላይ እያሉ ድርርቦሽ መከሰቱን ነው። ይህንንም ድርርቦሽ ክፍተትን ለመሙላት በሚደረግ ንግግር ሳቢያ የተከሰተ ድርርቦሽ እንለዋለን።

4.3 በተራ መውሰድ ወቅት ተደጋግመው የተከሰቱ ውቅሮች

በተዛማጅ ጽሁፍ ምዕራፍ 2.5 እንደተጠቀሰው በመምህር መራሽ ክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ውቅሮች ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ እና ማነሳሳት-ምላሽ-ምጋቤ ምላሽ ናቸው (ራይምስ፣2008) ። በእነዚህ የተራ መውሰድ ውቅሮች ላይ በመመስረትም ትንተናው እንደሚከተለው ቀርቧል።

4.3.1.ማነሳሳት- ምላሽ- ግምገማ

ማነሳሳት- ምላሽ- ግምገማ የምንለው መምህራን ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ የመሳላቸውን እንዲመልሱ የሚያደርጉበትን ሂደት ነው። በመጨረሻም ተማሪዎች ለሰጡት ምላሽ የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም ተማሪዎችን የሚያሞግሱበት እና ተማሪዎችን የሚገመግሙበት የተራ መውሰድ ውቅር ነው።

በመረጃው ውስጥ የተገኙት የማነሳሳት- ምላሽ- ግምገማ ውቅሮች እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

ምሳሌ 23 /ቀ1/፡-

266.መ/ት፡- በጣም ጥሩ ስለዚህ ነጻ እና ጥገኛ ምእላድ ገብቷችኋል። እሺ ዛሬ የተማርነውን ትምህርት ስመክስስ ያህል እስቲ በድጋሚ ሲያስረዳን የሚችል ተማሪ መጀመሪያ ስለቅጥያዎች እሺ

267.ሴተ፡- ቅጥያዎች የምንላቸው በቃል በመነሻ እና በመድረሻ የሚገቡ

268.መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ!

ከላይ በምሳሌው እንደምንመለከተው 266ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷ ቀድመው ስለተማሩት ርዕሰ ጉዳይ ግልጽነት በማረጋገጥ ስለእለቱ ትምህርት የተማሩትን እንዲከልሱላቸው ይጠይቃሉ። በሚጠይቁበትም ወቅት ከተማሩት ትምህርት አንዱን ብቻ በመነጠል ስለቅጥያዎች እንዲያብራሩላቸው ተማሪዎችን ያነሳሳሉ። በመቀጠልም 267ኛው ተራ ቁጥር ላይ ተራው የተሰጣት ተማሪ ስለቅጥያ ምንነት በመግለጽ ተራዋን ስትጨርስ መምህርቷ በተራ ቁጥር 268 ተማሪዋ የሰጠችውን ገለጻ በመገምገም ትክክል መሆኗን ያረጋግጡላታል።

ምሳሌ 24 /ቀ2/፡-

452.መ/ት፡-እሺ እዚያው ገጽ ላይ ቁጥሮ ያለውን ምንባብ የሚያነብ ስደተኛው አባይን እሺ እህቴ
453.ሴተ ፡-

ከኢትዮጵያ፣ ካፍሪቃውያን ገነት

በገጃሙ ክፍል፣ ሰክሳ ከሚሉት

ከዚያ ከረግረጉ፣ ከግሽ አባይ መሬት

ከዚያ ነው የፈለቅኩ እወቁኝ ሲታውንት

ከዚያ ተነስቼ ስመሄድ አቀድኩኝ

በኮረኮንች መንገድ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ

በጥንተ ተፈጥሮ እኔን የመሰሉኝ

በግራና በቀኝ አክብረው አጀቡኝ

ትንሽ ወረድ እንዳልኩ ወተት አባይ አሉኝ

ከዚያ ተነስቼ እየተዝናናሁኝ

በጣና ሀይቅ ላይ አለፍኩና ሄድኩኝ

ከዚያ በኋላማ ታላቅ ጅረት ሆንኩኝ

ከዚያ አልፌ ስደርስ ከታላቁ ቁጥኝ

ፏፏቴ ሆንኩና ከሰማይ ወረድኩኝ

ካጠገቤ ቆመው የተመራመሩኝ

ጢስ አባይ አሉና ስሜን አወጡልኝ

ጎጃምን ከጎንደር እያካለልኩት

ወሎንም ከጎጃም እያዋሰንኩት

ሸዋንም ከጎጃም እያካፈልኩት

ወለጋን ከጎጃም እያካለልኩት

መንቀሳቀስ ጀመርሁ ወደተለመድኩት

454.መ/ት፡- እሺ እናመሰግናለን አጨብጭቡላት

ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው 452ኛው ተራ ቁጥር ላይ መምህርቷ ግጥሙን የሚያነብላቸውን ተማሪ በማነሳሳት ይጠይቃሉ። እድሉ የተሰጣት ተማሪም በ453ኛው ተራ ቁጥር ላይ የተሰጣትን ግጥም አንብባለች። በ454ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷ በተማሪዋ በመደሰታቸው የተነሳ ጥሩ ነው ከማለት ይልቅ የተሻለ ነው ብለው ያሰቡትን ቃል በመጠቀም አመሰግነዋታል። ከምስጋናም በላይ ሙሉ ክፍሉ እንዲያጨበጭብላት አድርገዋል። ይህም የሚያሳየን በግምገማ ላይ ሃሳብን በቃላት መግለጽ ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ጭምር ተማሪዎችን መገምገም እንደምንችል ነው።

ምሳሌ 25 /ቀ3/፡-

544.መ/ት፡- እናመሰግናለን ግጥሙን ስላነበበልን! አሁን ይሄ ግጥም ምጸት ዘይቤ ነው። አምስተኛው ምጸት ዘይቤ ፤ምጸት ዘይቤ ምን አይነት ነው ታስታውሱ ከሆነ

545.ወተ፡- ምጸት ዘይቤ የምንሰው ስምሳሌ አንድ ጥቁር ሰው ሲመጣ ውይ ቀዮ መጣ ብንሰው ሽሙጥ ማለት ነው።

546.መ/ት፡- አዎ

547.ሴተ፡- ምጸት ዘይቤ የምንሰው አንድን ሰው የምናሞግስ መስሰን በተቃራኒው የምንሰድበው ወይም የምናሽሚጥጠው ከሆነ ነው።

548.መ/ት፡- በጣም ጥሩ እሺ↑

ከዚህ ምሳሌ መረዳት የምንችለው መምህርቷ በ544ኛው ተራ ቁጥር ተማሪዎቹን ግጥም ካስነበቡ በኋላ የግጥሙን አይነት ነግራዋቸዋል። በመቀጠልም ምጸት ዘይቤ ምን እንደሆነ በመጠየቅ ተማሪዎቹን በማነሳሳት ጥያቄውን እንዲመልሱ አድርገዋል። ተማሪውም በተሰጠው ተራ መሰረት ምላሽ ሰጥቷል። መምህርቷም የተማሪውን ምላሽ አወንታ በመግለጽ ላይ እያሉ ተራ ያልተሰጣት ተማሪ 547ኛው ተራ ቁጥር ላይ መመልከት እንደሚቻለው ጣልቃ በመግባት ምላሽ ትሰጣለች። መምህርቷም በ548ኛው ተራ ቁጥር ላይ በቅሬታ ድምጽ ሁለቱንም ተማሪዎች ትክክል መመለሳቸውን በጣም ጥሩ በማለት አሞግሰዋል። ይሁን እንጂ የመምህርቷ የድምጽ ቅላጼ እንደሚያመለክተው እድል ሳይሰጣት ጣልቃ በመግባት የመለሰችው ተማሪ ምላሽ ትክክል ቢሆንም እንኳን ተማሪዋ ተራ ሳይሰጣት በመመለሷ ደስተኛ አይደሉም። ይህም የሚያሳየን በክፍል ውስጥ የንግግር ልውውጥ ተራ መውሰድ ወይም ተራን ጠብቆ መናገር ለመምህራንና ተማሪዎች አስፈላጊ መሆኑን ነው።

4.3.2. ማነሳሳት- ምለሽ- ምጋቤ ምላሽ

ማነሳሳት- ምላሽ- ምጋቤ ምላሽ ማለት መምህራን ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ የመሳላቸውን እንዲመልሱ የሚያደርጉበት ነው። በመጨረሻም ተማሪዎች ለሰጡት ምላሽ ትክክል የሆኑትን ትክክል ናችሁ በማለት ተጨማሪ የግል ሃሳብን መስጠት ወይም ከዚያው ጋር አያይዞ ሌላ ጥያቄ ማከልን እና ትክክል ካልሆኑ መሳሳታቸውን በመንገር እርማት የሚሰጥበት የተራ መውሰድ ውቅር ነው።

ምሳሌ 26 /ቀ1/፡-

85.መ/ት፡- እስቲ እጅ በማውጣት እሺ አለም ጸሀይ

86.ሴተ፡- በሶስት አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ

87.መ/ት፡- በሶስት አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ በጣም ጥሩ! መደቦች ሶስት ናቸው። አንደኛ መደብ አስ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ፣ አንደኛ መደብ እስቲ እነማናቸው?

ይህንን ምሳሌ ስንመለከት በ85ኛው ተራ ቁጥር ላይ መምህርቷ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎችን ያነሳሳሉ። ተራ የተሰጣት ተማሪም በ86ኛው ተራ ቁጥር ላይ ምላሽዋን ትሰጣለች። በመቀጠልም መምህርቷ ምላሹ ትክክል መሆኑን በመግለጽ ሌላ ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ ይህም ምጋቤ ምላሽን ይመለከታል።

ምሳሌ 27 /ቀ1/፡-

154.መ/ት፡- እነዚህ ሲደመሩ ምን ይሆናሉ? [አረፍተነገር]

155.ተህ፡- [አረፍተነገር]

156.መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ! ባለቤት ምን ማለት ነው? እሺ ፍቅር

ከምሳሌ 27 የምንረዳው መምህርቷ ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ ራሳቸው የጠየቁትን ጥያቄ ለተማሪዎች እድል ከሰጡ በኋላ አንድ ላይ በመናገር ወይም በመመለስ መምህርቷ ድርርቦሽ መፍጠራቸውን ነው። የማነሳሳት እና የምላሽ ሂደቱ በዚህ መልኩ ከተከናወነ በኋላ ምጋቤ ምላሹ በ156ኛው ተራ ቁጥር ላይ የተማሪዎቹን ምላሽ በማድነቅ ሌላ ጥያቄ በማስከተል ተራዊ ንግግራቸውን ይጨርሳሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ሁለቱ የራይምስ የተራ መውሰድ ውቅሮች በመጠኑ የተከሰቱ ቢሆንም አብዛኛው ተራዊ ንግግር ግን ከላይ ከተተነተኑት ከሁለቱ ውቅሮች ውጭ ነው።

4.3.3. ጥያቄ-ምላሽ

ይህ ውቅር በራይምስ ያልተጠቀሰ ነገር ግን በዚህ ጥናት የተገኘ ነው። ከዚህም የምንረዳው ራይምስ በጥናታቸው የተራ መውሰድ ውቅሮች ናቸው ብለው ከጠቀሷቸው ሌላ የተራ መውሰድ ውቅር መኖሩን ነው። ይህም ውቅር በመረጃው ውስጥ በተከታታይነት የተከሰተው ጥያቄ-ምላሽ ወይም ማነሳሳት-ምላሽ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ምሳሌዎች ከእያንዳንዱ ቀረጻዊ መረጃ አንጻር እንመልከት፡-

ምሳሌ 28 /ቀ1/፡-

69. መ/ት፡- ጾታን ያመለክታል። ሁለተኛው ጾታን ነው። ...,... እስቲ ጾታን ከሚያመለክቱ ቅጥያዎች የተወሰኑትን ንገሪኝ።
70. ወ፡- ይኸው ቲቸር
71. ወ፡- ለምሳሌ ልጅ እና ልጂት
72. መ/ት፡- አዎ ልጅ ከሆነ ልጁ ብንለው ማን አለ?
73. ተ፡- ወንድ
74. መ/ት፡- አይደለ
75. ተ፡- አዎ
76. መ/ት፡- ልጁ ስንል-ሱ ነው ልጂት ስንል ደግሞ(.)
77. ተ፡- -ሲት
78. መ/ት፡- ልጁ ወንድ መሆኑን ልጂት ደግሞ ሴት መሆኗን ያሳያል። እስቲ ሌላ ደግሞ ተጨማሪ
79. ሴ፡- መምህር መምህርት
80. መ/ት፡- መምህር መምህርት አዎ! ስለዚህ ት የምትለው ነች ማለት ነው። በጣም ጥሩ ከጾታ ባሻገር ሌላ ቅጥያዎች º...º
81. ወ፡- መደብን ያመለክታል
82. መ/ት፡- እሺ መደብን በምንመለከትበት ሰዓት መደብ በራሱ በስንት ይከፈላል?
83. ተ፡- በሶስት

ከምሳሌው መረዳት የምንችለው ይህንን ውቅር ከጥያቄ ምላሽ ወይም ማነሳሳት ምላሽ ልንፈርጀው እንደምንችል ነው። ይህም ሂደት መምህርቷ ጥያቄ በሚጠይቁበት ወቅት ተማሪዎች ምላሽ የሚሰጡበት በመሆኑ በዚህ ጥናት የተገኘ አንድ ውቅር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ምሳሌ 29 /ቀ2/፡-

318.መ/ት፡- እናመሰግናለን ትንሽ እናስተካክለው በስድ ጽሁፍ ውስጥ አንቀጽ እንዳለ ሁሉ በግጥም ውስጥ ምንድን ነው የሚባለው

319.ሴ፡- አንጓ ወይም አርኬ

320.መ/ት፡- አዎ አንጓ ወይም አርኬ ይባላል። እሺ በጣም ጥሩ ሌላ ምንድን ነው ቀለማት ናቸው እንቆጥራለን ቀለም የምንለው የአናባቢና ተነባቢ ሆሂያት በአንድ ላይ ሲመጡ ማለት ነው እሺ ከመጀመሪያው እንጀምር እና የግጥም ሙያዊ ቃላት የምንላቸው አሉ። የመጀመሪያው ስንኝ ነው..,... ስንኝ ምንድን ነው እሺ መሳል ያለበው

321.ወ፡- የግጥም አንድ መስመር

322.መ/ት፡- በጣም ጥሩ ስንኝ የምንለው የግጥም አንድ መስመር ነው።___(0.15)___((በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻ በምትጽፍበት ወቅት)) ሁለተኛው የስንኝ ግማሽ ማን ነው

323.ተ፡- ሀረግ

324.መ/ት፡- በተለምዶ የስንኝ ግማሽ አካልን ሀረግ እንለዋለን ። ግን አሁን እንደዚህ ነው የምትሉት

325.ተ፡- አይደለም

326.መ/ት፡- ታድያ ምንድን ነው የምትሉት

327.ሴ፡- በአንድ ስንኝ ውስጥ ሁለት ሀረግና ከዚያ በላይ ሊኖር ይችላል።

328.መ/ት፡- በአንድ ግጥም ውስጥ የምትገኝ ስንኝ ሁለት ሀረግ ሶስት ሀረግ አራት ሀረግ አምስት ሀረግ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ሀረግ የስንኝ ግማሽ አካል ሳይሆን ግጥሙን ስናነብ ቆም የምንልበት ቦታ ይህ ትንፋሽ የሚቆምበት ቦታ ስናነብ መለየት ካቃተን እንዴት አድርገን ማወቅ በየትኛው ስርዓተ ነጥብ ማወቅ እንችላለን

329.ተ፡- በነጠላ ሰረዝ

ከምሳሌው መረዳት የሚቻለው ተራ ቁጥር 318፣ 320፣ 322፣ 324፣326 እና 328 መምህር፡ ጥያቄ የሚጠይቁበት ሲሆን የተቀሩት 319፣ 321፣ 323፣ 325፣ 327 እና 329 ደግሞ ተማሪዎች ምላሽ የሚሰጡበት መሆኑን ነው። ይህም ከማነሳሳት ምላሽ ወይም ከጥያቄ ምላሽ ውቅር የሚመደብ ነው።

ምሳሌ 30 /ቀ3/፡-

472.መ/ት፡- አንድ ሰው አወዳደቁን ምን ይመስላል ስንል ዛፍ ተቆርጦ የሚወድቀውን ያህል አወዳደቁ የከፋ መሆኑን ስመግለጽ ያስችለናል። ሽማግሌው እንደ ሰካራም ይወላገዳሉ። አሁን ሰውዬውን ከምን ጋር ነው ያነጻጸረው እዚያጋ

473.ተ፡- ›‹

474.ወ፡- እኔ

475.መ/ት፡- አዎ

476.ወተ፡- ሽማግሌው ከሰካራም ሰው ጋር

477.መ/ት፡- አዎ አንድ ሽማግሌ ሰውና ጠጥቶ የሰከረ ሰው እንዴት ይራመዳል የሚለውን እንደ ማንጸሪያ ተጠቅመን የሽማግሌውን አረማመድ እንገልጻለን፡፡ ሃና እብድ ይመስል ጨርቁን ጣለች ስንልስ እሺ

478. ሴተ፡- እሳ እና እብዷን ነው ያነጻጸረው በትክክለኛው ስንሄድ ጸጉሯን አሳንጨባረረችም እብዷን ስናይ ደግሞ ጸጉሯን አንጨብራለች ስለዚህ ንጽጽሩ በሃና እና በእብዷ መካከል ነው ማለት ነው፡፡

479.መ/ት፡- የሃና ሁኔታ የእብድ ስለሚመስል ሁኔታዋን ነው እንደ እብድ የተጠቀምነው፡፡ አህመድ እንደ ህጻን አስቀሰ፡፡ እሺ ያልሞከረ ተማሪ

480.ተህ፡-‹›

ከዚህም ምሳሌ መረዳት የሚቻለው በንግግር ልውውጡ የሚካሄዱ ተራ መውሰዶች በጥያቄ ምላሽ ውቅር ላይ ተገነቡ መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት በተደጋጋሚ የተከሰተው ውቅር በምሁራን ዘንድ የማይታወቀው ጥያቄ-ምላሽ ወይም ማነሳሳት-ምላሽ ሲሆን ራይምስ በጥናታቸው የተራ መውሰድ ውቅሮች ናቸው ብለው ያነሷቸው ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ እና ማነሳሳት-ምላሽ-ምጋቤ ምላሽ በቁጥር አነስተኛ በሆነ መልኩ የተከሰቱ ውቅሮች ናቸው፡፡

4.4. የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህጎች

የዚህ ጥናት ግኝት እንደሚያለክተው ተማሪዎች እና መምህራን ተግባራዊ የሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህግ በምእራፍ ሁለት 2.9 የተገለጸውን 1ለን ነው፡፡ አንድ ለ ደግሞ ፡-

“ለ. እስካሁን የነበረው የመምህሩ ተራ የወቅቱ ተናጋሪ ተማሪ የሚቀጥለውን ተማሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ የወቅቱ ተናጋሪ ወይም መምህሩ መቀጠል አለበት” የሚል ነው፡፡

በዚህም መሰረት የሚከተለው የንግግር ልውውጥ ለዚህ ህግ እንደ ምሳሌ የቀረበ ነው፡፡

ምሳሌ 31 /ቀ1/ ፡-

288.መ/ት፡- ብሄራዊ ቲያትር አለ፡፡ ስለዚህ ቲያትር ለምንድን ነው ቲያትር (.)---0.8--- ((ከውጭ መምህርቷን ለማናገር በመጣ ሰው ምክንያት የንግግር መቋረጥ)) እ እሽ አሁን ስለ ቲያትር

ተነጋገረናል አገር ፍቅር አስ ሲኒማ ቤት ብሄራዊ ቲያትር አስ። ከዚያ ቀጥሰን የተነጋገርነው የቲያትር አስባዊያን አሱ አደደል የተውኔት አሳባዊያን አሱ እሺ እነማን እነማን ናቸው ፋንቱ

289.ሴተ፡- ግጥም

290.መ/ት፡- እ

291.ወተ፡- መቼት

292.መ/ት፡- መቼት

293.ወተ፡- ታሪክ

294.መ/ት፡- ታሪክ

295.ወተ፡- ትልም

296.መ/ት፡- ትልም

297.ወተ፡- ግጭት

298.መ/ት፡- እሺ

299.ወተ፡- ትልም

300.መ/ት፡- ትልም እሺ

301.ሴተ፡- @@@º º

302.መ/ት፡- ምክንያቱን አውጭልኝ

ከምሳሌው መገንዘብ እንደሚቻለው የተራ አወሳሰድ ሂደቱ ተረኛው ተናጋሪ የሚቀጥለውን በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን መምህሩ ብቻ ለተማሪዎቹ ተራ የሚሰጥበት ነው በዚህም መሰረት በህግ ሁለት ላይ የተገለጸውን "ተረኛው ተናጋሪ ተማሪ የሚቀጥለውን ተማሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ የአሁኑ ተናጋሪ ወይም መምህሩ መቀጠል አለበት" የሚለውን የሚያሟላ ነው። በሶስቱም ቀረጻዎች የተካሄደው የመማር ማስተማር እና የተራ መውሰድ ሂደት ተመሳሳይ በመሆኑ በዚህ ግኝት ተግባራዊ የሆነው ህግ ከላይ የተገለጸው ህግ አንድ ለ ነው። ይሁን እንጂ ከአራቱ ህጎች አንዱ ህግ 2. ንዑስ ርእስ "ሐ" ከጥናቱ ግኝት ጋር የሚቃረንበትም ሁኔታ አለ። ህጉንም ለምሳሌ ብንመለከት፡-

"ሐ. እስካሁን የተመረጡት ተማሪዎች ተራ የሚቀጥለውን ተናጋሪ ተማሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ መምህሩ ራሱን ካልመረጠ ተረኛው ተናጋሪ ሊቀጥል ይችላል ነገር ግን ግዴታ አይደለም" ይላል። ነገር ግን የሚቀጥለውን ተራ አወሳሰድ ብንመለከት ከዚህ ጋር የሚቃረን ሆኖ እናገኘዋለን።

ምሳሌ 32 /ቀ1/ ፡-

138.መ/ት፡- በበር ገባ በጣም ጥሩ በበር እሺ

139.ሴተ፡- በኢትዮጵያ

140.ወተ፡- በበኩሉ

141.መ/ት፡- እሺ

142.ወተ፡- በአገራችን

143.መ/ት፡- እሺ

144.ሴተ1፡- በእቃ

145.ሴተ2፡- በ..,...ቤታችን

146.መ/ት፡- ገብቷችኋል! እነዚህ ቅጥያዎች መነሻ ላይ በመግባት ቃል የሚቀይሩ ናቸው። ገጽ 109 ሁለተኛው ተራ ቁጥር ሂዱ። ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገር ስሩባቸው። ከዚያም የቃላቱን ሙያ ባለቤትነት ተሳቢነት እያላችሁ ግለጹ። አሁን ደግሞ ምንድነው የምንፈልገው ባለቤትን የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ነው። ከዚያ በፊት ግን አረፍተ ነገር እራሱ ምን ማለት ይመስላችኋል።

ከምሳሌው የምንረዳው ነገር ከህጉ በተቃራኒ ነው። 140ኛ እና 145ኛውን ተራ ቁጥር ስንመለከት "መምህሩ ራሱን ካልመረጠ ተረኛ ተናጋሪው ሊቀጥል ይችላል" የሚለውን ህግ አያሟላም ምክንያቱም እንደ ህጉ ከሆነ 140ኛው ተራ ቁጥር ላይ ተራውን መውሰድ የነበረባቸው መምህርቷ ወይም 139ኛ ተራ ቁጥር ላይ ተራውን የወሰደችው ተማሪ መሆን ነበረባት። ነገር ግን ተራውን የወሰደው ለተራው ራሱን የመረጠው ወንድ ተማሪ ነው። ከዚህ በተጨማሪም 145ኛው ተራ ቁጥር ላይ በተመሳሳይ መልኩ መምህርቷ ተራውን ሳይወስዱ ቀርተው እና የአሁኗ ተናጋሪ ሳትቀጥል በመቅረቷ ሌላ ሴት ተማሪ ራሷን በመምረጥ ተራውን ወስዳለች። ስለዚህ የጥናቱ ግኝት ይህንን ህግ በሌላ አቅጣጫ እንድንመለከተው መንገድን ከፍቷል።

4.5. በተራ መውሰድ ወቅት የተራ አሰጣጥ ሂደት

የተራ አሰጣጥ ሂደት በንግግር ልውውጥ ወቅት አንድ ተሳታፊ የጀመረውን ተራዊ ንግግር ሲያጠናቅቅ ለማን ተራ እንደሚሰጥ እና ከማን ተራ እንደሚቀበል የምንመለከትበት ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡-

ምሳሌ 33 /ቀ1/ ፡-

147.__(0.54)__((ትምህርቱ እስኪጀመር ድረስ ያለፈ ጊዜ))

148.መ/ት፡- እሺ... እሺ ተማሪዎች የ...ባለፈው ትምህርታችን ስለምን ነበር?

149.ወ፡- ስለ ተውኔት

150.መ/ት፡- እጅ በማውጣት! እሺ እህቴ

151.ሴ፡- ስለ ተውኔት

152.መ/ት፡- ተውኔት፣ተውኔት ምንድነው አልን?

153.ወ፡- የስነጽሁፍ ዘርፍ

154.መ/ት፡- እሺ ሴላ ተጨማሪ

155.ተ፡-_____

156. መ/ት፡- እሺ ተውኔት በየት ቦታ [ይታያል አልን]?

157. ተ፡- [ቲያትር ቤት]

158. መ/ት፡- ተውኔት የራሱ የሆነ ቲያትር ቤት አለው። ድራማ እና ፊልም ብንመለከት በሬድዮ ወይም በቴሌቭዥን ይቀርባል። ተውኔት ግን የራሱ የሆነ ቦታ አለው ይህም ቲያትር ቤት ነው። እስቲ ከአዲስ አበባ ትያትር ቤቶች የሚነግረኝ?

ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው ተራ የሚሰጡት መምህርቷ ሲሆኑ ተራውን የሚቀበሉት ደግሞ ተማሪዎች ናቸው

ሂደቱ ተመሳሳይ ሆኖ እያለ አንዳንድ ጊዜ ተራ ሳይሰጣቸው ለራሳቸው ተራ በመስጠት ንግግር የሚያደርጉ ተማሪዎች ግን ተራውን ከተማሪዎች የሚቀበሉበት ሁኔታም አለ።

ምሳሌ 34 /ቀ1/ ፡-

41.መ/ት፡- አዎ! ቅጥያዎች ብቻቸውን ትርጉም ያሌላቸው ሲሆኑ ከቃላት ጋር በመጣመር ፍች ይሰጣሉ። ለምሳሌ አንደኛው የብዛት ፍች ነው [አይደል?]

42. ተ፡- [አዎ]

43. መ/ት፡- ለምሳሌ የብዛት ፍችን የሚያመለክቱ ቅጥያዎች እነማናቸው?

44. ተ፡- ይሀው ቲቸር

45. ሴ1፡- -ኦች

46. ሴ2፡- [-ዎች]

47. ተህ፡- [-ዎች]

48. መ/ት፡- እ?

49. ወተ፡- ች

50. መ/ት፡- እነ- እና (.)

51. ወተ፡- -ዎች

52. መ/ት፡-እነዚህን ቅጥያዎች ስንመለከት እዚህ ጋ ምልክት የምናደርገው ለምንድነው?

ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው በ41ኛው፣ በ43ኛው እና በ48ኛው ተራ ቁጥር መምህርቷ ለተማሪዎች ተራ የሚሰጡበት መሆኑን ነው። ነገር ግን ከተራ ቁጥር 44-47 ያለውን ተራ አወሳሰድ ስንመለከት ተማሪዎች ተራ ሳይሰጣቸው በሚያደርጉት ንግግር ምክንያት ከተማሪዎች ተራን የሚቀበሉበት መሆኑን እንረዳለን።

4.6 በራስ ተነሳሽነት ተራ መውሰድ

በዚህ ክፍል የምንመለከተው ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ የሚወስዱት ምን ክስተት ሲፈጠር እንደሆነ እያንዳንዱን መረጃ በምሳሌነት በመጥቀስ ነው።

ምሳሌ 35 /ቀ1/ ፡-

239.መ/ት፡-ጥገኛ ምእላድ እሺ ገበሬዎች እጅ በማውጣት እሺ ገበሬዎች ያልሞከረ ተማሪ እስካሁን እሺ=

240.ሴተ፡- =ገበሬ ነጻ ሲሆን -ኦች ደግሞ ጥገኛ ምእላድ ነው።

241.መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ ስሙ የሚሰው እሺ ሃቢብ=

242.ወተ፡- ስሙ ነጻ ምእላድ

243.መት፡- ስሙ...

244.ተህ፡- አይደለም

245.ወተ፡- [ስም እና -ሹ]

246.ተህ፡- [ስም እና -ሹ]

ከምሳሌ 35 የምንረዳው ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነት ተራ የሚወስዱት ጥያቄው ቀላል ሲሆን እና ምላሹ የሚታወቅ በሚሆንበት ጊዜ መሆኑን ነው። ይህም ከታች ክፍል ጀምሮ ተማሪዎቹ ስለ ቅጥያዎች ወይም ምዕላዶች የተማሩ ስለሆነ እድል እስኪሰጣቸው ሳይጠብቁ በራሳቸው

ተነሳሽነት ተራን በመውሰድ ምላሽ ሰጥተዋል። ስለዚህ በራስ ተነሳሽነት ተራ ከሚወሰድበት መንገድ አንዱ የጥያቄዎች መቅለል ነው ማለት እንችላለን።

ምሳሌ 36 /ቀ1/ ፦

181. መ/ት፦ እሺ እነዚህ የቁጥር አገልግሎታችው ነው። ሴሳስ የቅጥያ አገልግሎት? ((ስማንም ተራ ሳትሰጥ ዝም በማለት ወደ ጥቁር ሰሌዳ ፊቷን አዙራለች))
182. ሴተ1፦ ጾታን ያመለክታል
183. ሴተ2፦መደብን ያመለክታሉ ((ጣልቃ በመግባት))
184. መ/ት፦ ጾታን ያመለክታል። ሁለተኛው ጾታን ነው። ...,... እስቲ ጾታን ከሚያመለክቱ ቅጥያዎች የተወሰኑትን ንገሩኝ።

ምሳሌ 36 ላይ የቀረበው የንግግር ልውውጥ መምህርቷ ጥያቄ ጠይቀው ለተማሪዎች እድል በማይሰጡበት ሁኔታ ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነት ተራ መውሰዳቸውን የሚያመለክት ነው። ይህንን የምንረዳው አጥኚዋ በተራ ቁጥር 66 በሰጠችው አስተያየት ነው።

ምሳሌ 37 /ቀ1/ ፦

90.መ/ት፦ ነጠላ ቁጥር ሲሆን እኔ ብዙ ቁጥር ሲሆን
91. ወተ፦ እነሱ
92. ሴተ፦ እኛ

በተራ ቁጥር 90 ላይ እንደምንመለከተው መምህርቷ ምላሽ በመስጠት ላይ እያሉ ሳይጨርሱ ለተማሪዎቹ ልቅ ወይም ክፍት አድርገው ትተዋል። ይህም ለተማሪዎቹ በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ እንዲወስዱ ምክንያት ሆኗቸዋል።

ምሳሌ 38 /ቀ1/ ፦

241.መ/ት፦ እሺ በጣም ጥሩ ስሙ የሚሰው እሺ ሃቢብ=
242.ወተ፦ ስሙ ነዳ ምእሳድ
243.መት፦ ስሙ...
244.ተህ፦ አይደለም
245.ወተ፦ [ስም እና -ሱ]

246.ተህ፡- [ስም እና -ሹ]

247.መ/ት፡- ስም እና ሹ በጣም ጥሩ በእናትህ

ተራ ቁጥር 242 ላይ እንዲናገር እድል የተሰጠው ተማሪ ምላሹ ስህተት ነበር። ስህተት መሆኑንም መምህርቷ በመጠቆም ላይ እያሉ ተማሪዎቹ ከተራ ቁጥር 244-246 ድረስ ያለውን ተራ በራሳቸው ተነሳሽነት በመውሰድ ትክክል አለመሆኑን ጠቁመውታል። ስለዚህ የተረኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ምላሽ ስህተት መሆን እና የሌሎች ተማሪዎች ምላሹ ስህተት መሆኑን ማወቅ በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ እንዲወስዱ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ነው ማለት ይቻላል።

ምሳሌ 39 /ቀ2/ ፡-

392.መ/ት፡- ስንኝ የምንለው የመጨረሻው በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርስ ነው።

ጥዋት ብድግ ንስት ትስውና

ፊቷን ፍትግ ፍትግትግ

ዳሩ -ሳ---ዋን ዳሱሳዋን ልቅልቅ ስትል

ሴሳ ምናምኗን ዱቅት ሸፋሳን ሸፍል ጥቁር

ከንፈሯን ቅልት ቅልት ታደርግና

ንስት፣ፍትግ...ስለዚህ ስንት ስንኝ አለው

393.ተህ፡- አምስት-ስድስት- አራት

394.ወተ፡- አረ አይደለም ሰባት ነው

395.መ/ት፡- አምስት አይደለም ሁሳችንንም የሚያስማማ ቁጠሩ እና ንገሩኝ

ምሳሌ 39 ተራ ቁጥር 393 እና 394ን ብንመለከት በምላሹ ባለመስማማት ምክንያት የተፈጠረ በራስ ተነሳሽነት የተካሄደ ተራ መውሰድ ነው። ይህም የሚናገሩት ተማሪዎች በሙሉ ትክክል ነን ብለው አስበው በሚናገሩበት ጊዜ ሌሎች ተማሪዎችም እኛም ትክክል ነን በሚል ልበ ሙሉነት የየራሳቸውን ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት የሚፈጠር በራስ ተነሳሽነት የሚካሄድ የተራ መውሰድ ሂደት ነው። ስለዚህ ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነት ተራ ከሚወስዱበት መንገድ አንዱ መልሳችን ትክክል ነው ብለው መሰባቸው ነው ማለት ይቻላል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና ጠቋሚ አስተያየት

5.1. ማጠቃለያ

የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ማካሄድ እና የመምህር ተማሪን የክፍል ውስጥ የንግግር ልውውጥ ማጥናት የመማር ማስተማሩን መስተጋብር ምንነት በትክክል ለመረዳት ጉልህ ፋይዳ እንዳለው የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። ከነዚህም ምሁራን አንዱ ክራምስች የሚከተለውን አገልግሎት እንዳለው ይጠቁማሉ። የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማሻሻል እና ተጨማሪ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማድረግ የተራን ጠብቆ መናገር ውቅሮችን ማጥናት ቀላል ባይሆንም አስፈላጊ ነው። ክራምስች (1987፣22) እንደሚገልጹት ተማሪዎች እንዴት ተራን ጠብቀው መናገር እንዳለባቸው ማስተማር ቀላል አይደለም። ስለዚህ ይህ መጠናት የሚያስፈልገው ችግሮች በስፋት የሚታዩበት አካባቢ ነው ይላሉ።

ከችግሮቹም መካከል አንዱ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተራ መውሰድ ህጎችን ተግባራዊ ሲያደርጉ አለመስተዋላቸው አጥኚዋን ጥናቱን እንድታካሄድ መነሻ ሆኗታል። ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የመምህር ተማሪ የተራ አወሳሰድን በተመለከተ ጥናት ያልተካሄደበት በመሆኑ አጥኚዋ ጥናቱን እንድታካሄድ ፍላጎት አድሮባታል።

የዚህ ጥናት መነሻውም ይህው ነበር። የጥናቱ ዋና አላማም የተራ መውሰድ አደረጃጀት እና የተራ መውሰድ ህጎች አተገባበር ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንጻር መመራመር የሚል ሲሆን ጥናቱም በዝርዝር የሚመለከተው የተማሪዎችን እና የመምህራንን የተራ አወሳሰድ ሂደትን ዓላማ በማድረግ ነው። ጥናቱ በሂደቱ ለመመለስ ይሏቸው የተነሳው መሪ ጥያቄዎችም፡

- በተራ መውሰድ ሂደት ተደጋግመው የሚከሰቱት ውቅሮች ምን ምን ናቸው?
- ተማሪዎች እና መምህራን የትኛውን የተራ መውሰድ ህግ ተግባራዊ ያደርጋሉ?
- በተራ መውሰድ ሂደት ውስጥ ማን ለማን ተራ ይሰጣል ወይም ማን ከማን ይቀበላል?
- ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነትስ ተራ ይወስዳሉ ወይስ አይወስዱም? የሚወስዱ ከሆነ ምን ክስተት ሲፈጠር ነው? የሚሉት ናቸው።

ይህን አላማውን ለማሳካትም በአግዓዚያን ቁጥር ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሶስት ቀናት ቀረጻ በማድረግ የንግግር ልውውጡ መረጃም ወደ ጽሁፍ ተቀይሯል። ወደ ጽሁፍ በተቀየረው መረጃ ላይ ተመስርቶም ትንተናው ተካሂዷል። በትንተናው የተገኘው ውጤትም የሚከተለው ነው።

የተራ መውሰድ አካላት የሚባሉት ተራን መገንቢያ አሃድ፣ ተራን መምረጫ ስልት፣ መቋረጥ ወይም ድርርቦሽ፣ አርምሞ እና ማስተካከያ ናቸው።

የተራ መገንቢያ አሃዶች ከመዋቅር አንጻር ሲታዩ ዓረፍተ ነገራዊ፣ ቃላዊ እና ድምጻዊ ሊሆኑ ይችላሉ (ሳክስ እና ሌሎች 1974)። የመናገር ተራ የደረሰው ተሳታፊ ንግግሩን ለማፍሰቅ እነዚህን የተራ መገንቢያ አሃዶች ሊጠቀም ይችላል። ሳክስ እና ሌሎች የተራ መገንቢያ አሃዶች ናቸው ብለው ከዘረዘሯቸው ድምጻዊ፣ ቃላዊ እና ዓረፍተ ነገራዊ አሃዶች በተጨማሪም በዚህ ጥናት የተረጋገጠው ግጥም የተራ መገንቢያ አሃድ መሆኑን ነው።

የተራ መገንቢያ አሃዶች በእያንዳንዱ መረጃ ያላቸው ስርጭትም የተለያየ ነው። ከጠቅላላው 556 ተራዊ ንግግሮች ውስጥ 234 (42.09) ያህሉ የተገነቡት ከአረፍተ ነገራዊ አሃድ ሲሆኑ 24 (4.32) ያህሉ ደግሞ ከቃል መሰል ድምጽ ነው። ከመረጃው የተገኘው ንጽጽራዊ ስሌት እንደሚጠቁመው አረፍተ ነገራዊ ተራን መገንቢያ አሃድ በሶስቱም መረጃዎች ያለው ስርጭት ሰፊ መሆኑን እና የቃል መሰል ድምጽ ተራን መገንቢያ አሃድ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ስለሆነም በመምህር ተማሪ የክፍል ውስጥ የንግግር መስተጋብር ተደጋግሞ የተከሰተው ተራን መገንቢያ አሃድ አረፍተ ነገራዊ ውቅር ሲሆን የድግግሞሽ መጠኑ አናሳ የነበረው ደግሞ የቃል መሰል ድምጽ ተራን መገንቢያ አሃድ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል።

በንግግር ልውውጡ ወቅት ተግባር ላይ ከዋሉት ተራ መውሰዶች ከቃላት ብዛት አኳያ በሶስቱም መረጃዎች መምህርቷ 4654 (70.54%) እና ተማሪዎች ደግሞ 1944 (29.46%) ቃላትን የያዙና በአረፍተ ነገራዊ አሃዶች የተገነቡ ተራዊ ንግግሮችን መጠቀማቸውን ነው። መጠናዊ ስሌቱ እንደሚያሳየውም መምህርቷ ከተማሪዎቹ ተራዊ ንግግሮች የረዛዘሙ ተራዎችን ተጠቅመዋል። ከዚህም በመነሳት መምህራን በተራ አወሳሰድ ረገድ ረጅም ጊዜን ይጠቀማሉ ማለት ይቻላል።

ሁለተኛው የተራ መውሰድ አካል የሆነው ባለ ተራን መምረጫ ስልት ሲሆን የንግግር ልውውጥ ተሳታፊዎች ቀጣዩን ተናጋሪ በሁለት መንገዶች ሊመረጡ ይችላሉ። አንድም

እየተናገረ ያለው ተሳታፊ ቀጣዩን ተናጋሪ ሊመርጥ ይችላል፤ አለበለዚያም ቀጣዩ ተሳታፊ ራሱን በተናጋሪነት በመምረጥ ንግግሩን ይጀምራል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የተረጋገጠው በማስተማር ሂደቱ የተካሄዱ ተራዊ ንግግሮች ሁለቱንም የባለ ተራ መምረጫ ስልቶች በተግባር ላይ ማዋላቸውን ነው።

ማስተካከያን መሻት ተሳታፊዎች በመናገር፣ በማዳመጥ እና በመረዳት ረገድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች፣ መፍትሄ የሚሰጡበት ነው። በመማሪያ ክፍል ተራዊ ንግግርም ይህ ስልት ለዚሁ ተግባር ሲከናወን ተስተውሏል። በዚህ ጥናት የተገኘው ግኝት የሚጠቁመው በተራ መውሰድ ወቅት ከሚደረጉ ማስተካከያዎች ውስጥ ሶስቱ ማለትም በራስ አነሳሽነት የሚደረግ ማስተካከያ፣ በሌሎች አነሳሽነት በራስ የሚደረግ ማስተካከያ እና በሌሎች አነሳሽነት በሌሎች የሚደረግ ማስተካከያ፣ ብቻ ተግባራዊ መሆናቸውን ነው።

በዚህ ጥናት በተደጋጋሚ የተከሰተው ውቅር በራይምስ ጥናት ያልተጠቀሰው ጥያቄ-ምላሽ ወይም ማነሳሳት-ምላሽ ሲሆን ራይምስ በጥናታቸው የተራ መውሰድ ውቅሮች ናቸው ብለው ያነሷቸው ማነሳሳት-ምላሽ-ግምገማ እና ማነሳሳት-ምላሽ-ምጋቤ ምላሽ በቁጥር አነስተኛ በሆነ መልኩ የተከሰቱ ውቅሮች ናቸው።

የዚህ ጥናት ግኝት እንደሚያለክተው ተማሪዎች እና መምህራን ተግባራዊ የሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተራ መውሰድ ህግ የሆነውን 1ለን ነው። አንድ ለ ደግሞ፡- "እስካሁን የነበረው የመምህሩ ተራ የወቅቱ ተናጋሪ የሚቀጥለውን በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ የወቅቱ ተናጋሪ ወይም መምህሩ መቀጠል አለበት" የሚል ነው። በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው ህግ ከላይ የተገለጸው ህግ አንድ ለ ነው።

ይሁን እንጂ ከአራቱ ህጎች አንዱ ከጥናቱ ግኝት ጋር የሚቃረንበትም ሁኔታ አለ። ንዑስ ርእስ ህግ 2.ሐ." እስካሁን የተመረጡት ተማሪዎች ተራ የሚቀጥለውን ተናጋሪ በመምረጥ ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ መምህሩ ራሱን ካልመረጠ የአሁኑ ተናጋሪ ሊቀጥል ይችላል ነገር ግን ግዴታ አይደለም" የሚለው የሳክስ እና ሌሎች (1974) ህግ ከዚህ ጥናት ጋር የማይስማማ ነው።

የተራ አሰጣጥ ሂደት በንግግር ልውውጥ ወቅት አንድ ተሳታፊ የጀመረውን ተራዊ ንግግር ሲያጠናቅቅ ለማን ተራ እንደሚሰጥ እና ከማን ተራ እንደሚቀበል የምንመለከትበት ነው። በዚህም ጥናት ግኝት አብዛኛውን ጊዜ ተራ የሚሰጡት መምህርቷ ሲሆኑ ተራውን የሚቀበሉት

ደግሞ ተማሪዎች ናቸው። ሂደቱ ተመሳሳይ ሆኖ እያለ አንዳንድ ጊዜ ተራ ሳይሰጣቸው ለራሳቸው ተራ በመስጠት ንግግር የሚያደርጉ ተማሪዎች ግን ከተማሪዎች ተራን የሚቀበሉበት ሁኔታም አለ።

ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ የሚወስዱት ምን ክስተት ሲፈጠር እንደሆነ በዚህ ጥናት የተደረሰበት ውጤት የሚከተለው ነው። የጥያቄዎች መቅለል፣ መምህርቷ ምላሽ በመስጠት ላይ እያሉ ሳይጨርሱ ለተማሪዎቹ ልቅ ወይም ክፍት አድርገው ሲተው፣ የተረኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ምላሽ ስህተት መሆን እና የሌሎች ተማሪዎች ምላሽ ስህተት መሆኑን ማወቅ በራሳቸው ተነሳሽነት ተራ ሲወስዱ፣ የሚናገሩት ተማሪዎች በሙሉ ትክክል ነን ብለው አስበው በሚናገሩበት ጊዜ ሌሎች ተማሪዎችም እኛም ትክክል ነን በሚል ልበ ሙሉነት የየራሳቸውን ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት እና መምህርቷ ጥያቄ ጠይቀው ለተማሪዎች እድል በማይሰጡበት ሁኔታ ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነት ተራ መውሰዳቸውን ይህ ጥናት አረጋግጧል።

5.2 ጠቋሚ አስተያየት

ከዚህ ጥናት ውጤት በመነሳት የሚከተሉት ጠቋሚ አስተያየቶች ቀርበዋል።

1. የተራ አወሳሰድ መጠኑ በመምህራንም ሆነ በተማሪዎች ላይ ከክፍለ ጊዜ ክፍለ ጊዜ ልዩነት መታየቱ ተገልጸአል። ስለሆነም ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ከትምህርት አይነት እና ከመምህራን ስልጠና አንጻር ቢጠና፤
2. በመምህር ተማሪ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ማስተካከያን መሻት ስልቶች መካከል በራስ አነሳሽነት የሚደረግ ማስተካከያ በቁጥር አነስተኛ ወይም በጥናቱ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ የተከሰተ ሲሆን፣ በሌሎች አነሳሽነት የራስን ችግር በራስ ማስተካከል ደግሞ ተደጋግሞ እንደተከሰተ ተጠቁሟል። ስለሆነም እነዚህ ስልቶች ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ያላቸው ልዩነት ጥናት ቢካሄድበት፤
3. በተራ አወሳሰድ ረገድ ተማሪዎች ከመምህራኑ የበለጠ ተራ እንደወሰዱ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል። ይህ ሁኔታ በሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም የማረጋገጫ ጥናት ቢሰራበት፤
4. በዚህ ጥናት የመምህርቷ ተራዊ ንግግሮች አንጻራዊ ርዝመት እንዳላቸው ተጠቁሟል። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል መዳበር ሊቀንስባቸው ስለሚችል የት/ት

መሳሪያ አዘጋጆች የክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተናን በመምህራን ስልጠና መርሃ ግብር እንዲካተት ቢያደርጉ፤

5. መምህራን የክፍል ውስጥ ዲስኩርን በመተንተን የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማዳበርም ሆነ የራሳቸውን የንግግር ልውውጥ መመጠን ይችሉ ዘንድ ስለዲስኩር ትንተና የስራ ላይ ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ በሚመለከታቸው አካላት ቢመቻች፤
6. በዚህ ጥናት የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያትን የተራ መውሰድ ስንመረምር ተደጋግሞ የተከሰተው ውቅር በመጠኑ ተጠቁሟል። ይሁን እንጂ ይህ የተገኘው አዲስ ውቅር በስፋት አልተዳሰሰም፤ የታዩትም ቢሆኑ እንደገና በስፋት ቢጠኑ የመስኩን እውቀት ያጠናክረዋል።

ዋቢ ጽሁፎች

ከበደ ይመር። 2000። "የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የመምህር ተማሪ ንግግር ልውውጥ ትንተና"።ለአማርኛ ማስተማር ዲግሪ መሚያነት የተሰናዳ ጥናት ። አዲስ አበባ ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት። (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ። 1998። *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር*። ባህር ዳር፤ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ። አልፋ ማሳተሚያ ድርጅት።

ጌታቸው እንዳላማው። 1987። "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ስነ ጽሁፍ ተማሪዎች በተጻፉ ተራኪ ውህድ አሃዶች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች ስርጭትና ተግባር ትንተና።" ለአማርኛ ማስተማር ዲግሪ መሚያነት የተሰናዳ ጥናት ። አዲስ አበባ ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት። (ያልታተመ)

Allwright, R. L. 1980. Turns, topics, and tasks: Patterns of participation in language learning and teaching.In D. Larsen-Freeman (Ed.), *Discourse analysis in second language research*. (pp. 165-187). Rowley, MA: Newbury House

Allwright, R. L. 1984. "The Importance of Interaction in Classroom Language Learning". *Applied Linguistics*. 5/2,156 -171.

Brown, G. and Yule, G.1983. *Discourse Analysis*. Cambridge: Cambridge University Press.

Christie F. 2002. *Classroom Discourse Analysis A Functional Perspective*. New York: Continuum

Cook, G.1989. *Discourse.* Oxford: Oxford University Press.

Cunningsworth, A. 1987. "Course Book and Conversation Skills." In L.E. Sheldon (ed). *ELT Text Book and Materials; Problems, Evaluation and Development.* London: Modern English Publication.

Edelsky, C. 1981. *Who's got the floor? Language in society,*10 , 383-421. http://dx.doi.org/10.1017/S004740450000885X. [accessed nov.5/ 2012]

Ellis, R.1988b. *Classroom Second Language Development.* New York: Prentice Hall International.

Heritage, J. 1998. "Conversation Analysis and Instutional Analysis: Analyzing Distinictive Turn Taking System." In S, Cmerjrkova et al. (eds). *Proceeding of The Sixth International Congress of IADA.* Retrived from www.google.com/wikepidea/.

Herman, V. 1995. *Dramatic Discouse: Dialogue as Interaction in Plays.* London: Routledge.

Herman, V. 1998. "Turn management in drama". In J. Culpepper, M. Short and P. Vedonk. *Exploring the Language of Drama: From Text to Context.* London: Routledge.

Hutchby, I. and Wooffitt, R. 2002. *Conversation Analysis.* Great Britain: Polity Press and Blackwell.

Ikatura, H. 2001. 'Describing Conversational Dominance.' *Journal of Pragmatics* 33: 12:1859-1880.

Köktürk Şaban. 2012. Forms and Multi functionality of Interruptions and Simultaneous Speaking in Ordinary Talk — proposal of a Universal Model for the Evaluation of Interruptive Speech Sequences. *International Journal of Linguistics.* ISSN 1948-5425 2012, Vol.4, No.3 www.macrothink.org/ijl 551 [accessed, jan 26/2013]

Kramsch, J. 1987. "Interactive Discourse in Small and Large Groups". In Rivers, W. (ed). *Interactive Language Teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Kumaravadivelu, B. 1999. "Language learning tasks: Teacher intention and learner interpretation." *ELT Journal*, 45, 98-107.

Lerner, G. H. 1996. "Finding faces in perefence structure of talk-in-interaction." *Social psychology quarterly*. Vol 49, no. 4, pp 303-321. Retrieved from http://www.jstor.org/.

Lomax, H. T. (No date). Discourse Analysis. Www.google.com. [Accessed, Des 14/2012].

Machol A. (No date). The Organization of Turns at Formal Talk in the Classroom. *Language and Society*. 7, 183-213. Printed in Great Britain.

Mortensen K. 2008. "Instructions and Participation in the Second Language Classroom". Ph.D Dissertation. Institute of Language and Communication University of Southern Denmark. (Unpublished). [Accessed, jan 26/2013].

Nicholls, J. 1993. "Exchange Structure in the ESL Classroom: Q-A-C and Q-CQ-A-C Sequences in Small Group Interaction." *Pragmatics and Language Learning,* Monograph Series (4), 183-191

Norton, B., & Toohey, K. 2002. Identity and language learning. In R.B. Kaplan (Ed.), *The Oxford Handbook of Applied Linguistics* (pp. 115-123). Oxford: Oxford University Press.

Rex, L. A., & Schiller, L. 2009. Using discourse analysis to improve classroom interaction. New York: Routledge.

Richards, J. C. 1980. *The Language Teaching Matrix*. Cambridge: Cambridge University Press.

Rugen B. D. 2010. Understanding Nontraditional Students Through Classroom Discourse Analysis. *The Language Teacher online*» <jalt-publications.org/tlt> [Accessed, jan 26/2013]

Rymes, B. 2008. *Class Room Discourse analysis*: A Tool for Critical Reflection. Cresskill, NJ: Hampton press.

Sacks, H., Schegloff, A. and Jefferson, G. 1974. "A Simplest Systematics for the Organization of Turn Taking for Conversation." *Language*. 50/4: 696 — 735.

Schegloff E. A. 2007. *Sequence Organization in Interaction A Primer in Conversation Analysis I*. Cambridge: Cambridge University Press

Schiffrin, D. 1988. 'Conversation analysis' in New Meyer, F. J. Linguistics: The Cambridge Survey. Language: The Study of Language as Socio-cultural Context. Cambridge: University of Cambridge. [Accessed, jun 06/2013].

Selting, M. 2000. 'The Construction of Units in Conversational Talk'. *Language in Society*. 29: 4: 477-517.

Sinclair,J. McH. and Coulthard, R. M. 1975. *Towards an Analysis of Discourse: The English Used by Teachers and Pupils*. London: Oxford University Press.

Van Lier, L. 1988. *The Classroom and The Language Learner*. London: Longman.

Wortham, S. 1998. The commodification of classroom discourse in post modern contexts. In L. van Lier & D. Corson. [accessed, jan 26/2013]

አባሪዎች

ቀረጻ አንድ

1. __(0.54)__((ትምህርቱ እስኪጀመር ድረስ መምህርቷ የእለቱን ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያለፈ ጊዜ))
2. መ/ት፡- እሺ... እሺ ተማሪዎች የ...ባለፈው ትምህርታችን ስለምን ነበር?
3. ወ፡- ስለ ተውኔት
4. መ/ት፡- እጅ በማውጣት! እሺ እህቴ
5. ሴ፡- ስለ ተውኔት
6. መ/ት፡- ተውኔት፣ተውኔት ምንድነው አልን?
7. ወ፡- የስነጽሁፍ ዘርፍ
8. መ/ት፡- እሺ ሴላ ተጨማሪ
9. ተ፡-_____
10. መ/ት፡- እሺ ተውኔት በየት ቦታ[ይታያል አልን]?
11. ተ፡- [ቲያትር ቤት]
12. መ/ት፡- ተውኔት የራሱ የሆነ ቲያትር ቤት አለው። ድራማ እና ፊልም ብንመለከት በፊድዮ ወይም በቴሌቭዥን ይቀርባል። ተውኔት ግን የራሱ የሆነ ቦታ አለው ይህም ቲያትር ቤት ነው። እስቲ ከአዲስ አበባ ትያትር ቤቶች የሚነግረኝ?
13. መ/ት ፡- እሺ እዚያጋ
14. ወ፡- ብሄራዊ ቲያትር
15. ሴ፡- ( )
16. ወ ፡- የሀገር ፍቅር
17. መ/ት፡- ራስ ቲያትር እነኚህ እንግዲህ ቲያትር የሚታይባቸው ቦታዎች ናቸው። ከዚህ በመቀጠል የተመለከትነው የተውኔት አሳባውያንን [ነበረ]። እነማናቸው አልን?
18. ተ፡- [አዎ]
19. ሴ፡-መቼት፣ ግጭት....
20. መ/ት፡- አንድ አንድ
21. ወ፡- መቼት
22. መ/ት፡-መቼት
23. ወ፡- ታሪክ

24. መ/ት፡- ታሪክ

25. ሴተ፡- ትልም

26. መ/ት፡- ትልም

27. ወተ፡- ግጭት

28. መ/ት፡- ግጭት፣ተዋንያን ወይም ገጸባህሪያት የምንሳችው ናችው። እንግዲህ የዛሬው ትምህርታችን ደግሞ ሰዋስው ነው። ሰዋስው... ክዚያ ውስጥም ቅጥያዎች ናችው። ገጽ109 አውጡ(2)

((2.9))

29. __ __ (0.6) ((መጽሃፍ ስማውጣት የተጠቀሙበት))

30. መ/ት፡- ቅጥያዎች ማለት ምን ማለት ነው?

31. ሴተ፡- በአረፍተ ነገር መጀመሪያ እና መጨረሻ የሚገባ

32. መ/ት፡- በአረፍተ ነገር?

33. ሴተ፡- [በሀረግ]

34. ተህ፡- [በሀረግ]

35. መ/ት፡- እሷን የሚያስተካክል

36. መ/ት፡- እሺ ቃል ኪዳን

37. ሴተ፡- በቃሎች መጀመሪያ እና መጨረሻ በመግባት ቃሉን የሚያበዛ

38. ወተ፡- ደህው ቲቸር

39. መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ! ቅጥያዎች እንደኛቹ አብዝዎች ናችው በቃል መጀመሪያና መጨረሻ የሚገቡ ፣እሺ ቀጥል

40. ወተ፡- ቅጥያዎች ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ ሲሆኑ ብቻቸውን ትርጉም የማይሰጡ ናችው። ነገር ግን ከቃላት ጋር ሲጣመሩ ትርጉም የሚሰጡ ናችው።

41. መ/ት፡- አዎ! ቅጥያዎች ብቻቸውን ትርጉም ያሌላቸው ሲሆኑ ከቃላት ጋር በመጣመር ፍች ይሰጣሉ። ለምሳሌ እንደኛው የብዛት ፍች ነው [አይደል?]

42. ተህ፡-[አዎ]

43. መ/ት፡- ለምሳሌ የብዛት ፍችን የሚያመለክቱ ቅጥያዎች እነማናቸው?

44. ተህ፡- ደህው ቲቸር

45. ሴተ፡- -ኦች

46. ሴተ፡- [-ዎች]

47. ተህ፡- [-ዎች]

48. መ/ት፡- እ?

49. ወተ፡- ች

50. መ/ት፡- እነ- እና (.)

51. ወተ፡- ዎች

52. መ/ት፡-እነዚህን ቅጥያዎች ስንመለከት እዚህ ጋር ምልክት የምናደርገው ለምንድነው?

53. ተህ፡- ከፊት [ከፊት መግባቱን]

54. መ/ት፡- [ከፊት መግባቱን] ለማመልከት ነው። ከኋላ ብናደርግስ?

55. ተህ፡- ከኋላ መግባቱን

56. መ/ት፡- ከኋላ መግባቱን ወይም በመጨረሻ መግባቱን ለማመልከት ነው። በጣም ጥሩ! ቅጥያዎች ከቁጥር ብዛት ባሻገር ሌላ ምን አገልግሎት አላቸው?

57. ((ወደኋላ በመመለስ ስታስረዳ))

58. መ/ት፡- አሁን እዚህ ጋር የቁጥር ነው። ነጠላ ቁጥር ላይ እነዚህን ስንጨምር ወደ ምን ይቀየራል?((አብዝ ቅጥያዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ስታስረዳ))

59. ተህ፡- ወደ ብዙ

60. መ/ት፡- እስቲ ምሳሌ

61. ሴት፡- በግ

62. መ/ት፡- በጎች እሺ

63. ወተ፡- ሰው ሰዎች

64. መ/ት፡- ሰው ሰዎች ፤ነገሮችስ? ጠረጴዛ [ጠረጴዛዎች]፣ ወንበር [ወንበሮች]

65. ተህ፡- [ጠረጴዛዎች]፣ [ወንበሮች]

66. መ/ት፡- እሺ እነዚህ የቁጥር አገልግሎታቸው ነው። ሌላስ የቅጥያ አገልግሎት?((ለማንም ተራ ሳትሰጥ ዝም በማለት ወደ ጥቁር ሰሌዳ ፊቷን አዙራለች))

67. ሴተ፡- ጾታን ያመለክታል

68. ሴተ፡-መደብን ያመለክታሉ ((ጣልቃ በመግባት))

69. መ/ት፡- ጾታን ያመለክታል። ሁለተኛው ጾታን ነው። ...,... እስቲ ጾታን ከሚያመለክቱ ቅጥያዎች የተወሰኑትን ንገሩኝ።

70. ወተ፡- ይሀው ቲቸር

71. ወተ፡- ለምሳሌ ልጅ እና ልጂት

72. መ/ት፡- አዎ ልጅ ከሆነ ልጁ ብንስሙ ማን አለ?

73. ተህ፡- ወንድ

74. መ/ት፡- አይደለ

75. ተህ፡- አዎ

76. መ/ት፡- ልጁ ስንል-ሱ ነው ልጂት ስንል ደግሞ(.)

77. ተህ፡- -ኪት

78. መ/ት፡- ልጁ ወንድ መሆኑን ልጂት ደግሞ ሴት መሆኗን ያሳያል። እስቲ ሌላ ደግሞ ተጨማሪ

79. ሴተ፡- መምህር መምህርት

80. መ/ት፡- መምህር መምህርት አዎ! ስለዚህ ት የምትለው ነች ማለት ነው። በጣም ጥሩ ከጾታ ባሻገር ሌላ ቅጥያዎች...

81. ወተ፡- መደብን ያመለክታል

82. መ/ት፡- እሺ መደብን በምንመለከትበት ሰላት መደብ በራሱ በስንት ይከፈላል?

83. ተህ፡- በሶስት

84. __0.9__((በሩ በመንኳኳቱ ምክንያት መቋረጥ ተከሰተ))

85. መ/ት፡- እስቲ እጅ በማውጣት እሺ አለም ጸሀይ

86. ሴተ፡- /በሶስት አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ/

87. መ/ት፡- /በሶስት አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ/ በጣም ጥሩ መደቦች ሶስት ናቸው። አንደኛ መደብ አለ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሶስተኛ መደብ፣ አንደኛ መደብ እስቲ እነማናቸው?

88. ሴተ፡- [እኔ] እና እሱ

89. ወተ፡- [እኔ]

90. መ/ት፡- ነጠላ ቁጥር ሲሆን እኔ ብዙ ቁጥር ሲሆን

91. ወተ፡- እነሱ

92. ሴተ፡- እኛ

93. መ/ት፡- እጅ በማውጣት

94. ተህ፡- እኛ

95. መ/ት፡- እኛ እንደገና በሁለት ይከፈላሉ ነጠላ እና ብዙ ነው። የነጠላ ቁጥር አመልካች እናንተ እንዳላችሁት እኔ ነው። ብዛትን አመልካች ደግሞ..,... [እኛ]

96. ተህ፡- [እነሱ]

97. መ/ት፡- እኛ እሺ↑ ሁስተኛ መደብ

98. ሴተ፡- አንተ አንቺ እናንተ

99. መ/ት፡- ነጠላ ከሆነ አንተ እና አንቺ ብዙስ ከሆነ?

100. ተህ፡- እናንተ፣እነሱ...

101. መ/ት፡- እጅ በማውጣት

102. ሴተ፡- እናንተ

103. መ/ት፡- እሺ↑ ሶስተኛ መደብ

104. ወተ፡- እነሱ

105. መ/ት፡- ነጠላ ቁጥርስ እሱ [እሳ እነሱ]

106. ተህ፡- [እሳ እነሱ]

107. መ/ት፡- በነጠላ ከሆነ እሱ እና እሳ በብዙ ከሆነ እ...

108. ተህ፡- [እነሱ]

109. መ/ት፡- [እነሱ] እንደገና ነጠላን ስንመለከት ጾታን ያመለክታል። እኔ የወል ነው፣ እኛም የወል ነው አንተስ?

110. ተህ፡- የወል

111. መ/ት፡- ወንድ ምን ይባላል?

112. ተህ፡- ተባእት

113. መ/ት፡- አንተ ተባእት ነው እሳ ደግሞ አንስታይ ነች። ስለዚህ እነዚህ መደብን አመልካች ቅጥያዎች እሱ ማለት ነው። እሺ ሴሳ ደግሞ ቅጥያ የምንሳቸው መስተዋድዶችን ነው አይደል..,... መስተዋድዶችን እራሱ እንደ ቅጥያ ልናያቸው እንችላለን__(0.6)__። በቃል መነሻ እና በቃል [መድረሻ] ሳይ__(0.9)__።

114. ሴተ፡- [መድረሻ]

115. መ/ት፡- እሺ መጽሃፋችሁን ተመልከቱ ገጽ 109 ሳይ ክፍል 4 ይልና ሰዋስው፣ የሚከተሉትን መነሻ እና መድረሻ ቅጥያ በመጠቀም ቃላትን መስርቱና አረፍተ ነገር ስሩባቸው። አሁን ቅድም -ዎች እና -ኦች ምንድነው ብለናል

116. ተህ፡- [የቁጥር]

117. መ/ት፡- [የቁጥር] የብዛት

118. መ/ት፡- -ዎች እና -ኦችን ተመልክተናል። ሲ- ምንድነች ...ከቃል በፊት ገብታ የቃል ቅጥያን የምታመለክት ነች እነ በ- ፣ እየ- ፣ስ- እነሱ ደግሞ በቃል መነሻ በመግባት ያገለግላሉ። አስቲ በስ- ምሳሌ የሚሰጠኝ

119. ወ፡- ስሰው ልጅ ምግብና ውሃ አስፈላጊ ነው

120. መ/ት፡- ስሰው ልጅ ምግብና ውሃ- ስለዚህ እዚህ ጋ መነሻ ቅጥያ እናስገባለን። እሺ ስስ

121. ወ፡- ስስ በላ

122. መ/ት፡- እጅ በማውጣት

123. ሴ፡- ስስ እነሱ

124. መ/ት፡- እሺ።። እየ-

125. ሴ፡- እየበላ

126. ወ፡- ልጅቷ በጨለማ እየፈራች

127. መ/ት፡- ልጅቷ በጨለማ እየ።።ፈራች

128. ተ፡- እየጠጣ

129. መ/ት፡- እየጠጣ እህ

130. ወ፡- እየተራመደ

131. መ/ት፡- እሺ

132. ወ፡- እያጠና

133. መ/ት፡- ስለዚህ እየ- የምትለው መነሻ ቅጥያ ነች ማለት ነው። በጣም ጥሩ በ- ነው የሚቀረን በበ- ደግሞ የሚሰራ

134. ወ፡- በግ

135. ተ፡- @@@

136. መ/ት፡- በግ ቃል ነው እሺ ሌላ

137. ወ፡- በበር ገባ

138. መ/ት፡- በበር ገባ በጣም ጥሩ በበር እሺ

139. ሴ፡- በሲትዮጵያ

140. ወ፡- በበኩሉ

141. መ/ት፡- እሺ

142. ወ፡- በአገራችን

143. መ/ት፡- እሺ

144. ሴተ፦ በእቃ

145. ሴተ፦ በ..,...ቤታችን

146. መ/ት፦ ገብቷችኋል! እነዚህ ቅጥያዎች መነሻ ሳይ በመግባት ቃል የሚቀይሩ ናቸው። ገጽ 109 ሁለተኛው ተራ ቁጥር ሂዱ። ቀጥሎ በቀረቡት ቃሳት አረፍተ ነገር ስሩባቸው። ከዚያም የቃሳቱን ሙያ ባለቤትነት ተሳቢነት እያሳችሁ ግለጹ። አሁን ደግሞ ምንድነው የምንፈልገው ባለቤትን የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ነው። ከዚያ በፊት ግን አረፍተ ነገር እራሱ ምን ማለት ይመስሳችኋል።

147. ሴተ፦ አረፍተ ነገር የምንለው የቃሳት ስብስብ እንዲሁም ሀረግ ያለው እና ትርጉም ሊሰጥ የሚችል ነው።

148. መ/ት፦ አዎ በጣም ጥሩ ቃሳቶች አሉበት ፤ሀረጎች አሉበት ተጨማሪ ደግሞ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ተጨማሪ ሌሳ የምትሉት አለ ...,...አረፍተ ነገር በስንት ይመደባል አረፍተ ነገር ውስጥ ምን ዋና ነገሮችን እናገኛለን? እሺ

149. ሴተ፦ ባለቤት

150. መ/ት፦ እሺ ባለቤት እኔ

151. ሴተ፦ ሀረግ

152. መ/ት፦ ሀረግ አይደለም። ሌሳ ተጨማሪ ..,... ለምሳሌ በሀረግ ደረጃ አረፍተነገርን ስንመለከት ትክክል ናችሁ። መነሻ እና መድረሻ ሀረግ አለ። ይሄ ስምን እና ተሳቢን የሚይዘው ነው። ይሄ ደግሞ ግስን የሚይዘው ነው። ነገር አረፍተ ነገር በመዋቅሩ ሶስት ነገር ይይዛል መጀመሪያ አሁን ትብለጽ ያለችው ባለቤት ሲደመር ተሳቢ መጨረሻ.... [ግስ]

153. ተህ፦ [ግስ]

154. መ/ት፦ እነዚህ ሲደመሩ ምን ይሆናሉ [አረፍተነገር]

155. ተህ፦ [አረፍተነገር]

156. መ/ት፦ እሺ በጣም ጥሩ ባለቤት ምን ማለት ነው እሺ ፍቅር

157. ሴተ፦ ድርጊትን ፈጻሚ

158. መ/ት፦ አዎ አረፍተ ነገር ውስጥ ስለሚወራው ነገር ድርጊቱን የሚፈጽመው ሰው ባለቤት ይባላል። ተሳቢ ምንድነው እሺ

159. ሴተ፦ የዚያን ሰውዬ ያከናወነውን የሚገልጸው

160. መ/ት፦ ድርጊት ተቀባይ አሁን ለምሳሌ አልማዝ ቦርሳዋን ለበቀለች ሰጠቻት ብንል አሁን የዚህ ድርጊት ፈጻሚ ማነው እ

161. ሴተ፡- ድርጊት ፈጻሚዋ አልማዝ ነች ተሳቢዋ በቀለች ነች። ግሱ ደግሞ ሰጠች ነው።

162. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ስለዚህ ድርጊት በዋናነት የሚፈጽመውን ባለቤት እንለዋለን። ድርጊት ተቀባዩን...

163. ወተ፡- [ተሳቢ]

164. መ/ት፡- [ተሳቢ] እንለዋለን፤ ማሰሪያውን ወይም ግሱን ደግሞ ግስ እንለዋለን ወይም ማሰሪያ አንቀጽ እንለዋለን። ስለዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት አለው ተሳቢ አለው ግስ አለው። አሁን ወደ ጥያቄያችን ስንመጣ ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱባቸው ከዚያም በመሰረታችሁት አረፍተ ነገር የቃላቱን ሙያ ባለቤትነት ተሳቢነት እያላችሁ ግለጹ። እሺ ትውልድ፤ ወጣቱ ትውልድ ሀገር ተረካቢ ነው። ትውልድ ተሰምሮበታል ትውልድ ምንድነው

165. ተህ፡- ባለቤት =ተሳቢ...

166. መ/ት፡- ቆይ እሺ እድል ሰጥቻለሁ

167. ሴተ፡- ተሳቢ

168. መ/ት፡- ለምን ተሳቢ ላልሽ ወጣቱ ትውልድ ሀገር...

169. ሴተ፡- ወጣቱ ባለቤት ነው ትውልድ ደግሞ ተሳቢ ነው

170. መ/ት፡- እህ እሺ ሴላ የሚያስተካክል

171. ወተ፡- ትውልድ የሚለው ባለቤት ነው

172. መ/ት፡- ትውልድ ባለቤት ነው። ወጣቱ ትውልድ ሀገር ተረካቢ ነው። ወጣቱ ለምንድነው ባለቤት ያልሆነው

173. ተህ፡- ስም ስላልሆነ

174. መ/ት፡- ወጣት ስም ነው አይደለም ወጣት፣አሮጊት፣ሽማግሌ...ቅጽል ናቸው። ቅጽል ደግሞ ባለቤት አይደለም ያንን ባለቤት ማገላመስ ስለሆነ ስራው ትውልድ ነው ባለቤቱ፤ አሁን እናንተ ግንባታ የሚለውን ባለቤት አድርጋችሁ ስሩ። እ

175. ሴተ፡- አባት ግንባታውን ከልጁ ጋር እያፋጠነ ነው።

176. መ/ት፡- አባት አሁን ድርጊት ፈጻሚ ማነው

177. ተህ፡- አባት

178. መ/ት፡- እሺ ግንባታው ምንድነው የሚሆነው [ተሳቢ]

179. ተህ፡- [ተሳቢ]

180. መ/ት፡- እሺ የእጅ ካስ ባለቤት ወይም ተሳቢ በማድረግ ስሩ

181. ሴተ፡- º የእጅ ካስ መጫወት እወዳለሁ º

182. መ/ት፡- የእጅ ካስ መጫወት እወዳለሁ ዋናው ድርጊት ምንድነው

183. ተህ፡- መጫወት

184. መ/ት፡- መጫወት ነው የሚሆነው። መንቀፍ በሚለው አስቲ ሞክሩ እሺ እ

185. ሴተ፡- አባትየው ጥሩ ስራ ስላልሰራ ስልጁ ነቀፈው ማለቴ ልጁን ነቀፈው።

186. መ/ት፡- ልጁን ነቀፈው። ስለዚህ ባለቤት ማነው አባትየው የተነቀፈው ልጅየው ነው። ማህበር በሚለው እሺ

187. ወተ፡- በአራዳ ክፍለ ከተማ በጥቃቅን እና አነስተኛ ማህበር ተደራጅተዋል።

188. ተህ፡- @@@

189. መ/ት፡- ማህበር እዚጋ ተሳቢ ሆኖ ነው የገባው። @እሽ@ እስቲ ልማት በሚለው

190. ሴተ፡- በኢትዮጵያ ሀገራችን ልማት እየተፋጠነ ነው።

191. መ/ት፡- ባለቤቱ ማነው ኢትዮጵያ ነች አይደል- እሺ ልማቱ [ተሳቢ] ሆነ ማለት ነው። እሺ ስነምግባር በሚለው አንተነህ

192. ተህ፡- [ተሳቢ]

193. መ/ት፡- እሺ እንየው

194. ወተ፡- አንተነህ

195. መ/ት፡- እሺ አንተነህ ሶሪ

196. ወተ፡- በስነዜጋ ትምህርት ውስጥ ስነ ምግባር እንማራለን።

197. መ/ት፡- በስነዜጋ አይደለም። ከምንማራቸው ትምህርቶቹ አንዱ ስነዜጋ እና ስነ ምግባር ነው።

198. ወተ፡- ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ስነዜጋ እንማራለን።

199. መ/ት፡- አሁን እዚህ ጋር ስነዜጋ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆነ። እሺ አታላይ ሲያልቅ ነው የመጨረሻ

200. ሴተ፡- አበበች አታላይ ተማሪ ነች።

201. መ/ት፡- አበበች አታላይ ተማሪ ነች። ባለቤቷ ማነች

202. ተህ፡- አበበች

203. መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ እስካሁን ከተማርነው ውስጥ ጥያቄ ካላችሁ ስለ ባለቤት፣ተሳቢ እና ቅጥያ ወደ መጨረሻው ትምህርት ከመሄዳችን በፊት ማለት ነው። እሺ ጥያቄ ካሌላችሁ ወደ መጨረሻው እንሄዳለን። የሚከተሉትን ቃላት በነጻ እና ጥገኛ ምእላድ ከፋፍሉ። አሁን

ምእላድ ልንገባ ነው ማለት ነው። ወደዛ ከመሄዳችን በፊት ምእላድ በራሱ ምን ማለት ነው። በመጀመሪያው መንፈቀ ሰመት ስለተማራችሁት ታስታውሳላችሁ? እስቲ ምእላድ

204. ሴተ፡- ምእላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነ እና ወደ አነስተኛ ክፍል ሊከፈል የሚችል

205. መ/ት፡- ሊከፈል የሚችል ነው የማይችል

206. ሴተ፡- የማይችል

207. መ/ት፡- የማይችል በጣም ጥሩ ምእላድ ማለት በአማርኛ ቋንቋ የመጨረሻው ትንሹ ቅንጣት ምእላድ ነው። ያ ምእላድ ግን ትርጉም ሲሰጡ ወደ ሚችሉ ሊከፈል የማይችል ነው። ለምሳሌ ቤት ቃልም ነው ምእላድም ነው። ቤት ስንል ምን ማለት ነው አንድ መኖሪያ ቤት ማለት ነው አይደል?

208. ተህ፡-አዎ

209. መ/ት፡- ቤት ምእላድ ነው የተባለበት ምክንያት ቤትን ለሁለት ብንከፍለው ምን ትርጉም ያመጣል

210. ተህ፡- ምንም

211. መ/ት፡- ቤ የምትባል ድምጽ እና ት የምትባል ድምጽ ይሰጠናል። ስለዚህ እነዚህ ሁለቱም ትርጉም የላቸውም። ስለዚህ ምእላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነ ወደ ሌላ ቅንጣት ሊከፈል የማይችል ነው። ለምሳሌ ቤቶች ብንል...

212. ሴተ፡- ቤት እና -ኦች

213. መ/ት፡- ቤቶች መክፈል ይቻላል አይቻልም

214. ተህ፡- ይቻላል

215. መ/ት፡- ወደ ምን

216. ተህ፡- ቤት እና ኦች

217. መ/ት አሁን ይህንን ክፍፍል ተመርኩዞ ምእላድ በስንት ይከፈላል

218. ተህ፡- በሁለት

219. ወተ፡- ምእላድ እና ነጻ ምእላድ

220. ተህ፡- አይደለም@@@

221. መ/ት፡- እንደገና

222. ወተ፡- ነጻ ምእላድ እና ጥገኛ ምእላድ

223. መ/ት፡- በጣም ጥሩ አክመል እሺ እስቲ የቤቶችን ነጻ እና ጥገኛ ምእላድ ንገሩኝ

224. ሴተ፡- ነጻ ምእላዱ ቤት ሲሆን ጥገኛ ምእላዱ-ኦች ነው

225. መ/ት፡- -ኦች ነው ስለዚህ ነዳ ምላድ ምንድነው እሺ ያልሞከረ ሰው አንተነህ

226. ወ፡- ነዳ ምእላድ ትርጉም ሲሰጥ የሚችል ጥሬ ቃል

227. መ/ት፡- ነዳ ምእላድ ትርጉም ሲሰጥ የሚችል ጥሬ ቃሉ እሺ ሴላ ጥገኛወስ

228. ወ፡- ስብቻው ሆኖ ትርጉም ሲሰጥ የማይችል

229. መ፡- ብቻውን ሆኖ ትርጉም ሲሰጥ የማይችል [ነገር ግን ከነዳ ምእላድ ጋር ሆኖ]___እ ((ተማሪው በሚደረብበት ወቅት ተማሪው እንዲቀጥል ሆን ብላ እድል ሰጥታዋለች))

230. ወ፡- [ነገር ግን ከነዳ ምእላድ ጋር ሆኖ] ትርጉም ሲሰጥ የሚችል

231. መ/ት፡- ከቃላት ጋር ወይም ከነዳ ምእላድ ጋር በመቀጠል ትርጉም ሲሰጥ የሚችል እሺ ከገባችሁ እሱ ተመልከቱ ገጽ 109 ላይ ሰዎች ይላል ሰዎች ሲከፈል ምንድነው የሚሆነው=

232. ተህ፡-=ሰው እና -ኦች

233. መ/ት፡- ሰው ምንድነው=

234. ወ፡- =ነዳ ምእላድ

235. መ፡- እጅ በማውጣት=

236. ሴ፡- =ነዳ ምእላድ

237. መ/ት፡- ኦች የሚለው=

238. ተህ፡- =ጥገኛ ምእላድ

239. መ/ት፡-ጥገኛ ምእላድ እሺ ገበሬዎች እጅ በማውጣት እሺ ገበሬዎች ያልሞከረ ተማሪ እስካሁን እሺ=

240. ሴ፡- =ገበሬ ነዳ ሲሆን -ኦች ደግሞ ጥገኛ ምእላድ ነው።

241. መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ ስሙ የሚለው እሺ ሃቢብ=

242. ወ፡- ስሙ ነዳ ምእላድ

243. መ፡- ስሙ...

244. ተህ፡- አይደለም

245. ወ፡- [ስም እና -ሉ]

246. ተህ፡- [ስም እና -ሉ]

247. መ/ት፡- ስም እና ሉ በጣም ጥሩ በእናትህ

248. ሴ፡- እናት ነዳ ምእላድ በ ደግሞ ጥገኛ ምእላድ

249. መ/ት፡- ማን

250. ሴ፡- በ

251. መ/ት፡- ሴሳ ደግሞ ባርኔጣዎች

252. ሴተ፡- ባርኔጣ ነዳ ጥገኛ ደግሞ ዎች

253. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ጎበዞች አገሯ እስቲ ያልሞከረ ሰው ካሳ

254. ሴተ፡- አገር ነዳ ምእሳድ ሲሆን---

255. መ/ት፡- እ-

256. ሴተ፡- ዋ ደግሞ ጥገኛ ምእሳድ

257. መ/ት፡- አገር ነዳ ምእሳድ ዋ ድግሞ ጥገኛ ምእሳድ እሺ ገንዘቧ ማህሌት

258. ሴተ፡- ገንዘብ ነዳ -ዋ ጥገኛ

259. መ/ት፡- ደብተርሽ አስምጸሃይ

260. ሴተ፡- ደብተር ነዳ -ሽ ጥገኛ

261. መ/ት፡- እሺ ዘጠነኛ ቤቶች እዛ መጨረሻ

262. ወተ፡- ቤት እና ዶች

263. መ/ት፡- አምራችች እእ ያልሞከረ ሰው ማነው

264. ሴተ፡- አምራች ነዳ -ዶች ጥገኛ

((21.07))

265. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ስለዚህ ነዳ እና ጥገኛ ምእሳድ ገብቷችኋል። እሺ ዛሬ የተማርነውን ትምህርት ስመከለስ ያህል እስቲ በድጋሚ ሲያስረዳን የሚችል ተማሪ መጀመሪያ ስለቅጥያዎች እሺ

266. ሴተ፡- ቅጥያዎች የምንሳቸው በቃል በመነሻ እና በመድረሻ የሚገቡ

267. መ/ት፡- እሺ በጣም ጥሩ!

268. ወተ፡- ቅጥያ የምንለው ብቻቸውን ትርጉም የማይሰጡ ሲሆኑ ከሴሳ ጋር ሲደባለቁ ትርጉም ለዘል የሆኑ ናቸው።

269. መ/ት፡- እሺ ቅጥያዎችን ስንከፋፍል

270. ወተ፡- በቁጥር፣ በመደብ እና በጾታ በቁጥር የምንለው ስምሳሌ -ዎች እና -ዶች በጾታ የምንለው -ሱ እና -ሲት መደብም ለሶስት ይከፈሳል 1ኛ 2ኛ እና 3ኛ አንደኛ መደብ የምንሳቸው እኔ እና እኛ እኔ ነጠላ ሲበዛ ደግሞ እኛ ይሆናል። ሁለተኛ መደብ ደግሞ አንተ እና አንቺ በነጠላ በብዙ ሲሆን ደግሞ እናንተ ሶስተኛ መደብ ላይ ደግሞ እሱ እና እሳ በነጠላ ስብዙ ሲሆን ደግሞ እነሱ

271. መ/ት፡- በጣም ጥሩ እናመሰግናለን ሴላው ቅጥያ በመነሻ ቃል እና በመድረሻ ቃል ነው ሁለቱን የሚነግረን ተማሪ ካለ፤ መነሻ ቅጥያዎች ምንድናቸው መድረሻስ?

272. ሴተ፡- የዛሬው ትምህርታችን ሴላው መስተዋድድ ነው። መስተዋድድ በቃል መነሻ እና በቃል መድረሻ ይገኛል። በቃል መነሻ የምንላቸው ስለ፤ እንደ የመሳሰሉት ናቸው። በቃል መድረሻ የምናገኛቸው ዎች ኦች የመሳሰሉት ናቸው። ሴላው ትምህርታችን ደግሞ አረፍተነገር ነው። አረፍተነገር የምንለው ባለቤት ተሳቢ እና ግስ ያለው ነው። ሴላው ደግሞ ምእላድ ነው።

273. መ/ት፡- እናመሰግናለን! ሶስተኛው ጋ ስንሄድ ምእላድ ማጠቃለያ የሚሰጠን እሺ ትብለጽ

274. ሴተ፡- ምእላድ ማለት የቋንቋ አነስተኛ ክፍል ሲሆን ይህም ሲከፈል የማይችል ነው። ምእላድ በሁለት ይከፈላል። ነጻ እና ጥገኛ ምእላድ ነጻ ምእላድ ትርጉም ያለው ሲሆን ጥገኛ ምእላድ ቢከፈልም ትርጉም ያሌለው ነው።

275. መ/ት፡- ሁላችሁንም እናመሰግናለን የዛሬ ትምህርታችንን በዚሁ ጨርሰናል። የቤት ስራ እጽፍላችኋለሁ ትወስዳላችሁ(0.40)((የቤት ስራውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በማስተዋወቅ የባከነ))

((4.00))

ቀረጻ 2

276. መ/ት፡- ባስፈው ሳምንት የተማርነውን ስማሰታወስ ባስፈው ሳምንት የተማርነው ስለተውኔት ነበር፡፡ እ ተውኔት ምንድን ነው ተውኔት ምንድን ነው የት ነው የምንመለከተው እጅ በማውጣት መልሱ፡፡

277. ተህ፡- ቲየትር ቤት

278. መ/ት፡- አንዳንድ ሰው

279. ወተ፡-ቲያትር ቤት

280. መ/ት፡- ቲያትር ቲያትር ቤት ይታያል ፊልም ደግሞ [ሲኒማ ቤት] ይታያል

281. ተህ፡- [ሲኒማ ቤት]

282. መ/ት፡- ሰለዚህ ቲያትር የራሱ የሆነ ማሳያ አለው፡፡ እሰኪ በአዲስ አበባ የሚገኙ ቲያትር ቤቶችን ሚያስታወሰኝ ከመጨረሻ

283. ወተ፡- ራስ ቲያትር

284. መ/ት፡- ራስ ቲያትር

285. ተህ፡- አገር ፍቅር

286. መ/ት፡- አገር ፍቅር አለ

287. ተህ፡- ብሄራዊ ቲያትር

288. መ/ት፡- ብሄራዊ ቲያትር አለ፡፡ ስለዚህ ቲያትር ለምንድን ነው ቲያትር (.)---0.8--- ((ከውጭ መምህርቷን ለማናገር በመጣ ሰው ምክንያት የንግግር መቋረጥ)) እ እሽ አሁን ለለ ቲያትር ተነጋግረናል አገር ፍቅር አለ ሲኒማ ቤት ብሄራዊ ቲያትር አለ፡፡ ከዚያ ቀጥለን የተነጋገርነው የቲያትር አለባዊያን አሉ አይደል የተውኔት አሳባዊያን አሉ እሺ እነማን እነማን ናቸው ፋንቱ

289. ሴተ፡- ግጥም

290. መ/ት፡- እ

291. ወተ፡- መቼት

292. መ/ት፡- መቼት

293. ወተ፡- ታሪክ

294. መ/ት፡- ታሪክ

295. ወተ፡- ትልም

296. መ/ት፡- ትልም

297. ወ፡- ግጭት

298. መ/ት፡- እሺ

299. ወ፡- ትልም

300. መ/ት፡- ትልም እሺ

301. ሴ፡- @@@º º

302. መ/ት፡- ምክንያቱን አውጭልኝ

303. ሴ፡- º º

304. መ/ት፡- መቼት አለ፣ ትልም ተዋንያን ግጭት አለ ሰው ከራሱ ጋር ሰው ከእንሰሳት ጋር ይጋጫል፤ ሴሳ ምንድን ነው ያለው መቼት ነው ያለውን መቼት ነው መቼት ምንድን ነው እሽ

305. ሴ፡- መቼ እና የት

306. መ/ት፡- የት ና መቼ --- የት ና መቼ ሣይሆን ጊዜና ቦታው ነው ቦታ የት ቦታ ነው የተፈጸመው ጊዜ ጧት ነው ቀን ነው፣ መሸት ነው በጋ ነው ክረምት ነው የተፈጸመው የሚለውን እናያለን። እሽ ይህን ከጨረስን የዛሬው ትምህርታችን ደግሞ ስነ-ግጥም ነው ግጥም ምንድን ነው። እሽ ግጥም ምን ይለሳችኋል መጽሀፍ አገላብጦ ወይም አንብቦ የሚያቅ ካለ እሽ

((2.32))

307. ወ፡- ፈጠራዊ ስራ ነው

308. መ/ት፡- አዎ ግጥም ፈጠራዊ ስራ ነው አንድ ሰው ከሀሳቡ አፍልቆ የሚጽፈው ነው። እሺ እህቴ

309. ሴ፡- የራሱ የሆነ ዜማ አለው እሺ=

310. መ/ት፡- =ግጥም የራሱ የሆነ ዜማ አለው

311. ሴ፡- እንደ ስድ ጽሁፍ ሳይሆን እምቅነት ሀሳብ ያለው ነው=

312. መ/ት፡- አዎ ግጥም እንደማንኛውም ስድ ጽሁፍ ዝርዝር ሳይሆን በተመረጡ ቃላት የሚጻፍ የታመቀ ሀሳብን የያዘ ነው።

313. ሴ፡- ግጥም ውስጥ ስንኝ አለ።

314. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ግጥምን ስንኝ ፣ የመጠቀ ቃላትን በመጠቀም ማራኪና ዜማውን እንዲጠብቅ በማድረግ ውብ ማድረግ ይቻላል። እሺ እህቴ

315. ሴ፡- ግጥም ማለት በስንኝ በስንኝ የተከፋፈለ ማለት ነው።

316. መ/ት፡- በጣም ጥሩ በግጥም ውስጥ የራሡ የሆኑ ቃላት አሉ። ስንኝ አለው፣ ሀረግ አለው፣ ሴላስ ግጥም ውስጥ ምን እናገኛለን እሺ

317. ወ፡- በስንኞች መልክ የተስተካከለ ነው።

318. መ/ት፡- እናመሰግናለን ትንሽ እናስተካክለው በስድ ጽሁፍ ውስጥ አንቀጽ እንዳለ ሁሉ በግጥም ውስጥ ምንድን ነው የሚባለው

319. ሴ፡- አንጓ ወይም አርኬ

320. መ/ት፡- አዎ አንጓ ወይም አርኬ ይባላል። እሺ በጣም ጥሩ ሴላ ምንድን ነው ቀለማት ናቸው እንቆጥራለን ቀለም የምንለው የአናባቢና ተነባቢ ሆሄያት በአንድ ላይ ሲመጡ ማለት ነው እሺ ከመጀመሪያው እንጀምር እና የግጥም ሙያዊ ቃላት የምንላቸው አሉ። የመጀመሪያው ስንኝ ነው..,... ስንኝ ምንድን ነው እሺ መሃል ያለሀው

321. ወ፡- የግጥም አንድ መስመር

322. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ስንኝ የምንለው የግጥም አንድ መስመር ነው።____(0.15)____((በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻ በምትጽፍበት ወቅት)) ሁለተኛው የስንኝ ግማሽ ማን ነው

323. ተ፡- ሀረግ

324. መ/ት፡- በተለምዶ የስንኝ ግማሽ አካልን ሀረግ እንለዋለን ። ግን አሁን እንደዚህ ነው የምትሉት

325. ተ፡- አይደለም

326. መ/ት፡- ታድያ ምንድን ነው የምትሉት

327. ሴ፡- በአንድ ስንኝ ውሰጥ ሁለት ሀረግና ከዚያ በላይ ሊኖር ይችላል።

328. መ/ት፡- በአንድ ግጥም ውስጥ የምትገኝ ስንኝ ሁለት ሀረግ ሶስት ሀረግ አራት ሀረግ አምስት ሀረግ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ሀረግ የስንኝ ግማሽ አካል ሳይሆን ግጥሙን ስናነብ ቆም የምንልበት ቦታ ይህ ትንፋሽ የሚቆምበት ቦታ ስናነብ መሰየት ካቃተን እንዴት እድርገን ማወቅ በየትኛው ስርዓተ ነጥብ ማወቅ እንችላለን ።

329. ተ፡- በነጠላ ሰረዝ

330. መ/ት፡- እጅ በማውጣት እሽ

331. ሴ፡- በነጠላ ሰረዝ

332. መ/ት፡- አዎ ነጠላ ሰረዝ ነጠላ ሰረዝ ምን ታሳየናለች በአማርኛ ቋንቋ የእረፍት ምልክት ነች። ስለዚህ በምናነብበት ጊዜ ለመለየት የምታስችለን አፍታ ቆይታ እንድናረግ ያስችለናል ።

ይሕን የአፍታ ቆይታ እየቆጠርን ስንኝ ውስጥ ስንት ሀረግ እንዳስ እናውቃስን ማለት ነው። ስለዚህ ሀረግ ማለት በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ማለት ነው__(0.11)__። ሶስተኛው የግጥም ሙያዊ ቃላችን...,...

333. ተህ፡- [ቤት]

334. መ/ት፡- [ቤት] ነው። ቤት ምን ማለት ነው

335. ወተ፡- እኔ

336. መ/ት፡- አዎ

337. ወተ፡- በስንኝ የመጨረሻው ቃል ሆሄ

338. መ/ት፡- በጣም ጥሩ በስንኝ መጨረሻ ላይ ያለው የመጨረሻ ቃል ሆሄ ማለት ነው። ስለዚህ ቤት የምንለው ድምጽ ማለት ነው። በአማርኛ ቋንቋ ሰባት ድምጸች አሉ። እነዚህ ድምጾች ያልተሰማ አሉ። ሀ የራሳ ድምጽ አላት፣ ለየራሳ ድምጽ አላት። ስለዚህ ቤት የምንለው የመጨረሻው የስንኝ አካል ነው። የስንኝ ቃል ባልን ጊዜ የመጨረሻው ሆሄ ወይም ደግሞ ድምጽ ቤት እንለዋለን በጣም ጥሩ ከዚያም ቤት የምንለውን ካወቅን ወደ ምንድን ነው የምንመጣው

339. ተህ፡- ቤት መምቻ

340. መ/ት፡- ቤት መምቻ ነው እሺ ቤት መምቻ ምንድን ነው

341. ተህ፡- እኔ ቲቸር

342. መ/ት፡- እሺ

343. ሴተ፡- አንድ ስንኝ ምጣኔውን ሲያገኝ

344. መ/ት፡- አንድ ስንኝ ምጣኔውን ሲያገኝ በ"ን" ና ቀጥሎ "ም" ብሎ ቢጥረስ ወይም ደግሞ ክ፣ ግ ወይም ን ቅ ብሎ ቢጨርስ ሶስቱም በመጨረሻ "እ" የሚል ድምጽ ስላላቸው የዚህ ቤት ምጣኔ ተሳክቶ ሲያልቅ ቤት መታ እንላለን። ቤትደፋስ ለስቡበትና ትነግሩኛላችሁ___(0.5)___። አምስተኛው የአማርኛ የግጥም ቃል ቤት ደፋ ነው። እሺ እስቲ ያልሞከረ እሺ እህቴ

345. ሴተ፡- ግጥሙ ባለሁለት ስንኝ ከሆነና የሁለተኛው ስንኝ ተሳክቶ ሲጨርስ

346. መ/ት፡- እሺ ሁለት ስንኝ ከሆነ አንደኛው ሁለት መጨረሻው ማለት ነው አራት ሲሆንስ ሶስት ጊዜ እየመታ ይሄድና አራተኛው ላይ ይደፋል፣ ስድስት ሲሆንስ አሁንም አምስት ጊዜ ይመታና ይሄድና ስድስተኛው ላይ ይደፋል ማለት ነው። ስለዚህ የመጨረሻው ፍደል ሲጨርስ ቤት መቶ ሲጨርስ ማለት ነው እሽ ቀጥሎ ስድስተኛ ያለን ምንድን ነው [ቤት መምቻ ቃል]

347. ተህ፡- [ቤት መምቻ ቃል]

348. መ/ት፡- ቤት መምቻ ቃል ምንድነው እሽ

349. ወተ፡- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሡ ስንኞች፤----፤

350. መ/ት፡- አዎ የመጀመሪያው ስንኝ የመጨረሻ ቃል ___(0.7)___እሺ ሰባተኛ((ሰባተኛውን የቤት መምቻ ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ቤት መድፊያ ቃል በማለት ጽፋለች)) እሺ መርሻ

351. ወተ፡- በተመሳሳይ ሆሄ_

352. መ/ት፡- ቤት መምቻ ቃል. ቤት መድፊያ ቃል

353. ወተ፡- በተመሳሳይ ሆሄ-----የሚጨርሱ ስንኞች የተመሰረተ ግጥም የመጨረሻ ስንኝ የመጨረሻ ቃል

354. መ/ት፡- አዎ ወይም ይሄ ደግሞ የመጀመሪያ ስንኝ የመጨረሻ ቃል ሲሆን ይሄኛው ደግሞ የመጨረሻ ስንኝ የመጨረሻ ቃል ቤት መድፊያ ይባላል። አዎ በጣም ጥሩ ይሄ ደግሞ ቤት መድፊያ ቃል ይባላል___(0.10)___። በግጥም የመጨረሻው ሙያዊ ቃል መጨረሻ አንድ ነው ማን ነው

355. ሴተ፡- ሆሄ

356. መ/ት፡- ((በፊት እንቅስቃሴ ትክክል አለመሆኑን በመግለጽ)) አንጓ ወይም አርኬ እሺ ምን ማለት ነው እሺ እህቴ

357. ሴተ፡- በአንድ ግጥም ውስጥ የተደረደሩ ስንኞች ሀሳብ ሲሆን በአራት ነጥብ ይለያል።

358. መ/ት፡- አዎ ቅድም እንደነገርኳችሁ አንጓ/አርኬ የምንለው ለምሳሌ ግጥሙ አምስት ሀሳብ ቢኖረው አምስት አንጓ ይኖርዋል። አንድ ግጥም ሁለት ሀሳብ ከያዘ ሁለት አንጓ ወይም አርኬ አለው እንላለን። ይህን አንጓ ና አርኬ እ፡፡ሲላ መጠቆም የምንችለው ምንድነው አንድ ዓ.ነገር በአራት ነጥብ እንደሚዘጋ ሁሉ በግጥም የተነሳ ሀሳብ ሲያልቅ እንዲሁ በአራት ነጥብ ይዘጋል ማለት ነው። ስለዚህ የመጨረሻው ቃል አንጓ ወይም አርኬ በድርሰት አንቀጽ እንደ ምንለው ነው።___(0.16)___ በጣም ጥሩ እኒህን የመሰ ቃላት ካወቅን ወደ ግጥሙ ነው የምንሄደው ግጥሙ ገጽ ስለው ገጹ ልንገራችሁ

359. ተህ፡- (∅)

360. መ/ት፡- ገጽ 112 ልጅቱ የዘመነችቱ ይላል___(0.30)___።እሺ አሁን ይህን ግጥም ተመልከቱ የደበበ ገጣሚ ደበበ ሰይፉ ግጥም ነው። እ የመጀመሪያውን አንጓ ወይም አርኬ ተመልክተን ነው እነዚህን ሙያዊ ቃላት ላይ ተመስርተን ነው የምንሰጠው ብታነቡ መጀመሪያ ለማንበብ ፍቃደኛ የሆነ ተማሪ ሞክሩ! እሺ እህቴ ሞክሪ

361. ሴተ፡- እኔ

362. መ/ት፡- አም ብድግ በይ

363. ሴተ፡- ልጅቷ የዘመነችቱ

ጣት ብድግ ትስውና ትስውና

ፊቷ ፍትግ ፍትግትግ ታደርግና

ዳሴዋን.....

364. መ/ት፡- ድምጽሽን ከፍ ስሁሉም ተማሪ እንዲሰማ አርጊው አይሰማም።

365. ሴተ፡- ልጅቷ የዘመነችቱ

ጥዋት ብድግ ንስት ትስውና

ፊቷን ፍትግ ፍትግትግ

ዳሩ -ላ---ዋን ዳሱላዋን ልቅልቅ ስትል

ሴላ ምናምኗን ዱቅት ሸፋሏን ሸልፍ ትስውና

ከንፈሯን ቅልት ትስውና

366. መ/ት፡- እሺ እናመሰግናለን ሴላ በደንብ የሚያነብልን ወይ ቀጣዩን የሚያነብ

367. ወተ፡- ልጅቷ የዘመነችቱ

ሱሪዋን @---ስምቦጨሙን--@ ሱርት

368. ተህ፡- @@@

ጫማዋን ነጠላውን ጭምት

ቀበቶዋን ሰፊውን ቅብትት

ጃኬቷን የቆዳዋን ጅክት ታደርግና

369. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ሴላ የሚያነብልን እሺ

370. ሴተ፡- ልጅቷ የዘመነችቷ

መስታዋቷን ---

371. መ/ት፡- መስታወቷን

372. ሴተ፡- ትልቋ መስታወቷ ፊት ትቆምና

ፊት ቆምና ሳቅ ግጥጥ ሳቅ ግጥጥ ሳብ

ደርሶ ፍልቅ ፍልቅልቅልቅ ከንፈር ግጥም

ደሞ ክፍት ደሞ ክፍት ደሞ ግጥምጥም

ወደ ኋላ ሂድት ሂድት ደሞም ምልስ ምልስልስ

ሽንጧን ሽንጧ ሰበር ቅልስ ቅልስልስ

ዳሌዋን ወዝ--ወዝ--@@@

373. ተህ፡- @@@-

374. መ/ት፡- @ቀጥይ ቀጥይ--@

ቂብቂብ ቁንቁን

375. መ/ት፡- መሳቅማ አይፈቀድም

376. ሴተ፡- ቅውቅው ጅንን ጅንን

ደግሞ ፈገግ ደግሞ ቅጭም ቅጭምጭምጭም

አይኗን ከፈት ደግሞ ጨፈን ስልምልምልም

ደግሞ ጉልጉል ደግሞ ጥቅስ

ደግሞ ፈገግ ደግሞ ጭልም ጭልምልምልም

አይኗን ክፍት ደግሞ ጨፈን ስልምልምልም

ደግሞ ጉርጥ ደግሞ ጥቅስ ደግሞ @ጉልጉል@...

377. ተህ፡- @@@

378. ሴተ፡- በራሳ ትቀልድ ይመስል

379. መ/ት፡- እሺ እናመሰግናለን ቀጣዩን እሺ ወንድሜ እዚያጋ

380. ተህ፡- ተነሳ@@@

381. መ/ት፡- አንዴ እንደማመጥ እናዳምጠው

382. ወተ፡- ፕሮቫዋን ጥልፍልፍ

ወደ ቁርሳ መስስ ስትል

እማዬዋን ጥድፍ ቁጥት

ትንሽ እህቷን ጥርት

በኩርኩም ግጭት...

383. ተህ፡- @@@

...ገና ከአሁኑ ይውጣብሽ

ስምንድን ጥዋት መነሳትሽ

አባዬዋም እዝን ቁጭት

ጸሎታቸውን ዝንግት

ወይ ጉድ መበላሸት

384. መ/ት፡- ቀጥልበት

385. ወተ፡- ገሪብ ገሪብ እያስች

እማዬዋን እያሳቀስች

አባዬዋን እየገረመመች

ቦርሳዋን እንደ ቦረሰች

ሳስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች

እያንቀጫቀጨች

ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

386. መ/ት፡- እሺ ሁላችሁንም እናመሰግናለን ይሄ ግጥም እንደምታውቁት በምጸት የቀረበ ነው፡፡ ምጸት መሆኑን በምንድነው የምናውቀው

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

በጣም ቶሎ አልመጣችም ልጅቷ ነገር ግን ቶሎ እንደ መጣች አድርጎ በምጸት ነው የነገረን፡፡ አንዲት ልጅ እረሳን እያካኳለች እንደገና ደግሞ ስቤተሰቧ ለእናት አባቷ ጥራዝ ነጠቅ የሆነ ባህሪይን ያሳየች ልጅ ነች፡፡ ከዚህ ትምህርት የምንወስደው ምንድነው እንደ እሳ እንዳንሆን ነው፡፡ እስቲ ከመጀመሪያው እንጀምር

ጥዋት ብድግ ንስት ትስውና

ፊቷን ፍትግ ፍትግትግ

ዳረ -ሳ---ዋን ዳሱሳዋን ልቅልቅ ስትል

ሌሳ ምናምኗን ዱቅት ሽፋሳን ሽፍል ጥቁር

ከንፈሯን ቅልት ቅልት ታደርግና__አሁን እዚጋ ስንመለከት ስንት ስንኝ አለው

387. ተህ፡- ዐ ዐ

388. መ/ት፡- አዎ ስንት ስንኝ አለው ቆጥራችሁ ንገሩኝ

389. ተህ፡-ዐ ዐ

390. መ/ት የት የቱጋ

391. ወተ፡- ሰባት ጥዋት ብድግ ትልና...

392. መ/ት፡- ስንኝ የምንለው የመጨረሻው በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርስ ነው፡፡

ጥዋት ብድግ ንስት ትስውና

ፊቷን ፍትግ ፍትግትግ

ዳሩ -ሳ---ዋን ዳሱሳዋን ልቅልቅ ስትል

ሴሳ ምናምኗን ዱቅት ሽፋሷን ሽፍል ጥቁር

ከንፈሯን ቅልት ቅልት ታደርግና

ንስት፣ፍትግ...ስለዚህ ስንት ስንኝ አለው

393. ተህ፡- አምስት-ስድስት- አራት

394. ወተ፡- አረ አይደለም ሰባት ነው

395. መ/ት፡- አምስት አይደለም ሁሳችንንም የሚያስማማ ቁጠሩ እና ንገሩኝ

396. ተህ፡- አራት- አምስት -ስድስት

397. መ/ት፡- እሺ ስድስት የምትሉ እጃችሁን አውጡ

398. ተህ፡- ይህው

399. መ/ት፡- እሺ አምስት የምትሉ

400. ወተ፡- እኔ

401. መ/ት፡- እሺ እንዴት አልክ

402. ወተ፡- ---((መልሱን ባለማወቅ የተፈጠረ ዝምታ))

403. መ/ት፡- ንስት አንድ እሽት ሁለት ጥፍት ሶስት ጥቁርት አራት ሽፍል አምስት ቅልት ስድስት ስለዚህ አንዱ አምስት አንዱ ስድስት አይልም በተመሳሳይ ከሄድን እሺ ይሄንን ከጨረስን ወደ ሁለተኛው ስንኝ እንሂድና ቀጥለን የምንሰራው ሀረግ ነው።

ሱሪዋን ለምቦጨሙን ሱርት

ጫማዋን ነጠላውን ጭምት

ቀበቶዋን ሰፊውን ቅብት

ጃኬቷን የቆዳዋን ጅክት ታደርግና...ብሎ ነው ያቆመው እስቲ ሀረጉን ንገሩኝ

404. ተህ፡- ሶስት- አራት- አምስት- ስምንት

405. መ/ት፡- ስምንት አይደለ አራት አለ በግማሽ እዚህኛው ጋር ደግሞ [አራት]

406. ተህ፡- [ሸራት]

407. መ/ት፡- ሲደመር ስምንት ይሆናል፡፡ በጣም ጥሩ ሶስተኛው አንን ጋር እንሂድና ቤቱን ትነግሩኛላችሁ

ትልቁ መስታዋቷ ፊት ትቆምና

ፊት ቆምና ሳቅ ግጥ ሳቅ ግጥ ሳቅ

ደርሶ ፍልቅ ፍልቅልቅልቅ ከንፈር ግጥም

ከንፈር ግጥም ደሞ ክፍት ደሞ ግጥምጥም

ወደ ኋላ ሂድት ሂድት ደሞም ምልስ ምልስልስ

ሽንጣን ሽንጣ ሰበር ቅልስ ቅልስልስ

ዳሌዋን ወዝ--ወዝ--

ቂብቂብ ቁንቁን

ቅውቅው ጅንን ጅንን

ደግሞ ፈገግ ደግሞ ቅጭም ቅጭምጭምጭም

አይኗን ክፈት ደግሞ ጨፈን ስልምልምልም

ደግሞ ጉልጉል ደግሞ ጥቅስ

ደግሞ ፈገግ ደግሞ ጭልም ጭልምልምልም

አይኗን ክፍት ደግሞ ጨፈን ስልምልምልም

ደግሞ ጉርጥ ደግሞ ጥቅስ ደግሞ ጉልጉል

በራሳ ትቀልድ ይመስል

አሁን እዚህጋ ቤቱን ንገሩኝ ቤት ማለት የስንኞ መጨረሻ ትይዩ እና ፊደል ነው፡፡

ስምሳሌ የመጀመሪያው ቤት ማነች

408. ተህ፡- ይሀው ቲቸር

409. መ/ት፡-እ

410. ሴተ፡- ና

411. መ/ት፡- ና ነች ትቆምና የመጨረሻዋ ፊደል ና ነች ቀጥሎስ ደግሞ እሺ

412. ተህ፡- ቅ

413. መ/ት፡- ሳቅ ይሳል ቃሉ ቅ ን እንወስዳለን፡፡ ቀጥሎ የመጣውን ቅ አንወስድም ምክንያቱም በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርስ ቤት ነው እንጂ ቤት መምቻ ስለማይሆን ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ

414. ተህ፡- ት

415. መ/ት፡- ከፈት ት ምትለው እሺ ቀጥለን

416. ተህ፡- ም

417. መ/ት፡- እሺ እጅ በማውጣት አንዳንድ ሰው እሺ

418. ወተ፡- ም

419. መ/ት፡- ቀጥለን

420. ወተ፡- ይሀው ሂደት

421. ተህ፡- ት

422. መ/ት፡- ት ከኋላ

423. ወተ፡- ስ

424. መ/ት፡- እሺ እዚጋ

425. ተህ፡- ዝ

426. መ/ት፡- በዚህኛው መደዳ ወንድሜ

427. ወተ፡- ዝ

428. መ/ት፡- እዚህ መደዳ

429. ተህ፡- ን/ም

430. መ/ት፡- ን ካሳችሁ ምን አትጠሩልኝም

431. ተህ፡- ም

432. መ/ት፡- ን ካልን በኋላ ም ይቀጥላል፡፡ በጣም ጥሩ ገብቷችኋል ማለት ነው፡፡ ቤት መታ የምንለው የመጀመሪያው ስንኝ የመጨረሻ ቃል ነው፡፡ ሌላኛው ሀረግ ጋር እንምጣ ደግሞ

ፕሮቫዋን ፕቅልል

ወደ ቁርሷ መስስ ስትል

እማዬዋን ፕድፍ ቁፕት

ትንሽ እህቷን ፕርት

በኩርኩም ግጭት...

...ገና ከአሁኑ ይውጣብሽ

ስምንድን ፕዋት መነሳትሽ

ደግሞ ማለት

አበዬዋም እዝን ቁጭት

ጸሎታቸውን ዝንግት

ወይ ጉድ መበላሸት

433. ቤት መምቻውን ንገሩኝ ቤት መምቻ የምንለው ቤት መትቶ የሚያልቅበት ቦታ ነው ለምሳሌ እዚህኛው ሀረግ ላይ አንድ ልንገራችሁ

ፕቅልል ፤ስትል ፕቅልል ይመታል የሚደፋው ስትል የምትለው ቃል ነች ማለት ነው። ቀፕሳችሁ

434. ተህ፡- ግጭት ስትል አይደለም ግጭት ነው

435. መ/ት፡- እጅ በማውጣት

436. ወተ፡- ግጭት

437. መ/ት፡- አዎ እሺ ቀፕሱ ወንድሜ ቀፕል

438. ወተ፡- መነሳትሽ

439. መ/ት፡- መነሳትሽ ነው

440. ተህ፡- ይሀው ቲቸር

441. ሴተ፡- [ማለት]

442. ተህ፡- [ማለት]

443. መ/ት፡- የሚያስተካክሳት እሺ እህቴ

444. ሴ፡- መበላሸት

445. መ/ት፡- አዎ የሚያልቀው መበላሸት ላይ ነው። እሺ አምስተኛው አንን ጋር እንሂድ ደግሞ

ገሪብ ገሪብ እያለች

እማዬዋን እያሳቀለች

አባዬዋን እየገረመመች

ቦርሳዋን እንደ ቦረሰች

ሳስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች

እያንቀጫቀጨች

ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

አሁን የቀረን አነጓ አርኬ ነው አሁን የቀረን ይሄ የመጨረሻው ስዚህ ግጥም አርኬ ይሆናል ማለት ነው። እሺ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ እነዚህን ሙያዊ ቃላት በሚመለከት ያልገባችሁን አንሱ። እሺ

446. ወ፡- በግጥም ውስጥ የተቀመጠውን እንቆጥራለን

447. መ/ት፡- አዎ ለምንድን ነው ገጣሚው የራሱ የአጻጻፍ ስልት ስላለው ነው፤ አንዳንዱ ዝግዛግ ይጽፋል ፤አንዳንዱ ገባ ብሎ ይጽፋል፤ ቅንፍ ይጨምራል ። አሁን እዚህ ጋር እንዳየነው ቃላት ይደጋግማል። ስለዚህ ይሄ የራሱ ስታይል ስለሆነ አብረን እናያይዘዋለን። እሺ ሴላ ጥያቄ

448. ወ፡- የዘመነች ምን ማለት ነው

449. ተ፡- ዘመናይ

450. መ/ት፡- ዘመናይ ማለት ነው እሳ ዘመናይ ነኝ ብላ ነው ቢተሰጣን ረግጣ የምትሄደው ግን ይሄ ዘመናይነት ነው

451. ተህ፡- አይደለም

452. መ/ት፡- ሰሳ ነው ዘመናይነቱ፤ ነገር ግን እናንተ ማወቅ ያለባችሁ ዘመናይነት ይሄ አለመሆኑን ነው። ዘመናይነት በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ ስንደኛቻችን ስቤተሰቦቻችን በምንሰጠው ክበሬታ፣ መብታቸውን በማክበር፣ ግዴታችንን በመወጣት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መተዋወቅ፣ ማንበብ ወዘተ ነው። እሺ እዚያው ገጽ ላይ ቀጥሎ ያለውን ምንባብ የሚያነብ ስደተኛው አባይን እሺ እህቴ

453. ሴተ ፡-

ከኢትዮጵያ፣ ካፍሪቃውያን ገነት

በጎጃሙ ክፍል፣ ሰከላ ከሚሉት

ከዚያ ከረግረጉ፣ ከግሽ አባይ መሬት

ከዚያ ነው የፈለቅኩ እወቁኝ ሲቃውንት

ከዚያ ተነስቼ ስመሄድ አቀድኩኝ

በኮረኮንች መንገድ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ

በጥንተ ተፈጥሮ እኔን የመሰሉኝ

በግራና በቀኝ አክብረው አጀቡኝ

ትንሽ ወረድ እንዳልኩ ወተት አባይ አሉኝ

ከዚያ ተነስቼ እየተዝናናሁኝ

በጣና ሀይቅ ላይ አለፍኩና ሄድኩኝ

ከዚያ በጎላማ ታላቅ ጅረት ሆንኩኝ

ከዚያ አልፌ ስደርስ ከታላቁ ቁጥኝ

ፏፏቴ ሆንኩና ከሰማይ ወረድኩኝ

ካጠገቤ ቆመው የተመራመሩኝ

ጢስ አባይ አሱና ስሜን አወጡልኝ

ጎጃምን ከጎንደር እያካለልኩት

ወሎንም ከጎጃም እያዋሰንኩት

ሸዋንም ከጎጃም እያካፈልኩት

ወለጋን ከጎጃም እያካለልኩት

መንቀሳቀስ ጀመርሁ ወደተለመድኩት

454. መ/ት፡- እሺ እናመሰግናለን አጨብጭቡላት

455. ተህ፡- ጭብጨባ

456. መ/ት፡- የዛሬውን ትምህርት እዚህ ላይ ጨርሰናል።

((25.9))

ቀረጻ 3

457. ___(0.10)___((በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ የእስቱን ትምህርት ስማስተዋወቅ))

458. መ/ት፡- ገጽ 114 ላይ ግጥሞች አሉ። እነዚህ ግጥሞች ስደተኛው አባይ፣ ሙዚቃ፣ልጅቱ የዘመነችቱ የሚል ግጥም አስ እነዚህን ግጥሞች ከዘይቤ አንጻር እናያለን። ያንን ስመተንተን ያግዘን ዘንድ ዘይቤ ምን ማለት ነው

459. ___(0.18)___((መልስ ስመስጠት ቀድመው የተማሩትን ከደብተራቸው ስማግኘት በሚሞክሩበት ወቅት የተፈጠረ ዝምታ))

((1.00))

460. መ/ት፡- ዘይቤ የምንለው በአማርኛ ቋንቋ ወደ 50 የሚጠጉ የዘይቤ አይነቶች አሉ። ስእናንተ ስ9ኛ ክፍል ይመቿችሁ ዘንድ 13ቱን ነው የምትማሯቸው እነዚህን ዘይቤዎች የምትማሩት በዋናነት እናንተ ግጥም በምትገጥሙበት ሰአት እነዚህን ዘይቤ ከተጠቀማችሁ ዘይቤ ማለት የተደበቀውን የሚያሳይ፣ተስፋ ብንል፣ብስጭት ብንል ምን አይነት ነው እናውቃለን...

461. ተህ፡- አናውቅም

462. መ/ት፡- አናውቅም ዘይቤዎችን ተጠቅመን በአይን ሊታዩ የማይችሉ ነገሮችን ተጨባጭነት እንዲኖራቸው አድርገን ስመግለጽ፣ አንዳንዴ ደግሞ ውበት ቅንጅ ነው፣ በጣም ቅንጅ ናት እንሳስን ሴላው ደግሞ ስማወዳደር፣ ስማነን፣ አጉልቶ ስማሳየት እነዚህ ዘይቤዎችን እንጠቀማለን ስለዚህ ዘይቤ የአነጋገር ስዛ ሆኖ ነገሮችን የበለጠ የሚያብራራ ውበት ያለው የሚማርክ ነገር ነው እነዚህ ዘይቤዎች ከአንደኛው እስኪ እንጀምር እና አነጻጻሪ ዘይቤ፣ አነጻጻሪ ዘይቤ ምን አይነት ዘይቤ ነው___(0.9)___((የዘይቤውን አይነት ስመጻፍ እና ስተማሪዎች ጊዜ ስመስጠት በማሰብ)) እሺ

463. ሴተ፡- በዋናነት ሁለት ሃሳቦችን እያነጻጸረ የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው

464. መ/ት፡- አዎ አነጻጻሪ ዘይቤ የምንለው ሁለት እና ከዚያ በላይ ሲሆን ይችላል አንዱን ያክላል ይመስላል እንደ እያልን ከሴላው ጋር የምናነጻጽርበት ነው ስምሳሌ አማረ እንደ ተዋጊ በረ ተንደርድሮ.እየተንደረደረ መጣ። አሁን እዚህ ጋር የምንገልጸው ድርጊቱን ነው። እየተንደረደረ እንደ ምን ስንል እንደ በረ ስለዚህ አማረ ከበረ ጋር ተነጻጸረ ማለት ነው። ሴላ ደግሞ አለምነሽ ከተቀመተችበት ካስ ይመስል ነጥራ ተነሳች አለምነሽ ከምን ጋር ነው የተነጻጸረችው

465. ተህ፡- ከካስ ጋር

466. መ/ት፡- እጅ በማውጣት እሺ

467. ሴተ፡- ከካስ ጋር

468. መ/ት፡- ካሱ እንዴት ነው አንድ ካስ ብድግ ብድግ እንደሚለው ሁሉ የሳም አነሳስ እንደ ካስ የፈጠነ ነው ለማለት ነው። እሺ ልጁ እንደ ተቆረጠ ዛፍ ዠው ብሎ ወደቀ። የትኛው ነው ዘይቤው እሺ

469. ሴተ፡- እንደ ተቆረጠ ዛፍ___

470. መ/ት፡- ቆም ብለሽ

471. ሴተ፡- እንደ ተቆረጠ ዛፍ የሚለው ልጁ እንደ ተቆረጠ ዛፍ ዠው ብሎ መውደቁን ሲሆን ልጁ የተነጻጸረው ከተቆረጠ ዛፍ ጋር ነው።

472. መ/ት፡- አንድ ሰው አወዳደቁን ምን ይመስላል ስንል ዛፍ ተቆርጦ የሚወድቀውን ያህል አወዳደቁ የከፋ መሆኑን ለመግለጽ ያስችለናል። ሽማግሌው እንደ ሰካራም ይወላገዳሉ። አሁን ሰውዬውን ከምን ጋር ነው ያነጻጸረው እዚያጋ

473. ተህ፡- ››

474. ወተ፡- እኔ

475. መ/ት፡- አዎ

476. ወተ፡- ሽማግሌው ከሰካራም ሰው ጋር

477. መ/ት፡- አዎ አንድ ሽማግሌ ሰውና ጠጥቶ የሰከረ ሰው እንዴት ይራመዳል የሚለውን እንደ ማንጸሪያ ተጠቅመን የሽማግሌውን አረማመድ እንገልጻለን። ሃና እብድ ይመስል ጨርቋን ጣለች ስንልስ እሺ

478. ሴተ፡- እሳ እና እብዷን ነው ያነጻጸረው በትክክለኛው ስንሄድ ጸጉሯን አሳንጨባረረችም እብዷን ስናይ ደግሞ ጸጉሯን አንጨብራለች ስለዚህ ንጽጽሩ በሃና እና በእብዷ መካከል ነው ማለት ነው።

479. መ/ት፡- የሃና ሁኔታ የእብድ ለመሰል ሁኔታዋን ነው እንደ እብድ የተጠቀምነው። አህመድ እንደ ህጻን አስቀሰ። እሺ ያልሞከረ ተማሪ

480. ተህ፡-‹›

481. መ/ት፡- እንደ ህጻን መሃመድ አንድ ትልቅ ሰው ሲሆን ይችላል። ማንጸሪያው ግን ህጻን ነው። ህጻን ሲያለቅስ ስቅስቅ ብሎ እንደሚያለቅስ የሚያሳይ ነው። እሺ አሁን ያየናቸው አነጻጻሪ ዘይቤ በዝርው ነው ወይም በስድ ንባብ ሲቀመጡ ነው። በግጥም ደግሞ ሲገለጹ እንዴት ነው አሁን ትነግሩኛላችሁ

ቆንጆ ጎበዝ ሀብታም አዋቂ ተብሎ

ያዳም ልጅ በመሬት እናዳ አበባ በቅሎ

አንድ እንኳን ሳይታይ በመካካል ተርፎ

ሁሉም ወዳቂ ነው እንደ አበባ ረግፎ

482. መ/ት፡- እሺ

483. ወተ፡- አበባ እና የሰው ልጅ

484. መ/ት፡- አዎ አበባ እና የሰው ልጅ አበባን ብንመለከት አበባ ማደግ ይጀምራል፣ እንቡጥ ያወጣል፣ እያማረ ይሄዳል በኋላ ደግሞ [ይጠወልግ እና ይደርቃል]።

485. ተህ፡- [ይጠወልግ እና ይደርቃል]

486. መ/ት፡-...ህጻን ልጅም በልጅነቱ ይቦርቃል፣ እድሜው እየገፋ ሲሄድ ማስተዋል ይጨምራል፣ በኋላም እየሸመገለ ይሄዳል፣ ይሞታል። እሺ

ወትሮም ከአንጀቴ አይደል አሱን መጠጋቴ

አውሬ መሳዩን ሰው ሙጥኝ ማለቴ

ነበልባል መሰለ አስፈራራኝ ቁጣው

ቅይዱ ጠበቀ ሰንሰለት ማሰሪያው

ለማን አቤት ልበል ለማን ገላጋይ

ከገራው ለመውጣት ግብሩን እንዳላይ

እንደባህታዊ አለም እንደበቃው

ወይስ ልግባ ጫካው ሁሉንም በትኜው

የዚህ ግጥም አነጻጸሪ ዘይቤስ

487. ወተ፡- ሰውዬው እና አውሬውን ነው ያነጻጸረው፤ ያነጻጸረው ደግሞ የሰውዬውን ሃይለኛነት ነው።

488. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ይህች ሴት ባሏ ያስከፋት ሴት ናት። ከሱ ጋር መኖሩ እንደከበዳት አውሬ መሳዩን ሰው ሙጥኝ ማለቴ ትላለች። እንደ ባህታዊ አስም እንደበቃው ምንን ብዩ ገዳም ልግባ ወይ የምታነጻጽረው ክፋቱ የአውሬ እንደሆነባት ነው። እሺ አነጻጻሪ ዘይቤ ላይ ጥያቄ ላላችሁ....

489. ወተ፡- የለንም

490. መ/ት፡- እሺ ከሌላችሁ ወደ ሁለተኛው እንሄዳለን። ተለዋጭ፤___(0.15)___ተለዋጭ ዘይቤ ምን ማለት ነው እሺ መጨረሻ

491. ወተ፡- ተለዋጭ ዘይቤ የምንለው የአን./ተለዋጭ ዘይቤ የምንለው የአንዱን ባህርይ ለአንዱ አሳልፎ መስጠት ነው።

492. መ/ት፡- የአንዱን ባህርይ ለአንዱ ብቻ መስጠት ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መለወጥ ነው። ራሱን መሆን ነው። አሁን ቅድም እንደ ተዋጊ በረ፤ እንደ ኳስ እያልን ነበር። አሁን ግን ሰውዬውን ሙሉ በሙሉ ተለውጦ ወደዛ እንደተቀየረ ማድረግ ነው። ለምሳሌ፡- ፋጡማ ጸሃይ ነች። እንደ ጸሃይ ነች አላልኩም አይደል...

493. ተህ፡- አዎ

494. መ/ት፡- ፋጡማ ሙሉ በሙሉ ወደ ጸሃይ ተለወጠች። ምን ማለት ነው ጸሃይ ነች ስንል

495. ወተ፡- ታምራለች

496. መ/ት፡- ቆንጆ ነች ታምራለች ማለታችን ነው። እሺ እ.. አበበ ሲበላ ጅብ ነው። እሺ

497. ሴተ፡- ማለት አበበ አበላሉ ወደ ጅብ መቀየሩን ነው

498. መ/ት፡- አዎ አመጋገቡ ከሰው ልጅ ወደ ጅብ መቀየሩን ነው። እጇ በረዶ ሆነ። እሺ

499. ሴተ፡- እጇን ከበረዶ ጋር አገናኝቶ በረዶ ስለሚቀዘቅዝ እጇም በጣም መቀዝቀዙን ነው።

500. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ሙሉ በሙሉ ቀየርነው ማለት ነው። ይሄ በዝርው ሲቀርብ ነው በግጥም ደግሞ እስቲ እ..

ሲገረጉር ሲገረጉር

ከዚያ ባህር አሳ ሲያጠምድ

ከውሃ ውስጥ ከባህሩ እየወጣ ዘንዶ

ዘንዶው ያልፈለገው ያላሰበው ነዶ

ሲጎረጉር ሲጎረጉር የሰው ልጆችን ልብ ባህር

አንድ ጊዜ ሰውና አውሬ መርም የሚመር

ሲግረጉር ሲጎረጉር የሰው ልጆችን ልብ ባህር

ወጣበት አውሬ ነገር ማርስ ደመራል መራር መራር

የሰውን ልጅ ባህር

501. መ/ት፡- አሁን የሰው ወደ ምንድነው የተሰወጠው

502. ተህ፡- ወደ ባህር

503. መ/ት፡- የሰው ልጅ ሃሳቡ በሃሳብ ሲወጣ ሲወርድ ስማስት ነው። እ.. አዲስ ነገር ሲፈጥር ነው።

አካሄድሽ ደምጣ አረማመድሽ

ፕርስ አገላስፕሽ ከከንፈርችሽ

ትህትናሽ አታላይ ጅንንነትሽ

አንገትሽ ብርሌ ወይኒቱ ማር ነሽ

ተሰዋጭ ዘይቤ እህ

504. ወተ፡- ዐ ዐ

505. መ/ት፡- አንገትሽ ረጅም ነው ከማስት ይልቅ [ብርሌ ነው]

506. ተህ፡- [ብርሌ ነው]

507. መ/ት፡- ሌላስ እሺ

508. ወተ፡- ማር ነሽ

509. መ/ት፡- ማር ነሽ፤ ወይኒቱ ሲላት ራሱ ሴትዮዋን ወደ ወይን ቀየራት። እሺ በጣም ጥሩ ሶስተኛ የሚሆነው ሰውኛ ነው። እሺ ሰውኛ ዘይቤ ምን አይነት ዘይቤ ነው እሺ

510. ወተ፡- የሰው ልጅን ልዩ ባህርይ ሰው ላልሆኑ ነገሮች መስጠት

511. መ/ት፡- በጣም ጥሩ እንስሳትም ሲሆኑ ይችላሉ። ሰው እንደ ሰዎች አይደሉም ነገር ግን እንዲያስቡ፣ እንዲበሉ፣ እንዲጣሉ፣ እንዲዋደዱ ስናደርጋቸው ወደ ሰውኛ ዘይቤ ቀየርን ማለት ነው። እሺ

ጸደይ ልትመጣ ነው ደገሰች አበባ

ቁንን ልትመጣ ነው አቀረበች ኮርባ

አደይም ጀመረች ቀይ ቀለም ትቀባ

በለስ ከተፍ አለች ሰውነቷን ታጥባ

ከወይኒቱ ጋራ አደራሽ ልትገባ

512. መ/ት፡- እስቲ እዚጋ ሰውኛ ዘይቤው የትኛው ነው

513. ወተ፡- ማለት የሰውን ባህርያት ስተስያዩ ነገሮች ስጸደይ መስጠት ስምሳሌ የሰው ባህርይ የሚሆነው ገላን መታጠብ እና እነሱም ሲለወጡ ሰውኛ ይሆናል።

514. መ/ት፡- በጣም ጥሩ እነዚህ አትክልቶች ናቸው ግብዣ የተጠሩት ግብዣ ቦታ ሲሄዱ ነው። ጸደይ ልትመጣ ነው ስንል ጸደይ ወራቷን ሳይሆን እንደ ሰው ሆና ልትመጣ መሆኗን፣ ድግሱን የደገሰችው ደግሞ [አበባ]....

515. ተህ፡- [አበባ]

516. መ/ት፡- አበባ ነች አበባ ድግስ አይደግስም፣ የሰውን ባህርይ ወስዳ ደግሳለች። በለስ የተባለችው ዛፍ ደግሞ ወደ ግብዣ ስመሄድ ገላዋን ታጥባለች፣ ብቻዋን እንዳትሄድ ደግሞ ከወይን ጋር ተዘጋጅታለች። ስለዚህ የሰውን ባህርይ ሰው ሳልሆነ ነገር በመስጠቱ ግጥሙን ሰውኛ ዘይቤ እንለዋለን።

አለቀሰ ብዕር

በዱልዱም ቢቀርጹት ብዕር አለቀሰ

እርቁም ቀለም ሳይሆን ደም እያለቀሰ

ያሳሰበው ሲጻፍ ያሰበው ተወጦ

እውነት ሲጨነግፍ ጽልመት ሲታይ ወጥቶ

ውሸት ሸፋን ዘርቶ፣ደምቆ፣በልቶ፣ገልቶ

ዐ ዐ

ደም እያፈሰሰ ብእር አስቀሰ

አሁን እስኪ ማነው የሰው ባህርይ የወሰደው

517. ወተ፡- ይሀው

518. መ/ት፡- እሺ

519. ተህ፡- ብእር

520. መ/ት፡- ብእር ነው። ሰው ነው አይደል እንባ አውጥቶ የሚያስቅሰው ነገር ግን ደራሲው የተጠቀመው በብእር አማካኝነት ውሸት ገኖ በመታየቱ እውነት በመጥፋቱ የሚጸፈው ደግሞ ብእሩ ስለሆነ ብእሩ ሲያስቅስ አሳይቶናል። ስለዚህ የሰውን ባህርይ የወሰደው ብእር ነው ማለት ነው። እሺ

አንድ ቀን ብረት ድስትን አለው

እኔን ነው ዐ ዐ መልክህ የሚመስለው

ዐ ዐ ባታውቀው ነው እንጅ

ከዛሬ ጀምሮ እንሁን ወዳጅ

እሺ እዚጋ የሰው ባህርይ የሚያገኙት እነማናቸው እሺ

521. ሴተ፡- እሺ እዚህ ጋር ስንመለከት ሸክላ ድስት እና ብረት ድስትን ነው። ብረት ድስት ምን ይለዋል ወንድሜ ነህ አብረን ብንኖር ይለዋል። እንኑር የሚለው አነጋገር የሰው አነጋገር ነው። ሴላ ደግሞ ብረት ድስትም ሸክላ ድስትም አይናገሩም ነገር ግን እንደ ሰው ሲናገሩ ይታያል። ይህ ደግሞ የሚያመለክተን ሰውኛ መሆኑን ነው።

522. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ወንድምነት እህትማማችነት ያለው በሰው መካከል ነው። በብረት ድስት በሸክላ ድስት በእውኑ አለም የለም። ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ግጥሙን ሰውኛ ያደርጉታል። በጣም ጥሩ አፈተኛው የዘይቤ አይነት እንቶኔ ነው። ይህ ዘይቤ ምን አይነት ነው እሺ አማን

523. ወተ፡- በአጠገብ ያሌለን ነገር አቅርበን እንናገር↓

524. መ/ት፡- ሰዎ በሕጠገብ ያሴሰን ሰው ወይም ነገር የማይናገር ነገር እንደሚሰማ እና መልስ እንደሚሰጥ በመቁጠር ስናናግር ነው። ለምሳሌ ምነው አዲስ አበባ ጭንቅሽ በዛ እንላለን። አዲስ አበባ ከተማ ሰምታ መልስ ትሰጣለች

525. ተህ፡- አትሰጥም

526. መ/ት፡- አትሰጥም ግን ያለው የኑሮ ውድነት፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ የተለያዩ ነገሮችን ችግር ለመግለጽ ስንል አይ አዲስ አበባ ጭንቅሽ በዛ እንላለን። ስለዚህ ይህ እንቶኔ ዘይቤ ነው ይህች ከተማ ሰምታ መልስ ለለማትሰጥ ነው። አንዳንዱ ደግሞ ወደ ተራራ ወጥቶ እባክህ አንተ ተራራ አጫውተኝ ይላል። ተራራ መልስ ይሰጠዋል [አይሰጠውም]

527. ተህ፡- [አይሰጠውም]

528. መ/ት፡- ግን እንደሚያጫውተው በመቁጠር ለተራራው ሲናገር ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እ እነዚህ ጠንቂይ ቤት መተት አምላኪዎች ጋር ብንሄድ ደግሞ የአባቴ ውቃቢ ተለመነኝ ብለው ሲሉ ይችላሉ። ውቃቢ ምን እንደሆነ አይታወቅም ነገር ግን ሃሳባቸውን ልመናቸውን በእንቶኔ ዘይቤ ያቀርባሉ።

ምነው ጸሃይቱ ምነው ደማቂቱ

ያለወትሮሽ ወጣሽ ያውም በጥዋቱ

ያውም በጥምቀቱ ሳንበላ ከአሸቱ

ሳንጠጣ ከግቱ ህይወትን ኮነንሽው

ወሎን አስተኛሽው ትግሬን አሸነፍሽው

ቀን በቀን በላሽው

ማንን ነው ደራሲው እየጠየቀ ያለው

529. ተህ፡- ጸሃይን

530. መ/ት፡- እጅ በማውጣት እሺ

531. ሴተ፡- ጸሃይን

532. መ/ት፡- ለምንድነው የጠየቃት

533. ወተ፡- ማስት ጸሃይ ድርቅ እያመጣች ስለሆነ ያንን ቦታ ደረቅ እንዲሆን እያደረገች ስለሆነ...

534. መ/ት፡- እህ

535. ወተ፡- ጸሀይን ነው የሚያናግረው ማለት ነው

536. መ/ት፡- አዎ ምን ሆነሽ ነው እያለ እየጠየቃት ነው። ይሄ ግጥም የ77ቱን ድርቅ መሰረት አድርጎ የተገጠመ ግጥም ነው። ወሎን አስተኛሽው ብዙ ወገኖቻችን በረሃብ ምክንያት ሞተዋል። ትግሬን አሸነፍሽው ቀን በቀን በላሽው መብላት ራሱ... በዝናብ እጦት ምክንያት እንደሞተ ሲገልጽልን ነው። እሺ

ተነገር አንተ ሀውልት አንተ አክሱም ያለህው

እስክላሬ ድረስ ብዙ ጉድ ያየህው

አንተ ህያው ድንጊያ ብዙ ያሳለፍከው

ሶስት ሺህ ዘመናት እዚያ ተገትረህ

እስቲ ያየሀውን ንገረኝ ዘርዝረህ

እኔ ብእር ይዜ ታሪክ ልጻፍልህ

ደራሲው ማንን ነው እያናገረ ያለው

537. ተህ፡- ሃውልቱን

538. ወተ፡- አክሱምን...

539. መ/ት፡- እሺ

540. ወተ፡- እሱን ሲያናግር የቻለበት ምክንያት አክሱም በአድዋ ጦርነት ላይ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር በመጣችበት ሰላት ላይ ያ

541. መ/ት፡- አዎ ታሪክ ነው የሚጠይቀው 3000 ዘመን ቆመን እዛ ተገትረህ ምን እያደረግክ ነው እስቲ ስለ ኢትዮጵያ ንገረኝ፣ ስለ ኢኮኖሚዋ፣ ስለ ተሪካ፣የታዘብከውን ንገረኝ ብዙዎች ሲያልፉ አንተ ግን ቆመህ ቀርተሃል እያለ ሲያናግረው ነበር። ሀውልቱ ግን አያናግረውም። ስለዚህ እንቶኔ ዘይቤ መልስ የማይሰጥን መጠየቅ፣ መማጸን፣ ማናገር ያካትታል

ማስት ነው። አሺ ይሄን ካየን ወደ ገጽ 114 ሂዱ። ግጥሞች አሉ። በፍቃደኝነት ግጥሙን የሚያነብ

542. ወተ፡- ልጅቱ የዘመነችቱ

ገሪብ ገሪብ እያለች

እማዬዋን እያሳቀለች

አባዬዋን እየገረመመች

ቦርሳዋን እንደ ቦረሰች

ሳስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች

እያንቀጫቀጨች

ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

ደበበ ሰይፉ በ1980 ከ40 ገጽ ጀምሮ የተወሰደ

543. ተህ፡- @@@

544. መ/ት፡- እናመሰግናለን ግጥሙን ስላነበበልን! አሁን ይሄ ግጥም ምጸት ዘይቤ ነው። አምስተኛው ምጸት ዘይቤ ፤ምጸት ዘይቤ ምን አይነት ነው ታስታውሱ ከሆነ

545. ወተ፡- ምጸት ዘይቤ የምንለው ስምሳሌ አንድ ጥቁር ሰው ሲመጣ ውይ ቀዮ መጣ ብንለው ሽሙጥ ማለት ነው።

546. መ/ት፡- አዎ

547. ሴተ፡- ምጸት ዘይቤ የምንለው አንድን ሰው የምናሞግስ መስለን በተቃራኒው የምንሰድበው ወይም የምናሽሚጥጠው ከሆነ ነው።

548. መ/ት፡- በጣም ጥሩ አሺ↑

549. ወተ፡- ዐ ዐ

550. መ/ት፡- አዎ ግን ሲናገር እውነት ነው፡፡ የምንናገረውን ነገር ያደምቃል እንጂ ዘይቤው ውሸት አይደለም፡፡ አሁን ምጸትን ስንመለከት እኮ ያ ሰውዬ ፈረንጅ ነው፡፡ እሱ እንደነገረን ጥቁር ሰው ሲመጣ ፈረንጅ ነህ ስንለው ምን ማለታችን ነው? ቀይ አይደለህም የሚለው እውነት አለ፡፡ ለምሳሌ፡- ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች

እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች

አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላለች

በመሃሉ 24 ሰአት አለ አይደል

551. ተ፡- አዎ

552. መ/ት፡- ግን እሱ አሳጥሮ በመግለጹ ነው፡፡ አሁን ለምሳሌ አንድ እናት ልጇ ብድግ አድርጎ ብርጭቆ ቢሰብር እሰይ ጎሽ ለበረው...

553. ወ፡- ጨርሰው

554. መ/ት፡- ብትለው ለበረው ማለቷ ነው

555. ተ፡- አይደለም @@@

556. መ/ት፡- ልጁ ራሱ ከአሁን በኋላ ወየሁልህ እያለችው መሆኑ ይገባዋል፡፡ ከፊት ለፊት ሲታይ ያንን ነገር አድርጉት ፈጽሙት ይመስላል፡፡ እሺ ሁለተኛውን ግጥም የሚያነብልን

557. ሴ፡- ስደተኛው አባይ

ከኢትዮጵያ፣ ካፍሪቃውያን ገነት

በገጃሙ ክፍል፣ ሰከላ ከሚሉት

ከዚያ ከረግረጉ፣ ከግሽ አባይ መሬት

ከዚያ ነው የፈለቅኩ እወቂኝ ሲቃውንት

ከዚህ ተነስቼ ለመሄድ አቀድኩኝ

በኮረኮንች መንገድ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ

በጥንተ ተፈጥሮ እኔን የመሰሉኝ

በግራና በቀኝ አክብረው አጀቡኝ

ትንሽ ወረድ እንዳልኩ ወተት አባይ አሉኝ

558. መ/ት፡- ጨረሽ

559. ሴተ፡- አዎ((በጭንቅላት እንቅስቃሴ))

560. መ/ት፡- የሚየግዛት እሺ

561. ወተ፡- ቀጣዩን

562. መ/ት፡- አዎ ከዚያ ተነስቼ

563. ወተ፡- ከዚያ ተነስቼ እየተዝናናሁኝ

በጣና ሀይቅ ላይ አስፍኩና ሄድኩኝ

ከዚያ በጓላማ ታሳቅ ጅረት ሆንኩኝ

ከዚያ አልፌ ስደርስ ከታላቁ ቂጥኝ

ፏፏቴ ሆንኩና ከሰማይ ወረድኩኝ

ካጠገቤ ቆመው የተመራመሩኝ

ጢስ አባይ አሉና ስሜን አወጡልኝ

ጎጃምን ከጎንደር እያካለልኩት

ወሎንም ከጎጃም እያዋሰንኩት

ሸዋንም ከጎጃም እያካፈልኩት

ወለጋን ከጎጃም እያካለልኩት

መንቀሳቀስ ጀመርሁ ወደተለመድኩት

564. መ/ት፡- ሁለታችሁንም እናመሰግናለን ስደተኛው አባይ የየትኛው ዘይቤ ነው እሺ

565. ወተ፡- ሰውኛ

566. መ/ት፡- ሰውኛ ነው አይደለ

567. ተህ፡- አዎ

568. መ/ት፡- አባይ እንደ ሰው ደንዛል፣መነሻዬ ጎጃም ነው ይላል፣እ ጎረቤቶቹን ይጠቅሳል፣ስም አለኝ ይላል፡፡ ስለዚህ ይሄ ሰውኛ ዘይቤ ነው፡፡ ቀጥሎ ሙዚቃ የሚል ግጥም አለ ቀጥል

569. ወ፡- ፈልቀሽ የተገኘሽ ከሸበርት ራስ

ከቢቶቨን ናላ ከሞዛርት መንፈስ

ከቮፐን ትካዜ ከያሬድ ልቦና

መዓዛ የሞላብሽ የብስጭት ቃና

ረቂቁ ድምጽ ሁይ ውቢቷ ሙዚቃ

ንጹህ እንደ ጸሃይ ውብ እንደ ጨረቃ

የጨዋታሽ ስዛ የድምጽሽ ፍስሃ

መሳይ ድንቅ አረቂ የነፍስ እህል ውሃ

አገርሽ ገነት ነው ሰፈርሽም ኤደን

በሰማንሽ ቁጥር በሃሳብ መንገድ ሄደን

ታጫውችናለሽ በህሊና ቁንቁ

ነፍሴ ከአንቺ ጋር በመተዋወቁ

ትሽቆጠቆጣለች ድምጽሽን ስትሰማ

ጠባይሽ ሲገለጥ በምድራዊ ዜማ

መስሎ የሚመነጭ ከገነት የወጣ

ጣእሙ አይጠገብም ቢጠጣ ቢጠጣ

የትካዜ ከርቤ የብስጭት እጣን

የመልእኮች ቁንቁ የሱራፌል ልሳን

ቃናሽ ነፋስ ሆኖ ድምጽሽ ሰረገላ

ውሰጃት እባክሽ ነፍሴን ወደ ሴላ

570. ተህ፡- ጭብጨባ

571. መ/ት፡- እናመሰግናስን ደራሲው በየትኛው ዘይቤ ነው ያቀረበው ብላችሁ ታስባላችሁ

572. ወተ፡- እንቶኔ

573. መ/ት፡- እንቶኔ ስምን አልክ እንግዲህ ሴሎቻችሁ ሞክሩ

574. ወተ፡- እንቶኔ ሙዚቃ በተፈጥሮው ሰው አያናግርም ስለዚህ እንቶኒ ዘይቤ ነው።

575. መ/ት፡- እሺ ሴላ

576. ሴተ፡- ሰውኛ

577. መ/ት፡- እ

578. ወተ፡- ሰውኛ አለበት አሁን እዚጋ

ከቮፐን ትካዜ ከያሬድ ልቦና

መዓዛ የሞላብሽ የብስጭት ቃና

ብሎ

ንጹህ እንደ ጸሃይ ውብ እንደ ጨረቃ

ምስያ ይመስላል።

579. መ/ት፡- ስለዚህ የሚያስተካክል እንደ ይመስላል ትመስል የየትኛው ዘይቤ መገለጫ ነው

580. ተህ፡- አነጻጻሪ

581. ሴተ፡- አነጻጻሪ ዘይቤ ነው። ምክንያቱም ንጹህ እንደ ጸሃይ ይላል። እንደ የሚለው ቃል አነጻጻሪ ነው።

582. መ/ት፡- አዎ አንድ ግጥም ውስጥ ብዙ ዘይቤዎችን መጠቀም ይቻላል። ንጹህ እንደ ጸሃይ ውብ እንደ ጨረቃ ሲል አነጻጻሪ ነው።መልሶ ደግሞ ሙዚቃን የነፍስ እህል ውሃ ወደ ምን ቀየረው

583. ተህ፡- ወደ ውሃ

584. መ/ት፡- ጠምቶ ወደሚጠጣ ውሃ ተለዋጭ ዘይቤ ነው።

በሰማንሽ ቁጥር በሃሳብ መንገድ ሄደን

ታጫወችናስሽ በህሊና ቋንቋ

ነፍሴ ከአንቺ ጋር በመተዋወቋ

ትሸቆጠቆጣለች ድምጽሽን ስትሰማ

ጠባይሽ ሲገለጥ በምድራዊ ዚማ

ደግሞ ሴላ የተማራችሁት ዘይቤ አለ። አሲገሪ ይባላል ታስታውሳላችሁ

585. ____

586. መ/ት፡- ረቂቅ የሆኑ ነገሮች የማጨበጡ ነገሮች ስምሳሌ፡- ሙዚቃ እንሰማለን እንወዳለን እንላለን እንጂ ምን አይነት ቀለም እንዳለው ማወቅ እንችላለን [አንችልም]

587. ተህ፡- [አንችልም]

588. መ/ት፡- እንደዚህ የረቀቀ ተስፋ፣ምኞት አሁን ስምሳሌ ቢጫ ምንድነው

589. ወተ፡- ተስፋ

590. መ/ት፡- ተስፋ አይታይም አይደል እነዚህ ረቂቅ የሆኑ ሃሳቦችን በአሲገሪ ዘይቤ እናቀርባለን። ስለዚህ ሙዚቃ የረቀቀ ሃሳብ ነው። አሲገሪ ዘይቤም አለው ማለት ነው። እንደገና የትካዜ ክርቤ የብስጭት እጣን ሙዚቃ ወደ ምን ተቀየረ [ወደ እጣን]

591. ተህ፡- [ወደ እጣን]

592. መ/ት፡- ወደ ክርቤ የሚባል እጣን የመሳእክት ቋንቋ የሱራፌል ልሳን ወደ ስምሳክ ቋንቋ ተለዋጭ ነው።

ቃናሽ ነፋስ ሆኖ ድምጽሽ ሰረገላ

ውሰጃት እባክሽ ነፍሴን ወደ ሴላ

ስለዚህ በዚህ ግጥም ውስጥ በርካታ ዘይቤዎች አሉ። እስቲ ሌሎች ግጥሞችን እንደ እያነበብን እንይ። አንድ ተማሪ ያነባል። ሴላው ደግሞ የዘይቤውን አይነት ይናገራል። እጅ በማውጣት ግጥሙን የሚያነብ አሺ መልሱን ትነግሩኛላችሁ ጮክ ብለህ አንብብ

593. ወተ፡- ጠዋት ብትታይም ጸሃይ ክፍ ብላ

የማታ የማታ እሳም አሸቆልቅላ

አይቀርም መጥሰቅ

አይቀርም መውረዷ

ብርሃኗን ሰውሪ ከአይን መጋረጃ

ሰውንም ስናየው ሳስ በህይወቱ

እሸት ነው ስጋ በወጣትነቱ

የወጣቱ ጉዞ ምንም ቢበረታ

አይቀርም መድከሙ የማታ የማታ

594. መ/ት፡- በጣም ጥሩ ይሄ ግጥም ምን አይነት ዘይቤ ነው ያሰው የሚነግረኝ

595. ወተ፡- ይህው ቲቸር

596. መ/ት፡- ያልሞከረ እሺ

597. ሴተ፡- ምስያ ነው ምክንያቱም መጀመሪያ ስንመለከተው የአኗኗር ሁኔታ ነው የነገረን የጸሃይ እና የሰው º º

598. መ/ት፡- በጣም ጥሩ እናመሰግናለን ምስያ ዘይቤ የሚባለው በግጥም ብቻ የሚቀርብ ዘይቤ በዝርው የማይቀርብ ነው ። ይሄ ምስያ ዘይቤ በግጥም የሚቀርበው ከላይ የሚገለጸው አንዱ ከታች ይደረግና የላይኛውን አጉልቶ እንዲያሳይ የሚደረግ የዘይቤ አይነት ነው። እሺ እስካሁን ከተማርነው ጥያቄ ካላችሁ

((29.43))

599. ___ (1.00)___

600. መ/ት፡- ከገባችሁ እናመሰግናለን!

((1.05))

ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የራሴ መሆኑንና በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሁፎችና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በስሜና ፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ሔኖክ ገመዳ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ